# የመዝሙረ ዳዊት ጥናት

ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የተዘጋጀየኢትዮጵያውያን ወንጌላዊት
- ዳላስቅዱሳንን የማጽናት አገልግሎት

Ethiopian Evangelical Baptist Church
2822 S Jupiter Rd, Garland TX 75041
www.wongelkedallas.org
Tel.2147030100
Fax: 2147030161

# መዝሙረ ዳዊት

መዝሙረ ዳዊት ከብሉይ ኪዳን 39 መጽሐፍት አንዱ ሲሆን 150 ምዕራፎች ያሉትና **ዳዊትን ጨምሮ ብዙ ዘማሪዎች የዘመሩዋቸው የመዝሙሮች ስብስብ ነው።** ከ1000 በላይ በሆኑ ዓመታት የተደረሰ ሲሆን ስለ እግዚአብሔር ህልውና በግልጽ የሚያስረዳ፣ የእግዚአብሔርን ባህርይ የሚያስተምር፣ብዙ ባህልና ታሪክን ያካተተ፣ ክፉዎችንና ጻድቃንን የሚያነጻጽር፣ የሰዎችን የህይወት ገጠመኞችን የሚያንጸባርቅ፣ የማህበረሰብና የግለሰቦችን እውነተኛ የነፍስ ጩኸት፣ጸሎት፣ድል.፣ ደስታና ሀዘን የሚገልጥ፣ **ስለክርስቶስ ትንቢታዊ መልዕክት የያዘ**፣ለእግዚአብሔር የመታዘዝና ያለመታዘዝ ውጤት በግልጽ የሚናገር መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ ተምሳሌታዊ ንግግሮችንም በብዙ ይጠቀማል።በዚህ መጽሐፍ ያሉ መዝሙሮች በሙዚቃ መሣሪዎች ታጅበው የተዘመሩ መዝሙሮች ናቸው። በተለይም የእስራኤላውያንን ወይም የአይሁዳውያንን በግልም ይሁን በማህበረሰብ ከምርኮ በፊት፣በምርኮ ጊዜና ከምርኮ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ህብረት ይናገራል።

በመዝሙር መጽሐፍ የተጻፉ መዝሙሮች በጸኃፊው ዘመን የተጻፉና የተዘመሩ መዝሙሮች ብቻ ሳይሆን በኋላም በነበሩት ዘመናት የተዘመሩ መሆናቸውን መዘንጋት የለበትም። መዝሙር አሁንም እንደምንዘምረው ሆኖ እንደተቀመጠም ማወቅ አለብን።

ይህ የመዝሙር መጽሐፍ በአምስት ትንንሽ መጽሐፍት ይከፈላል (የአምስቱም) መደምደሚያቸው አንድ ዓይነት መልክ አለው፡፡

1. 1-41=41 መዝሙሮች (ለምሳሌ መዝጊያ ቁጥር 41፡13 "ከዘላለም እስከ ዘላለም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ። አሜን አሜን")።
2. መዝሙር 42-72=31 መዝሙሮች (ለምሳሌ መዝጊያ ቁጥር 72 ፡19-20፡- ቁ.19 የምስጋናው ስም ለዓለምና ለዘላለም ይባረክ ምስጋናውም ምድርን ሁሉ ይሙላ። ይሁን ይሁን)።
3. መዝሙር 73-89=17 መዝሙሮች (ለምሳሌ መዝጊያ ቁጥር 89፡52 "እግዚአብሔር ለዘላለም ይባረክ ይሁን ይሁን")
4. መዝሙር 90-106=17 መዝሙሮች ናቸው መዝ (106)፡48 መደምደሚያ ነው።
5. መዝሙር 107-150=44 መዝሙሮች ናቸው (መዝሙር 150 እንዳለ እንደ መዝጊያ ይቆጠራል)።

በተጨማሪም መዝሙሮቹ የተለያዩ ዓይነት መዝሙሮችና በብዛት በሙዚቃ የተሰሩ ናቸው። ለምሳሌ የጥበብ፣ የምስጋና፣የተለያዩ ጸሎቶች፣የአምልኮ፣የመሢህ፣የጽዮን፣የመርገም፣የንጉስ፣የቤተ መቅደስ እና ወዘተ ናቸው። በጥቅሉ እንጂ አንዳንዶቹ ተደራራቢ መሆናቸው ይታወቃል። እነዚህ በዚህ ጥናት ሰፋ ባለ መልኩ የምናያቸው ይሆናል። መዝሙሮቹን የበለጠ ለመረዳት የስንኞችን ማለትም አንደኛና ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ መስመር እንዴት እንደሚስማማ፣ እንደሚነጻጸር፣ እንደሚደራጅና ሌሎችንም ማየቱ ጥሩ ይሆናል። የመጽሐፍ ቅዱስ ቅኔዎች እንደ አማርኛ የመጨረሻ ፊደልና የሀሳብ አንድነት ሳይሆን የሚገጥመው የሁለቱና ከዚያም በላይ ስንኞች የሀሳብ አንድነትና ለአንዳንዶቹ የመጀመሪያ ፊደላት መግጠም ይሆናል። በርግጥ የአነባብ ውበት ለሁሉም ይጠቅማል።

በቤተክርስቲያናችን ይህን ጥናት ሲዘጋጅ አጠቃላይ ዓላማው ስለ መዝሙረ ዳዊት የተሻለ እውቀት በማግኘት በየቀኑ በምንኖረው ኑሮ ቅኔውን (**ግጥሙን**) ውዳሴውን ጸሎቱንና ሌሎቹንም የአጻጻፍ ዘይቤዎችን በመጠቀም ህይወታችንና አገልግሎታችንን እንድናጎለብት ነው። ለብዙ አማኞችም በረከት እንዲሆን ጸሎቷ ነው። መሪውም ይሁን ህብረቱ **ጥያቄዎችን ትኩረት እየሰጣችሁ እንብበት።**

የቤተ ክርስቲያንቷ ትምህርት ክፍል 214-703-0100 (ext 217)

**ዛሬ የመግቢያ ጥያቄዎች መወያያና ወደ ፊት ላለን የጥናት ጊዜያት የጸሎት ቀን ይሆናል**

1. ከመግቢያ ምን ተማራችሁ

2. ቤተክርስቲያን ይህን ጥናት ማዘጋጀት ለምን አስፈለጋት?
3. ቡድናችሁ ተጨማሪ ሰው የሚያስፈልገው ከሆነ ሰው ለመጨመር ተወያዩ (እያንዳንዳችን አንድ አንድ ሰው መምጣት ከቻልን ጥሩ ይሆናል)። በመካከላችሁ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በመምራት ማገልገል ልቡ ውስጥ ያለው ሰው በመሪያችሁ በኩል ትምህርት ክፍሉን ማነጋገር ትችላላችሁ።

## ጥናት አንድ

### የንባብ ክፍል
### መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 1
### የጥበብ (የትምህርት) መዝሙር
### ዓላማ፦ በየቀኑ እግዚአብሔርን በመፍራት የመመላለስ ህይወትን ማስተማር

**መግቢያ፦**

መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 1 የጥበብ መዝሙራት ተብለው ከሚጠሩት መዝሙሮች አንዱ ነው። ከመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ አንድ ሌላ ምዕራፍ 10:12፣15:19፣19:32፣34፣36፣37፣49፣ 50፣ 52፣ 53፣ 73፣ 78፣ 82፣ 90፣ 91፣ 92፣ 94፣ 111፣ 112፣ 119፣ 127፣ 128፣ እንዲሁም 139 የጥበብ መዝሙራት ናቸው። "የጥበብ መዝሙራት" የሚለው ስያሜ ሊሰጣቸው የቻለብት ምክንያት እነዚህ መዝሙራት እግዚአብሔርን በመፍራት እንድንኖር እና በየዕለቱ የጽድቅን ኑሮ እንድንፈልግ የሚያስምተሩ ስለሆኑ ነው።

በመዝ 111 ፡10 ላይ እንዲሁም በምሳ 1፡7 ላይ እንደምናነበው፣ "የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው"። የጥበብ መዝሙራትም አይነተኛ አላማቸው ይህንን እውነት ማስጨበጥ ነው። ጠቢብ ሰው እግዚአብሔርን በመፍራት ይመላለሳል። መዝሙረኛው በእነዚህ መዝሙራት ውስጥ እግዚአብሔርን የሚፈራ እና በጽድቅ የሚኖር ሰው እንዴት ያለ ሰው እንደሆነ፣ እንዲህ ያለውን ሰው ደግሞ እግዚአብሔር ከክፉ እንዴት እንደሚጠብቀው እና እንደሚባርከው ይዘረዝራል። በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔርን ያለመፍራት አደጋ ምን እንደሆነ ያሳስባል። እግዚአብሔርን ባለመፍራት እና በኃጢአት የሚመላለሰው ደግሞ ሕይወቱ በችግር እና በመከራ የተሞላ፣ እንዲሁም በጊዜው ከእግዚአብሔር ቅጣቱን እንደሚቀበል ያስተምራል። እግዚአብሔር ጻድቃንን ስለሚባርክ እና ስለሚያከብራቸው እግዚአብሔርን በመፍራት እና በመታመን መኖር መልካም ነው። በሌላ በኩል ግን ኃጢአተኞች ለጊዜው የተሳካላቸው እና መንገዳቸው የቀና ቢመስልም መጨረሻቸው ግን ጥፋት ነው። ስለዚህም ዘማሪው ምንም የተሳካላቸው ቢመስል "በክፉዎች ላይ አትቅና፣ ዓመፃን በሚያደርጉ ላይ አትቅና፣ እንደ ሣር ፈጥነው ይደርቃሉና፣ እንደ ለመለመ ቅጠል ይረግፋሉና" ሲል ይመክራል (መዝ 36:1)። በሌላ በኩል ጻድቃን የወደቁ እና የተጣሉ ቢመስሉም እንኳ እግዚአብሔር ግን ያስባቸዋል፣ ከክፉም ያስጥላቸዋል። "የጻድቃን መድኃኒታቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፤ በመከራቸውም ጊዜ መጠጊያቸው እርሱ ነው። እግዚአብሔር ይረዳቸዋል፣ ያድናቸዋልም፣ ከኃጢአተኞችም እጅ ያወጣቸዋል፣ ያድናቸውማል፣ በእርሱ ታምነዋልና" (መዝ 36፡39-40)።

የጥበብ መዝሙራት ጻድቃንን እግዚአብሔር እንደሚባርክ፣ ኃጥንን ደግሞ እንደሚቀጣ ያስተምራል ስንል ግን አሳባዊ (ideal) እንዲሁም አጠቃላይ (general) የሆነ እውነትን የሚያስተምር እንጂ በቀን ተቀን የሕይወት ምዕራፍ ውስጥ የሚከሰት እውነት እንዳልሆነ ልናስተውል ይገባል። ለምሳሌ እግዚአብሔር ኃጣንን ይቀጣል ስንል ኃጣን ሁሉ ሁልጊዜ አይሳካላቸውም ማለት አይደለም። እንዲያውም ኃጢአተኛ ከፍ ከፍ ብሎ ሊታይ የሚችልበትም ጊዜ እንዳለ መዝሙረኛው ራሱ ይመሰክራል (መዝ. 36፣35)። በሌላ በኩል እንዲሁ ጻድቅን እግዚአብሔር የሚባርክ መሆኑ እውነት ቢሆንም፣ ጻድቅ አይጎዳም፣ አያዝንም ወይንም መከራ አያይም ማለት አይደለም። ስለ ጽድቅ ብለው ብዙ የተንገላቱ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳሉ እናውቃለን። አሳባዊ እና ጠቅለል ባለ መልኩ ግን እግዚአብሔር ጻድቃንን ይባርካል ኃጣንን ደግሞ ይቀጣል - ወይም በየዕለት ተዕለት ኑሮአቸው ወይንም በዘመን ፍጻሜ! ፍጻሜው ምንም ይሁን ምን ግን የጽድቅን ኑሮ መኖር ማስተዋል እና ጥበብ ነው በኃጢአት መመላለስ እና እግዚአብሔርን ወደ ጎን ማድረግ ሞኝነት እና ፍጻሜው ጥፋት ነው።

መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ አንድም የጥበብ መዝሙር እንደመሆኑ የጻድቃን እና የኃጢአተኞችን አካሄድ ያወዳድራል እንዲሁም የጻድቃንን በረከት እና የኃጢአተኞችን ጥፋት ያስረግጣል። ለግል ንባብ እና ለጥናት እንዲያመች፣ መዝ አንድን እንደሚከተለው ልንከፍለው እንችላለን።

I. **የጻድቅ ሰው አካሄድ** (1፡1-2)
II. **የጻድቅ ሰው መልካም ዕጣ ፈንታ** (1፡3)
III. **የኃጣን አካሄድ** (1፡4)

IV. **የኃጣን ክፉ ዕጣ ፈንታ** (1:4-5)
V. **የእግዚአብሔር ፍርድ በምስጉን እና በኃጢአተኛ መካከል** (1:6)

**ሀ. የጻድቅ ሰው አካሄድ** (1:1-2)

በመጀመሪያው ሁለት ቁጥሮች ውስጥ፣ ዘማሪው ጻድቅ ሰው እንዴት ያለ ሰው እንደሆነ ይነግረናል። በቁጥር አንድ ላይ ጻድቅ ሰው የማያደርገውን ሲነግረን በቁጥር ሁለት ላይ ደግሞ ጻድቅ የሚያደርጋቸውን ነገሮች ይነግረናል። በመጀመሪያ ጻድቅ ሰው ከኃጢአተኞች ጋር አይተባበርም (ቁ. 1)። ይህንን እውነት ዘማሪው በሦስት ሀረጎች (phrases) ይገልጻል። ጻድቅ በክፉዎች ምክር የማይሄድ፣ በኃጢአተኞች መንገድ የማይቆም፣ እንዲሁም በዋዘኞች ወንበር የማይቀመጥ ነው። ሦስቱም ሀረጎች በአጭሩ እንዲያስተላልፉ የተፈለገው መልዕክት ጻድቅ ሰው ከኃጢአተኞች ጋር እንደማይተባበር ነው። ሆኖም ግን ዘማሪው የተጠቀማቸው ሥዕላዊ ሀረጎች አንባቢው ጉዳዩን በሚገባ እንዲያስተውለው የሚያደርግ ነው። ጻድቅ ሰው በኃጢአተኞች ወይንም በክፉዎች ወይንም በፌዘኞች ምክር አለመሄድ ብቻ ሳይሆን፣ በመንገዳቸው አይቆምም ወይንም አይቀመጥም። ዘማሪው ጻድቅ በኃጢአት እንደማይተባበር ለማሳየት የተጠቀማቸው ቃላት ጻድቅ ከኃጢአት ጋር ላለመተባበር የሚወስደውን ጠንካራ እርምጃ ያስገነዝባል። ጻድቅ በኃጣን ምክር አለመሄድ ብቻ ሳይሆን አብሮአቸው አይቆምም። ጻድቅ አለመቆም ብቻ ሳይሆን አብሮአቸው መቀመጥ እንደሌለበት ያስተምራል። አብሮአቸው መተባበርም የለበትም። ይህ ጠቢብ ሰው ከኃጢአተኛ ጋር በኃጢአት እንደማይተባበር ለመግለጽ ዘማሪው የተጠቀመው የአገላለጽ ዘዴ እንጂ በእውነት ጻድቅ ሰው ኃጢአተኛ ሰውን በመንገድ ሲያገኘው አብሮት አይሄድም ወይንም ክፉ ከሚያደርጉ ሰዎች ጋር በሥራ ጉዳይ ቢገናኙ አብረው ተቀምጠው አይወያዩም ማለት እንዳይደለ ሊስተዋል ይገባል።

ታዲያ ጻድቅ ሰው ምንድን ነው የሚያደርገው የሚል ጥያቄ ቢነሳ፣ ዘማሪው በቁጥር ሁለት ላይ መልስ ይሰጣል። ጻድቅ ሲሄድ፣ በመንገድ ሲቆም ወይንም ሲቀመጥ የሚያደርገው ከኃጢአተኛ ጋር መተባበር ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ መሰኘት እና ሕጉን ማሰላሰል እንዲሁም እንደ ሕጉ መሰረት መኖር ነው (ቁ. 2)።

እንዲህ ያለውን ሰው ዘማሪው "ምስጉን" ነው ይለዋል (ቁ. 1)። ምስጉን የሚለው ቃል በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች ላይ "የተባረከ"፣ "የታደለ"፣ "ደስተኛ" ተብሎ የተተረጎመ ሲሆን ዋናው ሊያስጨብጥ የፈለገው ቁም ነገር ግን እንዲህ ያለው ሰው በእግዚአብሔር የተባረከ ሰው መሆኑን ነው። ይህ ሲባል የግድ እንዲህ ያለው ሰው በምድራዊ ሃብት የተባረከ ነው ወይንም ሁልጊዜ እንደተደሰተ እና ፈገግ እንዳለ ይኖራል ማለት አይደለም። የምድር ሃብት ባይኖረው፣ አሳዛኝ ገጠመኞችም በሕይወቱ ቢያልፉም እንኳ፣ እንዲህ ያለው ሰው በእግዚአብሔር ልቡ አርፎ እና ረክቶ፣ ሕጉ በማወቁ እና በሕጉ መሰረት በመኖሩ ደስተኛ ሆኖ ይኖራል … በእግዚአብሔር የተባረከ ነውና። ተስፋው እግዚአብሔር ነው።

**ለ. የጻድቅ ሰው ዕጣ ፈንታ** (1:3)

በቁጥር ሦስት ላይ እግዚአብሔን በመፍራት እና ሕጉን በመከተል የሚኖር ጻድቅ እድል ፈንታው ምን እንደሆነ ይገልጻል። በወንዙ ዳር ስላለ የአየር ጸባይ በተለዋወጠ ቁጥር እንደማይለዋወጥ ግን ሁልጊዜ እየለመለመ እንደሚገኝ ዛፍ ይለመልማል፣ የሚሰራውን ሁሉ መከናወን እግዚአብሔር ይሰጠዋል። ይህን ሥዕላዊ አገላለጽ በሚገባ መረዳት አስፈላጊ ነው። ዘማሪው የዛፉን ምሳሌ ሲሰጥ ዛፉ የሚለመልመው ወቅቶች ስለማይፈራረቁበት አይደለም … ነገር ግን ውርጭ፣ ድርቅ ሆነ ሌላ አይነት ከባድ የአየር ጸባይ ቢመጣ "በውኃ ፈሳሾች ዳር" ተተክሎአልና ቅጠሎቹ አይረግፉም ወይንም ዛፉ አይደርቅም … ሁሌ እንደለመለመ ነው። ጻድቅ ሰውም እንደዚሁ ነው - ችግር፣ ስደት፣ መከራ እና ረሃብ … በሰው የሚደርሰው ሁሉ ሊደርስበት ይችላል … ሆኖም ግን በዚህ ሁሉ አሸንፎ እና ለምልሞ መኖር ይችላል። የጳውሎስን ምስክርነት በፊል 4:11-13 ያለውን እና የ ዮሴፍን የሕይወት ታሪክ ያስተውሉ። ጻድቅ እንደመሆኑ እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር የነበረ በመሆኑ መከናወንን ቢሰጠውም፣ ግን ፈታኝ በሆኑ የተለያዩ ፈተናዎች ማለፍን እናውቃለን። ሆኖም በእነዚህ ሁሉ አልፎ ግን በእግዚአብሔር ጉልበት እያሸነፈ ኖሯል። ዘማሪው በዚህ ክፍል ውስጥም

የሚያሳስበን ምስጉን እና እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እንደዚህ ይለመልማል ነው።

**ሐ. የኃጢአተኞች አካሄድ** (1:4)

እንደ ምስጉኑ ሰው፣ ዘማሪው ኃጣኑ ሰው የሚሰራውን እና የማይሰራውን ነገር እየዘረዘረ አይነግረንም ግን ባጭሩ “ክፉዎች እንዲህ አይደሉም” ይለናል። በሌላ አባባል ክፉዎች ምስጉኑ ሰው በሚሄደው አካሄድ አይሄዱም እንዲሁም እንደ ምስጉኑ ሰው አይባረኩም ማለት ነው። ስለዚህ የክፉዎች አካሄድ ምን ይመስላል ብንል፣ በክፉዎች ምክር የሚሄድ፣ በኃጢአተኞች መንገድ የሚቆም፣ በዋዘኞች ወንበር የሚቀመጥ … ባጭሩ ራሱን በክፋት እና በኃጢአት የሞላ ደግሞም ከኃጢአተኞች ጋር የሚተባበር ነው ማለት ነው። አካሄዱ የምስጉኑ ሰው ተቃራኒ እንደመሆኑ ዕጣ ፈንታውም እንዲሁ ይሆናል ማለት ነው። ቀጥሎ ባለው ክፍል ዕጣ ፈንታው እንዴት እንደሚሆን ይዘረዝራል።

**መ. የኃጢአተኞች ዕጣ ፈንታ** (1:4–5)

እግዚአብሔርን የሚፈራው ሰው በሚያልፍበት ሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ እየተባረከ እና እየለመለመ ሲሄድ፣ ኃጢአተኞች ግን ይጠፋሉ። ዘማሪው ይህንን እንደገና ሥዕላዊ በሆነ መንገድ ያሳያል። ገበሬ ሰብሉን ከሰበሰበ በኋላ ሰንዴውን ከገለባው የሚለይበትን መንገድ እንደ ምሳሌ ይጠቀማል። ገበሬው ሰብሉን በመንሽ ወደ ሰማይ በሚበትንበት ጊዜ ነፋስ ገለባውን እንደሚወስደው፣ የኃጢአተኛም ሕይወት እንዲሁ ይሆናል። ለጊዜው ያለ ይመስላል፣ ኋላ ግን በእግዚአብሔር ቀን እና ጊዜ እንደገለባው ይጠፋል።

በቁጥር 5 ላይ እንደሚነግረን፣ የእግዚአብሔር ፍርድ በሚመጣበት ጊዜ ክፉዎች መቆም አይችሉም ወይንም ከጻድቃን ጋር ተመሳስለው እና ተቀላቅለው መኖር አይችሉም። በበልጉ ወቅት ገለባው ከስንዴው ጋር ተመሳስሎ እንደማይቀመጥ እንዲሁ እግዚአብሔር ሲፈርድ ኃጢአተኞች የእግዚአብሔርን ፍርድ አይቋቋሙም ወይንም ከጻድቃን ጋር ተመሳስለው መቆም እና ማምለጥ አይችሉም - ይጠፋሉ። ኃጢአተኞች ይጠፋሉ ሲባል ከመኖር ወደ አለመኖር ይሄዳሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን በኑሮአቸው ደስታ አይኖርም ለወደፊት ደግሞ ተስፋ አይኖራቸውም ማለት ነው። ስለ ወደ ፊት ሲታሰብ ኃጢአተኛ ሊታሰብለት የሚቸለው ጥፋት ብቻ ነው። ኃጢአተኛ ይጠፋል ማለት ነው፡

**ሠ. የእግዚአብሔር ፍርድ በምስጉን እና በኃጣን መካከል** (1:6)

በቁጥር ስድስት እግዚአብሔር ለምን የጻድቁን ሕይወት ባርኮ ኃጢአተኛውን እንደሚቀጣ ያስተምራል። ለምን እግዚአብሔር ጻድቃንን ይባርካል ብንል መልሱ “እግዚአብሔር የጻድቃንን መንገድ ያውቃልና” ነው ይለናል ዘማሪው። እግዚአብሔር የሁሉንም አካሄድ ያያል እንዲሁም ያውቃል። እንደ እውቀቱ መሰረት ጻድቁን ይባርካል፤ “የክፉዎች መንገድ ግን ትጠፋለች።” ለጻድቁ መባረክ እና ለኃጢአተኛው መቀጣት መለያ ምክንያቱ የእግዚአብሔር እውቀት ፍርድ ፍትሐዊ ነው። ጻጽቅ ጻድቅ መሆኑን ሰው ላያውቅ ይችላል፤ እንዲሁም ኃጢአተኛ በሰው ፊት ጻድቅ መስሎ ሊታይ ይችላል። የበረከት እና የፍርድ መለኪያው የሰው እውቀት ቢሆን ኖሮ ፍትህ ይዛባ ነበር - ነገር ግን መለኪያው እና መለያው የእግዚአብሔር እውቀት መሆኑ ሁሉም የሚገባውን እንዲያገኝ ያደርጋል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

**ማስተወሻ** (**ካላለቀ የሁለት ቀን ጥናት ማድረግ ትችላላችሁ**)

1. ከመግቢያ ስለ ጥበብ መዝሙራት ምን ተረዳችሁ?
2. በመግቢያ ሀሳብ መሰረት በጥብብ መዝሙራት አንድ ሰው ጠቢብ የሚያሰኘው ምንድን ነው?
3. መዝ 1:1 መሰረት ጻድቅ በክፉዎች ምክር አይሄድም፣ በኃጢአተኞች መንገድ አይቆምም ወይንም በዋዘኞች ወንበር አይቀመጥም። በዚህ መሰረት እግዚአብሔርን የመፍራት ጉዳይ የመሄድ የመቆም እና የመቀመጥ ጉዳይ ነው? ካልሆነ ምን ማለት ነው “ያልሄደ … ያልቆመ … ያልተቀመጠ?”
4. እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል እንደገናም በቀን እና በሌሊት ያስበዋል። ሰው በእግዚአብሔር ሕግ ደስ የመሰኘቱ እና በቀን እና በሌሊት የእግዚአብሔርን ሕግ ማሰቡ የሚታወቀው በምንድን

ነው? ውጤቱስ ምንድን ነው?

5. የጻድቃን በረከት በውሃ ዳር ተተክሎ እንደሚለመልም ዛፍ እንደሚሆን ዘማሪው አሳይቷል። በዚህ መሰረት ግን ጻድቅ አይቸገርም፣ አያጣም ኑሮው ከአልጋ ወደ አልጋ ይሆናል ማለት ነው? ካልሆነ ምን ማለት ነው?
6. በሌላ በኩል ኃጢአተኛ እንደሚጠፉ ዘማሪው ሲያመለክት የኃጢአተኛ ሕይወት ሁልጊዜ በሃዘን እና በጥፋት የተሞላ ነው ማለት ነው? ካልሆን ምን ማለት ነው?
7. በቁጥር 6 መሰረት እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ቀጥቶ ጻድቁን እንዲባርክ የሚያደርገው ምንድን ነው? ይህስ የእግዚአብሔር ውሳኔ ፍትህ የተሞላበት እንደሆነ እንዴት ያሳየናል?
8. ይህ ትምህርት ከአዲስ ኪዳን ትምህርት ጋር ምን ይገናኛል? አናብራራ?
9. ዛሬ ባየነው ምዕራፍ መሰረት እግዚአብሔርን በመፍራት የሚኖር ሰው የማያደርጋቸው እና የሚያደርጋቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

**መደምደሚያ**

እንግዲህ ባጭሩ መዝ. ዳዊት 1 ከጥበብ መዝሙሮች መካከል የሚመደብ ሲሆን፣ ይህ ምዕራፍ ሰው በጽድቅ መንገድ እንዲሄድ ያነሳሳል። በመጀመሪያ በጽድቅ መንገድ የሚሄደው ሰው እንዴት ያለ እንደሆነ እና በሕይወቱ አካሄና አረማመዱ እንዴት ያለ እንደሆነ ይዘረዝራል። እንዲህ ያለው ሰው እንዴት ሕይወቱ የተባረከ እንደሚሆን ቀጥሎ ያስረዳል። ልክ በዚያው አይነት ክፉ ሰው  ፍጻሜው ደግሞ ጥፋት እንደሚሆን ያስገነዝባል። በመጨረሻም እግዚአብሔር የጻድቁንም ሆነ የኃጢአተኛውን መንገድ ስለሚያውቅ፣ ለሁሉም እንደ ሥራው እንደሚከፍል ያሳስባል። ስለዚህ እግዚአብሔርን በመፍራት እንደጻድቅ መኖር መናገርና እና መኖር ያዋጣል።

ይህንን ትምህርት አዲስ ኪዳንም አጥብቆ ያስተምራል። የማቴዎስ ወንጌል 16፥27 "የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና፤ ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል"። 1ኛ ጴጥ 1፥17 "ለሰው ፊትም ሳያደላ በእያንዳንዱ ላይ እንደ ሥራው የሚፈርደውን አባት ብላችሁ ብትጠሩ በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ። ራእይ 20፥13 "ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ፥ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፥ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ"። በተጨማሪም ራዕይ 22፥12 "እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ" ይላል። በመጨረሻ ጌታ ለሁሉም እንደሥራው ይከፍላል። እኛም አማኞች ይህንን አውቀን በየቀኑ ጥበብ በተሞላ ህይወት መመላለስ አለብን።

## ጥናት ሁለት

**የንባብ ክፍል**
***መዝሙረ ዳዊት 127***
**የጥበብ (የትምህርት) መዝሙር**

***ዓላማ፡-*** *ይህን መዝሙር በማጥናት የእግዚአብሔር ጥበብ በዚህ ጊዜያዊ ምድር ላይ በየቀኑ ለምገጥሙን ነገሮች እንደሚገባ መልስ መስጠት የምንችልበት የህይወታችን መሪህ እንዲሆን ማስተማር።*

***መግቢያ፡-***

*መዝሙረ ዳዊት 127 የጥበብ መዝሙራት ተብለው ከሚመደቡት አንዱ ነው። ባለፈው ጥናታችን እንደተመለከትነው የጥበብ መዝሙራት ሰው እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲኖር የሚያነሳሱ መዝሙራት ናቸው። መዝ. 127ም ከዚሁ የተለይ አላማ የለውም። ዘማሪው እግዚአብሔርን ማዕከል ያላደረገ ሕይወት እና ጥረት ከንቱ ልፋት መሆኑን በመጀመሪያ በማስጨበጥ እግዚአብሔርን አለማስቀደም እና አለመፍራት ሞኝነት መሆኑን በተዘዋዋሪ ያስገነዝባል። በሌላ በኩል ግን እግዚአብሔር የባረከው ሰው እና ቤተሰብ እንዴት ያለ እንደሆነ ያሳይ እና በተዘዋዋሪ እግዚአብሔር የባረከው እና እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው መሆን እንዴት መልካም እንደሆነ ያስገነዝባል።*

***መዝ. ዳዊት 127ን በአጭሩ በሁለት ከፍሎ ማጥናት ይቻላል።***

I. ***ያለ እግዚአብሔር የሰው ጥረት እና ሕይወት ከንቱነት*** (127፥1-2)
II. ***እግዚአብሔር የባረከው ሰው እና ቤት*** (127፥3-5)

### *ሀ.* ***ያለ እግዚአብሔር የሰው ጥረት እና ሕይወት ከንቱነት*** (127፥ 1-2)

*በዚህ ክፍል ውስጥ ዘማሪው ሰው በሕይወት ዘመን ውስጥ ራሱን ለማሻሻል ከሚጥርባቸው ነገሮች ጥቂቶቹን ለናሙና ያህል ይጠቅስና እነዚህ ሁሉ ጥረቶች ያለ እግዚአብሔር ዋጋ ቢስ መሆናቸውን ያሳስባል። ቤት መገንባት፣ ከተማን መጠበቅ እንዲሁም ኑሮን ለማሻሻል ቀን እና ሌሊት መድከም በኑሮ ውስጥ ያለ እና የተለመደ እንዲሁም ተገቢ ነገር ነው። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር ዘማሪው እነዚህ ነገሮች ሁሉ ከንቱ እና አላስፈላጊ ናቸው አያለ አይደለም ያለው። እግዚአብሔር ከሌለበት እነዚህ ጥረቶች ሁሉ ከንቱ ናቸው ነው መልዕክቱ። ያለ እግዚአብሔር የሕይወት ጥረቶች በሙሉ ከንቱ ድካም መሆናቸውን ለማሳሰብ በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ብቻ ሦስት ጊዜ "**ከንቱ**" የሚለውን ቃል መደጋገሙን ያስተውሉ።*

*መዝ 127፡1 መሰረት* ***"እግዚአብሔር ቤትን ካልሰራ፣ ሠራ****ተኞች በከንቱ ይደክማሉ።" በብሉይ ኪዳን ቤት መገንባት የመኖሪያ ቤት መስራትን ሊያመለክት ይችላል ወይንም ደግሞ ቤተሰብ መመስረትን ሊያሳይ ይችላል። በዚህ ክፍል ሁለቱንም ትርጉም ሊይዝ ይችላል። ሰው እግዚአብሔርን ሳይፈራ እና እሱን ሳያስቀድም የመኖሪያ ቤትም ሆን ቤተሰብን ቢመሰርት ከንቱ ነው። እግዚአብሔርን በመፍራት በተገኘ ጥረት ሰው ቤትን ቢሰራ፣ ወይንም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆን ቤተሰብን ሲመሰርት ብቻ ነው ከንቱ ያልሆነ ድካም የሚባለው። ስለዚህ ቤትን ወይንም ቤተሰብን የሚመሰርት በመጀመሪያ በህይወቱና በኑሮው ሁሉ እግዚአብሔርን ሊያስቀድም ይገባል - ያለዚያ ድካሙ ከንቱ ነው።*

*በዚሁ ቁጥር ላይ እንደገና* ***"እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ፣ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል።"*** *አሁን ባለንበት ዘመን የአገር ደኅንነት አንገብጋቢ ጉዳይ እንደሆነ እና መንግስታት የአገራቸውን ሰላም እና ደኅንነት ለመጠበቅ ብዙ የገንዘብ እና የሰው ጉልበት እንደሚያስወጡ ሁሉ በብሉይ ኪዳን ዘመን ውስጥም እንዲሁ ነበር። በበሉይ ኪዳን መንግስታት ከተማቸውን በወታደር ማስጠበቅ ብቻ ሳይሆን የከተሞቻቸውን ዙሪያ በግንብ ያጥሩ ነበር። ዘማሪው ግን እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ የወታደር መንጋጋት እና ከተማን ማሳጠር ከንቱ ነው ይላል። ስለዚህ ጠቢብ እና አስተዋይ የሆነ ሰው ከተማን ለማስጠበቅ በወታደሩ ብዛት እና በአጥሩ ርዝመት እና ጥንካሬ አይመካም ነገር ግን ከተማን በእርግጥ ለሚጠብቅ ለእግዚአብሔር በቅድሚያ አደራ ሰጥቶ እና እሱን ፈርቶ ወታደሮቹን ያሰማራል። እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ነጥብ*

እግዚአብሔር ከሌለበት የሰው ጥበቃ ከንቱ ነው፣ ስለዚህ ጠባቂ በመጀመሪያ እግዚአብሔርን ሊያስቀድም እና ሊፈራ … ሥራውንም በመጀመሪያ ለእግዚአብሔር አደራ ሊሰጥ ይገባዋል።

በቁጥር ሁለት ላይ ቤትን መስራት እና ከተማን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ከሌለበት በአጠቃላይ የሰው ድካም ሁሉ ከንቱ መሆኑን ያስገነዝባል። በዚህ ክፍል ላይ ዘማሪው ሊለው የፈለገውን እውነት በሚገባ ለመረዳት አዲሱ መደበኛ ትርጉምን ማወዳደሩ ይጠቅማል። "የዕለት ምግብ ለማግኘት በመጣር፣ ማልዳችሁ መነሳታችሁ፣ አምሽታችሁም መተኛታችሁ ከንቱ ነው፤ እርሱ ለሚወዳቸው እንቅልፍን ያድላልና" (አዲሱ መደበኛ ትርጉም መዝ 127፡2) ። በሰው ሕይወት ውስጥ በማለዳ ለስራ መነሳት፣ ሲመሽም ሲሰሩ መገኘት የታታሪነት ምልክት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር የሌለበት ልፋትና እና ጥረት እንዲሁ ከንቱ ነው - ምክንያቱም ቀን ከሌት የለፋለት "ኩርማን እንጀራ"፣ ወይንም ሃብት አያረካም። ስለዚህ እውነተኛ እና እግዚአብሔርን የሚፈራ ታታሪ ሰው በሕይወቱ እግዚአብሔርን የሚያስቀድም፣ ለጌታው ጊዜ ያለው እንዲሆን ዘማሪው በተዘዋዋሪ ያሳስባል።

ባጭሩ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ዘማሪው እያሳሰበ ያለው መስራት እና መጣር ከንቱ መሆኑን ሳይሆን እግዚአብሔርን ማዕከል ሳያደርግ እና እሱን ሳያስቀድም የሚደረግ ጥረት ሁሉ ከንቱ መሆኑን ነው። መልእክቱ ቤት መስራት ከንቱ ነው ሳይሆን ቤት የሚሰራ እግዚአብሔርን በመፍራት እና በማስቀደም ይስራ፣ ከተማንም የሚጠብቅ እንዲሁ ከእግዚአብሔር ጋር ይጠብቅ፣ ሕይወቱንም ለማሻሻል የሚጥረው ታታሪ እግዚአብሔርን በማሰብ እና በመፍራት ይጣር። እንዲህ ያለው ጥረት ከንቱ አይደለምና!

**ለ. እግዚአብሔር የባረከው ሰው እና ቤት** (127 ፡ 3-5)

በዚህ ክፍል እንደ መዝ. ዳዊት ምዕራፍ አንድ ጠቢብ እና እግዚአብሔር የሚፈራ ጻድቅ ሰው እንዴት እንደሚኖር እና እንደሚመላለስ አይዘረዝርም፤ ሆኖም ግን እንዲያለውን ሰው እግዚአብሔር ከሚባርክበት መንገዶች አንዱ ልጆች እና ቤተሰብ በመስጠት እንደሆነ ያሳያል። ሆኖም ግን ይህንን ከሚገባ በላይ ለጥጠነው ቤተሰብ መመስረት ገና እድሉን ያላገኘ ወይንም ልጆች የሌለው ሁሉ ጻድቅ አይደለም ማለት እንዳልሆነ ልናስተውል ይገባል - ባለፈው ጥናታችን እንዳየነው የጥበብ መዝሙራት አሳባዊ እና አጠቃላይ የሆነ እውነትን የሚያንጸባርቁ ትምህርቶች እንደሆኑ አንዘንጋ።

በቁጥር ሦስት ላይ እንደምንረዳው ልጆችን ማግኘት የእግዚአብሔር በረከት ነው። ከላይ እንዳየነው እግዚአብሔር ቤተሰብን ካልመሰረተ እና ካልሰጠ የሰው ድካም ከንቱ ነው። እግዚአብሔር ለሰው ቤትን ሲሰራ ግን በረከት ነው። አንደኛው የቤተሰብ በረከት እግዚአብሔርን የሚፈሩ ልጆችን ከእግዚአብሔር ማግኘት ነው። ልጆች የሁለት ተቃራኒ ጾታዎች ግንኙነት ውጤት ብቻ አይደሉም - የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው።

በቁጥር አራት  እና አምስት ላይ ዘማሪው እግዚአብሔር የባረከው ሰው በልጆቹ እንዴት ይበልጥ እንደሚባረክ ያሳያል። ይህንን ለማስጨበጥ የጦር እቃዎችን ምሳሌ ይጠቀማል። ለጦር የሚወጣ ሰው ጠላትን የሚያጠቃበትን ጦር እንዲሁም ፍላጻዎቹን የሚይዝበትን ኮረጆ ይይዛል። እግዚአብሔር የባረከው ቤተሰብ ብዙ ፍላጻዎችን በኮረጆው እንደሞላ ሰው ነው (አዲሱ መደበኛ ትርጉምን ያነጻጽሩ)። እንዲህ ያለው ሰው ወዳጁ ጠላት ሆኖ ቢነሳበት አይፈራም - ልጆቹ ይጠብቁታል እና በፍርድም ጊዜ ልጆቹ ይሟገቱለታልና። ይህንን ስንል ከላይ በቁ. ፩ ላይ ያነሳነውን አሳብ አንዘንጋ። እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ምንም ያህል ጠባቂዎች ቢሰማሩ ከተማ ደኅንነት አይኖራትም፣ እግዚአብሔር የባረከው ሰው ግን ምንም ጠላቶች ቢኖሩት እንኳ እግዚአብሔር በሚጠብቁት ልጆች ባርኮታል እና ደኅንነት አለው።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በዛሬው የመግቢያ ሀሳብ መሰረት መዝ 127 የጥበብ መዝሙር ነው የሚያሰኘው ምንድ ነው? ከመዝ. ምዕራፍ 1 ጋርስ በምን ይመሳሰላል?

2. መዝ 17፡1 መሰረት ሰው እንዴት ነው ከእግዚአብሔር ጋር ቤትን ሊሰራም ሆነ ከተማን ሊጠብቅ የሚችለው? እንወያይ።

3. በቁ.1 መሰረት ቤትን የሚሰራውም ሆነ ከተማን የሚጠብቅ እግዚአብሔር ከሆነ፣ የሰው ድርሻ ምንድ ነው?

4. የሰው ትጋትና ልፋቱ ከንቱ ሆነ  የሚባለው እንዴት ነው? (መልሱን ግልጽ ለማድረግ በምሳሌ አስደግፉ።)

5. በቁ 2 መሰረት ያለ እግዚአብሔር ወይም ብቻውን የሚታጋና ከ እግዚአብሔር ጋር ከሚተጋ ሰው መካካል ያለው ልዩነት ምንድ ነው?  (መልሱን ግልጽ ለማድረግ በምሳሌ አስደግፉ።)

6. በቁ 1 ላይ ያለ እግዚአብሔር የተመሰረተ ቤተሰብ ከንቱ መሆኑን ይናገራል። ከቁ. 3-5 ባለው መሰረት እግዚአብሔር የሰራው ቤት እንዴት ያለ ነው?
    - ልጆችም ይሁን ሌላ ምድራዊ በረከት የሌለበት ቤት ሁሉ ያልተባረከ ቤት ነው ማለት ይቻላል? እንዴት?

7. መዝ 127  በማር 8፡36 ካለው ሀሳብ ጋር በምን ይመሳሰላል?

8. በዛሬው ጥናት ጌታን ስለ መፍራትና በኑሮአችን እርሱን ስለ ማስቀደም ምን ተማርክ? ትጋትም ሆነ ሩጫችን ከንቱ እንዳይሆን ምን ማድረግ አለብን? በዚህ ጉዳይ እንድትጸልዩ እናሳስባለን።

**መደምደሚያ፡-**

ምዕራፉን በአጭሩ ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው፣ እግዚአብሔር የሌለበት ድካም ሁሉ ከንቱ ነው፣ ስለዚህ አስተዋይ በጥረቱ እና በልፋቱ ሁሉ እግዚአብሔር በዚህ ነገር ውስጥ አለ ወይ ብሎ ሊጠይቅ እና ራሱን ሊያይ ይገባል። እግዚአብሔር ያለበት ቤት እና ጥረት ግን በበረከት የተሞላ ነው። እንዲህ ላለው ሰው እና ቤት እግዚአብሔር ደኅንነት እና በረከትን ይሰጣልና። መክብብ መጽሐፍ ደጋግሞ ሁሉም ያለ ጌታ ከንቱ እንደሆነ ይናገራል። በአዲስ ኪዳን የማርቆስ ወንጌል 8፡36-37 እንደሚከተለው ይላል  “36 ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? 37 ሰውስ ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?”

## ጥናት ሶስት

**የንባብ ክፍል መዝሙር ምዕራፍ 116**
**የምስጋና መዝሙር**
**ዓላማ፡- እግዚአብሔር ያደረጋውን ሁሉ በማሰብ ህዝቡ እግዚአብሔርን ማመስገን እንዳለበት እንደገና ማሳወቅ**

***መግቢያ፡-***

መዝሙር ዳዊት 116 የምስጋና መዝሙር ተብለው ከተመደቡት መዝሙራት አንዱ ነው። የምስጋና መዝሙራት ሁለት አይነት ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ እንደ መዝ. 74፣ መዝ 104 ያሉት መዝሙሮች **የግል የምስጋና** መዝሙር ሲባሉ፣ እንደ መዝ 18 እና 21 ያሉት ደግሞ **የጉባኤ ወይንም የሕብረት** የምስጋና መዝሙር ይባላሉ። የግል የምስጋና መዝሙር የሚባሉት መዝሙሮች፣ እግዚአብሔር በዘማሪው ሕይወት ውስጥ የሰራውን መልካም ነገር እያወሳ እግዚአብሔርን የሚባርክባቸው መዝሙሮች ሲሆኑ፣ የጉባኤ ወይንም የሕብረት መዝሙር የሚባሉት ደግሞ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያረገውን የሚተርኩ እና እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ መዝሙራት ናቸው። የምስጋና መዝሙራትን ምንም የግል እና የጉባኤ እያልን ብንከፋፍላቸውም፣ መሰረተ-መልዕክታቸው ግን ተመሳሳይ ነው። እነዚህ መዝሙራት ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን በማመስገን እና በማወደስ ይጀምራሉ ወይንም አድማጩ /አንባቢው እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን ጥሪ በማቅረብ ይጀምራሉ። ለምሳሌ “አሕዛብ ሁላችሁ እግዚአብሔርን አመስግኑት …” (117፡1)፣ “ሃሌሉያ። የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሆይ አመስግኑት፣ የእግዚአብሔርንም ስም አመስግኑ” (113፡1)፣ “እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ፣ ምስጋናውም ዘወትር በአፌ ነው” (33፡ 1)። በመቀጠልም፣ ዘማሪው ወይንም የእግዚአብሔር ሕዝብ ያለፈበትን ከባድ እና አስጨናቂ ጊዜ በመተረክ እግዚአብሔር ከዚያ ሁኔታ ውስጥ እንዴት እንዳወጣው/እንዳወጣቸው ያሰላስላል። በመጨረሻም የእግዚአብሔርን መልካምነት እና የሰራውን በመንተራስ እንደገና እግዚአብሔርን በማወደስ እና በማመስገን ይጨርሳል። እነዚህ መዝሙራት አንዳንድ ጊዜ ይሄንን ቅደም ተከተል ባይከተሉም ግን እነዚህን ነገሮች ያካትታሉ።

መዝ 116 የግል የምስጋና መዝሙር ከሚባሉት አንዱ ሲሆን ዘማሪው እግዚአብሔርን በማወደስ ጀምሮ እግዚአብሔር በግል ሕይወቱ ያደረገውን እያወሳ ለእግዚአብሔር ምስጋናን ለመሰዋት ስዕለት በመሳል ይደመድማል። በኃይለ ስላሴ ትርጉም ይህ ምዕራፍ በሁለት ተከፍሎ ብናየውም (ከቁ 1-9 እና እና 10-19) አዲሱ መደበኛ ትርጉም እና ሌሎችም የእግሊዝኛ ትርጉሞች ይህ ምዕራፍ አንድ ወጥ እንደሆነ እናስተውላለን። ሙሉውን አሳብ ለመጨበጥ እንዲያመቸን የአዲሱ መደበኛ ትርጉም ባስቀመጠው መሰረት ከቁ. 1-19 ያለውን እንደ አንድ ምዕራፍ አድርገን እንመለከታለን። ለዛሬው ጥናት እንዲያመቸን ምዕራፉን በሚከተለው መንገድ ከፍለን ልናጠናው እንችላለን።

I. ***ዘማሪው ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር እና ምስጋና*** (1-2)
II. ***ዘማሪው ያለፈበት አስጨናቂ ሁኔታ*** (3-4)
III. ***ዘማሪውን ከነበረበት ሁኔታ ያስጣለው የእግዚአብሔር ምህረት እና መልካምነት*** (5-11)
IV. ***እግዚአብሔርን ለማመስገን የዘማሪው ስለት እና ውሳኔ*** (12-19)

### *ሀ. ዘማሪው ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር እና ምስጋና* (1-2)

ብሉይ ኪዳን በመጀመሪያ በተጻፈበት ቋንቋ (በዕብራይስጥ) ምዕራፉ የሚጀምረው፣ “ወደድኩት እግዚአብሔርን” በማለት ነው። ቀጥሎ ግን እግዚአብሔርን እንዲወድ ያደረገውን ምክኒያት ይጠቅሳል - “እግዚአብሔር የልመናዬን ድምፅ ሰምቶአልና።” በዚህ ቁጥር ውስጥ ዘማሪው ወደ እግዚአብሔር እንዲጮህ እና እንዲጣራ ያደረገውን ነገር ባይጠቅስም፣ ግን ካለፈበት ችግር የተነሳ ወደ እግዚአብሔር ይጮህ እንደነበረ ግልጽ ነው። ዘማሪው እግዚአብሔርን እንዲወድ እና እንዲባርክ ያደረገው እግዚአብሔር ጩኸቱን መስማቱ ነው።

ሆኖም ግን ዘማሪው እግዚአብሔር ከዚህ በፊት ጩኸቱን መስማቱ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር የሰውን ልመና ሁልጊዜ የሚሰማ መሆኑ ዘማሪውን እንዲያመሰግን ብቻ ሳይሆን ለእድሜ ዘመን የሚሆን ውሳኔ እንዲወስን አድርጎአል - “ጆሮውን ወደ እኔ አዘንብሎአልና፣ በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ወደ እርሱ እጣራለሁ።”

## ለ. ዘማሪው ያለፈበት አስጨናቂ ሁኔታ (3-4)

በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ዘማሪው የገባበትን አስጨናቂ ሁኔታ በዝርዝር አይገልጽም ሆንም ግን የጭንቀቱን ክብደት ግን ሥዕላዊ በሆነ አገላለጽ ያስረዳል። "የሞት ጣር ያዘኝ፣ የሲኦልም ሕማም አገኘኝ" ሲል የግድ ዘማሪው ለሞት የሚያደርስ ሕመም ወይንም አደጋ አጋጥሞት ለሞት እያጣጣረ ነበር ማለት አይደለም ነገር ግን የነበረበት አስጨናቂ ሁኔታ ከባድ እንደነበረ የሚገልጽበት መንገድ ነው። እንዲያውም ቀጥሎ "ጭንቀት እና መከራን አገኘሁ" በማለት እንደ ሞት ጣር እንድ እንደ ሲኦል ሕማም የከበደው ነገር ያለፈበት ጭንቀት እና መከራ እንደሆነ ያሳስባል።

ዘማሪው በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ ነው ወደ እግዚአብሔር የጮኸው እና እግዚአብሔር የሰማው። በዚህ ጊዜ "የእግዚአብሔርን ስም ጠራሁ" ይላል ዘማሪው። "አቤቱ ነፍሴን አድናት!" በማለት የጮኸው ጩኸት በከንቱ አልቀረም። ከላይ እንዳነበብነው እግዚአብሔር ጩኸቱን ሰምቷል።

## ሐ. ዘማሪውን ከነበረበት ሁኔታ ያስጣለው የእግዚአብሔር ምህረት እና መልካምነት (5-11)

ከቁ.5-11 ባለው ዘማሪው ዘማሪውን ከነበረበት ከባድ እና አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ያስጣለውን የእግዚአብሔርን ባህርይ ይዘረዝራል። በነዚህ ጥቂት ቁጥሮች ውስጥ ብቻ በቀላሉ ልንጠቅሳቸው የምንችላቸውን አምስት የእግዚአብሔር ባህርያት ይጠቅሳል። እግዚአብሔር መሓሪ ነው (ቁ. 5) ፣ እግዚአብሔር ጻድቅ ነው (ቁ. 5)፣ አምላካችን ይቅር ባይ ነው (ቁ.5)፣ እግዚአብሔር ጠባቂ ነው (ቁ. 6)፣ እንዲሁም እግዚአብሔር አዳኝ ነው (ቁ. 6 እና 8)። እግዚአብሔር ዘማሪው እንደ ሞት ከሚያስጨንቅ ሁኔታ ውስጥ እንዲወጣ ያደረገው ባጋጣሚ ሳይሆን ባሕርዩም ግድ ስለሚለው ነው። ዘማሪው እንደዚያ ባለ ሁኔታ ያለፈው በራሱ ጥፋት እንኳ ቢሆን ኖሮ፣ እግዚአብሔር መሓሪና ይቅር ባይ ስለሆነ ያድነዋል። ዘማሪው በሌሎች ተንኮልና እና ግፍ በከፋ ሁኔታ ያለፈ ቢሆንም አምላካችን ጻድቅ ፈራጅ ነው፣ ገሮችን ከክፉ የሚጠብቅ እንዲሁም አዳኝ ስለሆነ አስጥሎታል። ስለዚህም በምንም አይነት ምክኒያት ቢሆን ሰው በከባድ ሁኔታ ሲያልፍ ወደ እግዚአብሔር መጮህ መልካም ነው ... እግዚአብሔር በባህርዩ መልካም ስለሆነ!

በአማርኛ ትርጉም በቁ.6 እና 11 ላይ ያሉት ነገሮች ትንሽ ግራ የሚያጋቡ እና ዘማሪው እያስረዳ ካለው ሁኔታ ጋር የማይሄድ ነገር የሚዘምር ይመስላል። በኃይለ ሥላሴ ትርጉም በቁ. 6 ላይ "እግዚአብሔር ሕጻናትን ይጠብቃል" የሚለው አሳብ እግዚአብሔር የዋህ የሆኑትን ወይንም ገሮችን (simplehearted) እንደሚጠብቅ (ከክፉ እንደሚጋርዳቸው) የሚያስረዳ ነው። ዘማሪው ሊል የፈለገው እግዚአብሔር ሊያድነው ያስቻለው አንደኛው ምክኒያት እሱ ገር ሆኖ ሳለ በገጠመው መከራ ገሮችን የሚጠብቀው እግዚአብሔር ስለጠበቀው እንደሆነ ነው።

በቁ. 11 ላይ እንዲሁ በኃይለ ሥላሴ ትርጉም ላይ "እኔም ከድንጋጤዬ የተነሳ ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው አልሁ" ወይንም በአዲሱ መደበኛ ትርጉም "ግራ በተጋባሁ ጊዜ፣ 'ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው' አልሁ"የሚለው ሰው ሁሉ የማይታመን (unreliable) ነው የሚለውን አሳብ ለመግለጽ የተጠቀሰ ነው። ዘማሪው ከላይ የእግዚአብሔርን መልካም ባሕርይ እና አዳኝነት በመዘርዘር እግዚአብሔር ሰው ሊታመንበት የሚገባ እና ወደ እርሱ መጮህ መልካም መሆኑን አስረድቷል - እግዚአብሔር ታማኝ ነው። በዚያው ልክ በሰው መታመን ከንቱ ነው - ሰው ሁሉ ሊታመኑት ወይንም ሊደገፉበት የሚበቃ አይደለምና። ዘማሪውም በነበረበት ከባድ ሁኔታ ውስጥ የተማረው እውነት ሰው ሁሉ (ንጉስ ሆነ ተራ ሰው) ሊታመኑበት የሚገባ እንዳልሆነ ነው።

## መ. እግዚአብሔርን ለማመስገን የዘማሪው ስለት እና ውሳኔ (12-19)

በቁ. 12 ላይ "ስላደረገልኝ ሁሉ ለእግዚአብሔር ምን እመልሳለሁ?" የሚለው ጥያቄ ዘማሪው ከላይ ለዘረዘረው የእግዚአብሔር መልካምነት እና ከታች ለጠቀሰው የግል ውሳኔው ጥሩ መሸጋገሪያ ነው። ከላይ እንዳየነው እግዚአብሔር መልካም ነው! እሱ ለቅዱሳኑ ታማኝ እና አዳኝ ነው። ዘማሪውም ይህንን የእግዚአብሔር መልካምነት በራሱ ሕይወት ተለማምዶታል። ይህ የእግዚአብሔር መልካምነት በዘማሪው ሕይወት የሚያመጣው ለውጥ ምንድን ነው? ዘማሪውስ ለዚህ የሚሰጠው ምላሽ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ዘማሪው ከታች የሚዘረዝረው ውሳኔው ነው።

ከቁ.12-19 ባለው ዘማሪው እግዚአብሔር ስላደረገለት የሚመልሰውን በተለያየ አባባል ይዘረዝራል -

“የእግዚአብሔርን ስም እጠራለሁ” (ቁ. 13)፣ “በሕዝቡ ሁሉ ፊት ስእለቴን ለእግዚአብሔር እፈጽማለሁ” (ቁ. 14)፣ “ለአንተ የምስጋና መስዋዕትን እሰዋለሁ፣ የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ” (ቁ.17)፣ “በሕዝቡ ሁሉ ፊት ስእለቴን እፈጽማለሁ” (ቁ. 18)። በአጭሩ እግዚአብሔር ስላዳነውና በባሕርዩ መልካም ስለሆነ እንዲወስን ያደረገው ነገር በአደባባይ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን እና ለእግዚአብሔር የገባውን ቃል (ስእለት) በአደባባይ እንዲፈጽመው ነው።

በቁ. 15 እና 16 ላይ ከእግዚአብሔር መልካምነት እና ከዋለለት ውለታ ባሻገር እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን እና እንዲያገለግል የሚያደርገው ነገር እንዳለ ያስረዳል። እነዚህ ቁጥሮች በመሰረቱ በአውደ ምንባቡ ውስጥ የሚሰጡትን ትርጉም ለመርዳት የሚያስቸግሩ እና የሚያጨቃጭቁ ቢሆኑም በርጋታ ለሚያጠና ሰው ግን አሳቡን ለመረዳት አያስቸግርም። በቁ. 15 ላይ “የቅዱሳኑ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው” በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ “የከበረ” ለሚለው ቃል ትክክለኛው እና ተመጣጣኙ ቃል “ውድ” (precious) የሚለው ነው። ለአማኝ ሞት ከእግዚአብሔር ጋር የሚሆንበት መንገድ በመሆኑ ሞት መልካም ቢሆንም፣ የቅዱስ ሰው ሞት ግን በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ውድ ነው - ጻድቅ ወደ አምላኩ ሲሰበሰብ በምድር የሚሰጠው አገልግሎት ይቀራል እና። ቅዱስ ጳውሎስም ይህንን እውነት በፊል 1፡22-24 ባለው ሲያስረዳ “በሥጋ ከቆየሁ፣ ፍሬያማ ተግባር ይኖረኛል፣ ነገር ግን የትኛውን እንደምመርጥ አላውቅም። በእነዚህ በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ፣ ከክርስቶስም ጋር ልሆን እናፍቃለሁ፤ ይህ እጅግ የተሻለ ነውና። ነገር ግን በሥጋ መኖሬ እጅግ አስፈላጊ ነው”። መሞት ለጳውሎስ መልካም ነው ነገር ግን የእርሱ ሞት እጅግ ውድ ነው ለሚያገለግላቸው ያጎድልባቸዋልና። እንዲሁም ዘማሪው ይህንን በመረዳት፣ በሕይወት እስካለ የእግዚአብሔር ባሪያ እና አገልጋይ ነው ቁ. 16። በዚህ ጊዜ እንደ ባሪያነቱ እና አገልጋይነቱ እግዚአብሔርን ሊያመሰግን፣ ሊያገልግል እንዲሁም ለእግዚአብሔር የገባውን ስእለት ሁሉ ሊፈጽም ይገባል። የእርሱ አገልግሎት አስፈላጊ ነውና ከባድ ከነበረው እስራቱ እና ሰንሰለቱ አስጥሎታል … የቅዱሳን ሞት በእግዚአብሔር ፊት ውድ እንደሆነ ሁሉ የዘማሪውም ጥፋት ለእግዚአብሔር ውድ ስለሆነ አድኖታልና፣ማለትም እግዚአብሔር ዘማሪው እንዲጠፋ አይፈልግም ። ሆኖም ግን እግዚአብሔር ያዳነው ሊያገለግል እና ሊያመሰግን እንደመሆኑ ዘማሪው እየደጋገመ እግዚአብሔርን ሊጠራ እና ሊያመሰግን ቃል ይገባል።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በዛሬው የመግቢያ ሀሳብ መሰረት መዝ 116ን የምስጋና መዝሙር ያሰኘው ምንድ ነው?
2. መዝ 116፡1-2 መሰረት ዘማሪው እግዚአብሔርን የወደደበት ምክንያት ምንድ ነው?
3. መዝ 116፡3-4 ዘማሪው እያለፈበት ያለው ሁኔታ ምንድ ነው።
4. ከላይ በተጠቀሱት ቁጥሮች መሰረት ዘማሪው እያለፈበት ላለው የህይወት ተግዳሮት የሰጠው ምላሽ ምንድ ነው?
5. ከቁ.5-11 ባለው መሰረት የተዘረዘሩት የእግዚአብሔር ባሕርያት ምንድን ናቸው? እነዚህ ባሕርያት ዘማሪው እያለፈበት ላለው ችግር ምን ጠቀሜታ አለው?
6. በቁ. 6 ላይ እግዚአብሔር ሕጻናትን ይጠብቃል ሲል ምን ማለቱ ነው? ሕጻን ማለት ምን ማለት ነው? (ለተጨማሪ ማብራሪያ አዲሱን መደበኛ ትርጉም ይመልከቱ)። በዚህ ቁ. መሰረት ህጻን የሚለው ሀሳብ በእግዚአብሔር ፊት ገር እና የዋህ መሆንን የሚያመለክት ነው ትላለህ?
7. በቁ. 11 ላይ “ሰው ሁሉ ውሸተኛ ነው” ሲል ምን ማለቱ ነው? ወይስ እውነትን ለማስጨበጥ በቃለ አጋኖ እየተጠቀመ ነው?
8. ቁ. 2 እና ከቁ. 12-19 በማወዳደር እግዚአብሔር መልካም አምላክ በመሆኑ እና ለሚፈሩት የሚያድን የመሆኑ እውነት ዘማሪው ምን እርምጃ እንዲውስድ ነው ያደረገው? ክፍሉን በዝርዝር ተነጋገሩ።
9. በቁ. 15 ላይ የቅዱሳን ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው የሚለው ሀሳብ ምን ያመለክታል? ከፊል 1፡23 ጋር በማያያዝ ተነጋገሩ? (አንድ አገልጋይ በሞት ቢለይ ጥቅምና ጉዳቱ ምንድ ነው?)

10. ከዛሬው መዝሙር ምን ተማራችሁ?

***መደምደሚያ፡-***

በአጭሩ፣ የምስጋና መዝሙራት በመዝሙር 116 እንዳየነው በተለምዶ እግዚአብሔርን በማመስገን ወይንም በመወደስ ይጀምራሉ። ዘማሪው ወይንም የእግዚአብሔር ሕዝብ ያለፉበትን አስቸጋሪ ሁኔታዎች በመዘርዘር እግዚአብሔር ዘማሪውን ወይንም ሕዝቡን እንዴት እንደታደጋቸው ያወሳሉ። በመጨረሻም ለእግዚአብሔር ምስጋና በማቅረብ ይጨርሳሉ። በመዝ 116 እንደሰፈረው በዚህ ዘመንም የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ እግዚአብሔር የሚሰማ እና የሚያይ በመሆኑ በችግሩ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ሊጣራ ይገባል። ግን ደግሞ የእግዚአብሔር ሰው የሚፈልገውን ብቻ የሚጠይቅ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ውለታ እና መልካምነት እያነሳ የሚያመሰግንም ሊሆን ይገባል።

## ጥናት አራት

**የግል ጸሎት፡ የታመመ ሰው ጸሎት**

**የምንባብ ክፍል፡- መዝሙር 41**

**የጥናቱ ዓላማ፡-**

ለድሆች በማሰብ፥ በቅንነት በመኖርና በጸሎት እግዚአብሔር በችግራችን ጊዜ አብሮን እንደሚሆንና እንደሚረዳን ለማሳየት

**መግቢያ፡-**

ይህ መዝሙር በደህና ጊዜ ለድሆች የሚያስበውን ቅን የሆነ ሰው ችግር ሊገጥመው እንደሚችል፥ ነገር ግን በችግሩ ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሚሆን የሚያሳይ መዝሙር ነው። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ቢሆንም ሌሎች በጠላትነት በእርሱ ላይ እንደተነሱ እርሱ ግን ቅንነቱ ጠብቆ በጸሎት እንደተጋም ያሳያል። ይህም መልካም ማድረግ ብቻ ሳይሆን ጸሎትም እንደሚያስፈልግ በተግባር ያስረዳል። መዝ 103፡1-5 ከዚህ መዝሙር ጋር ተያያዥነት ያለው መዝሙር ነው።

1. **<u>መዝሙር 41፡1-3 መልዕክት፡</u> ዘማሪው ካለፈበት ህይወት የተማረው ትምህርት**

ቁ 1፡ እኛን እግዚአብሔር በክፉ ቀን እንዲያድነን ዛሬ ክፉ ለሆነባቸው(ለድኾች) ማሰብ፥ ማለትም እነሱን በሚቻለው ሁሉ መርዳት።

ቁ 2-3 እግዚአብሔር ለድሃ ለሚያስብ የሚያደርግለትን ይዘረዝራል። ቁ3 ላይ እንዳይታመም ያደርገዋል ወይም ወዲያው ይፈውሰዋል ሳይሆን ታሞ ሳለ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚንከባከበው ይናገራል።

2. **<u>መዝሙር 41፡4-13 ጸሎት፡</u> ዘማሪው ያለፈበት ህይወትና የጸለየው ጸሎት**

**ቁ 4** ዘማሪው በመጀመሪያ እግዚአብሔር ምህረት አድርጎ ነፍሱን እንዲፈውስው ይጸልያል። ባለፈው ጥናት ዘማሪው በደረሰበት የሃሰት ክስ፥ እግዚአብሔርን ስለንጽህናዬ እርዳኝ ብሎ እንደጸለየ አይተናል። አሁን ግን ስለምህረትህ ይለምናል። ጌታንም እንደበደለ ይናገራል። የጠየቀው ፈውስ ግን የነፍስ ፈውስ ነው። ይህም ከስጋ ፈውስ የነፍስ እንደሚበልጥ፥ ሰው ስጋው ታሞ ነፍሱ ከዳነ ይህ ትልቅ የእግዚአብሔር ምህረት እንደሆነ ያሳያል። ማረኝ ስላለ የያዘው በሽታ ከሃጢያቱ የተነሳ እንደመጣበት ሊያሳይ ይችላል። ነገር ግን በሽታ ሁሉ ከሃጢያት እንደማይመጣ ከዮሐንስ ወንጌል 9፡1-5 እና ከያዕቆብ 5፡15 እንማራለን።

**<u>3. መዝሙር 41፡5-9 ዘማሪው ጠላቶቹ ለህመሙ የሰጡትን ምላሽ ይዘረዝራል።</u>** ጠላቶቹ የሚላቸው ወዳጆች መስለው፥ ሊጠይቁት እየመጡ ግን ሞቱን የሚጠባበቁ፥ በእርግጥ ያላዘኑለት፥ የማይጸልዩለት፥ምን አልባት ቢሞት የሚሉ የእርሱን በረከትና ቦታ ለመያዝ የሚፈልጉ የቅርብ ስዎችን ሊወክል ይችላል።

**ቁ 9ኝ** በዮሐንስ ወንጌል 13፡18 ላይ ኢየሱስ ይናገረዋል “እንጀራዬን የሚበላ በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣብኝ ያለው ይፈጸም ዘንድ ነው”።። ይህም የሚያሳየን መዝሙሩ የታመመ ሰው ጸሎት ቢሆንም መልዕክቱ ግን በሌላም ችግር ላለም ሰው ይሆናል።

**<u>4. ቁ10 ላይ ጠላቶቹን ማሳፈር እንዲችል እግዚአብሔር ከበሽታው እንዲያስነሳው ሲጸልይ</u>** ቁ11 ላይ ደግሞ ጸሎቱ ተሰምቶ ጠላት ያሰበው ስላልሆነ ይህም እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን ፍቅር እንደሚገልጽ እንዳያበት ይናገራል። ነገር ግን እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር የምናውቀው ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሰራው ስራና አሁንም ከሚያደርግልን መልካም ነገር ተነስተን እንጂ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመፎካከር መሆን የለበትም። ፈውስ የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ ከስራችን የተነሳ እንደሆነ አድርገን የምናገንነው አይደለም።

ቁ.10 ላይ ሌላው የምናየው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ሰዎች የሚሉትና የሚያደርጉት ሁሉ ምናልባት ልክ ነው ማለት

አይቻልም። ዘማሪው ቢፈወስ ሌሎችን በመፈወስ የሚያስቀና ይመስላል። በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ጠላት ስለተገዛልን ሳይሆን ስማችን በሰማይ ስለተጻፈ፥ ልጆች ስለሆንን ደስ ሊለን እንደሚገባ ያስተምረናል። ከጌታ ጋር መሆን ይበልጣል።

<u>**5. ቁ12 ላይ ቅንነቴ የሚለው በቁ 1 ላይ እንደተናገረው ለድሆች ማሰቡን፥**</u> ለሌሎች ክፉ የማያስብ ሰው መሆኑ ነው። ጠላቶቹ ለእርሱ ክፉ ቢያስቡም እርሱ ግን ለሌሎች ክፉ አያስብም። ይህ ማለት ግን ሃጢያት የለበትም ማለት አይደለም፥ ቁ4 ላይ እንዳየነው ዘማሪው እግዚአብሔርን እንደበደለ ያምናል።

**6. ቁ13 ዘማሪው በህይወቱ ስለሆኑ ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናል።**

***የመወያያ ጥያቄዎች:-***

1) መዝ 41፡ 1-3 ድረስ ዘማሪው እርሱ ካለፈበት የተማረውና መዝሙሩን ለሚሰሙ የሚያስተምረውን ትምህርት በዝርዝር ተነጋገሩበት
2) ከዘማሪው ጸሎት ውስጥ በእርሱ የደረሰበት ችግር ምንድን ነው? (በተለይ ቁጥር 8)
3) መዝ 41፡4 መሰረት ዘማሪው በመጀመሪያ የሚጠይቀው ምንድን ነው?
4) መዝ 41፡ 5-9 ዘማሪው ጠላቶቼ የሚለው ምን የሚያደርጉ ሰዎችን ነው? እነዚህ ጠላቶቼ የሚላቸው ሰዎች በህመም ጊዜ ምን አደረጉ? ምንስ አሉ?
5) መዝ 41፡10 ላይ ለሁለተኛ ጊዜ ምህረት መጠየቁ ምን ያስተምራል?
6) በቁጥር 10 እና 11 ላይ ዘማሪው ፈውስን የፈለገው ለምን እንደሆነ ይናገራል? እግዚአብሔር እንደወደደው የሚያውቀው እንዴት ነው?
7) መዝ 41፡12 ላይ ቅንነቴ ብሎ የሚለው በዚህ መዝሙር ውስጥ ምኑን ነው?
8) በዚህ መዝሙር ተግሣጽን የተቀበለ ሰው ካለ ለህብረቱ ያካፍል? ለሌሎች ጠላት የሆንክበት ጊዜ አለ? የሌሎች ማጣት ለኛ በረከት ሊሆን ይችላል? ከዚህ መዝሙር የተማራችሁትን ማንኛውንም ነገር ጊዜ እንደፈቀደ ተነጋገሩ
9) በጸሎት ጊዜአችሁ እግዚአብሔር ከቅዱሳን ልብ ውስጥ ጠላትነትን እንዲያርቅ ጸልዩ። እንደታመሙ ለምናቃቸውም ሰዎች በመጀመሪያ ለነፍስ ፈውስ ከዚያም እግዚአብሔር እንደፈቃዱ ሥጋቸውን እንዲፈውሳቸው ጸልዩ።

***መደምደሚያ:-***

እድሉና አቅሙ ሲኖረን ለተቸገሩ የምናደርገው መልካም ነገር በእግዚአብሔር ፊት ይመዘገባል፥ ብድራትም አለው። "ለድሃ የሚራራ ለእግዚአብሔር ያበድራል፥ስላደረገውም ተግባር ዋጋ ይሰጠዋል" (ምሳሌ 19፡17)። ይህን በጸሎት መደገፍ ደግሞ አለብን። በቅንነትና በጸሎት መኖር በችግር ጊዜ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆኖ ከችግር እንዲጠብቀን ይረዳናል። ይህን ትምህርት ክርስቶስ በወንጌል በጥብቅ አስተምሯል "ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፥ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋው አይጠፋበትም" (ማቴ 10፡42)።

## ጥናት አምስት

### የግል ጸሎት፡ ክስ በሀሰት የቀረበበት ሰው ጸሎት

### የምንባብ ክፍል፡ መዝሙር 7

**የጥናቱ ዓላማ፡-** እግዚአብሔር የፍትህ አምላክ መሆኑን አውቀን ፍትህ ሲጓደል ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ እምነታችንን አድርገን በጸሎት የእርሱን ፊት እንድንፈልግ ለማበረታታት።

***መግቢያ፡-***

ይህ መዝሙር አንድ በሀሰት የተከሰሰውን ግለሰብ ጸሎት የያዘ የጸሎት መዝሙር ነው። የሀሰት ክስ ማለትም በደል አለብህ፥ ክፉ አድርገሃል ተብሎ በተከሰሰ ጊዜ በጸሎት የዘመረ መዝሙር ነው።

በህይወቱ በዚህ ወቅት በንጽህና የሚኖር ሰው ጠላቶች ሊኖሩት እንደሚችል፥ ነገር ግን የፍትህ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ፍትህ እንደሚያደርግ ዘማሪው በሙሉ እምነት ይናገራል። በንጽህና የኖረ ሰው በእግዚአብሔር ፊት በድፍረት መቅረብም እንደሚችል ያሳያል። ክፉ የሆኑትን ሰዎች ጌታ እንደሚታገሥና በጊዜው ግን እንደሚፈርድም በማሳየት ያስጠነቅቃል። በአጠቃላይ እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ መሆኑን የምናይበት መዝሙር ነው። ይህ መዝሙር ለህይወታችን ብዙ ይናገረናል።

***መዝሙር 7፡1-17***

1. ***መዝ 7፡1-2 ጸሎት፡*** የአድነኝ ጥያቄ፡

*ዘማሪው ጌታ ካላዳነው ሌላ መፍትሄ የለውም። የሚያሳድዱት ሰዎች ብዙ ናቸው። እነርሱ ሲያሳድዱት ወደ ጌታ ሸሽቶ ደብቀኝ ይላል። ጌታ ካላዳነው አሳዳጆቹ እንደሚያጠፉት ይናገራል። "እንደ አንበሳ ይዘነጣጥሉኛል" ማለቱ ችግሩ ምን ያህል አስፈሪና አስጊ እንደሆነ ያሳያል። "የሚያድን በሌለበት" ማለቱ ከእግዚአብሔር ሌላ ሊያድነው የሚችል እንደሌለ ማመኑን ያሳያል። "እግዚአብሔርን መሸሸጊያዬ" ማለቱ እርሱ ከተፈጥሮ ችግር ብቻ ሳይሆን ከሰው ጠላትም እንደሚያድን ያሳያል።*

2. ***መዝ 7፡3-5*** **የተከሰሰበትን ክስ ይክዳል**

የተከሰሰበትን ክስ አድርጎት ከሆነ በራሱ ላይ ፍርድ ይጠራል። (ወደታች በጠላቶቹ ላይ የሚጠራውን የእግዚአብሔርን ቁጣ ስናየው ፍትሃዊ ጸሎት እንደሆነ እናያለን።) ዘማሪው ምንም ዓይነት ጥፋት እንዳላጠፋ የምናውቀው ሦስት ዓይነት ጥፋቶችን አላደረኩም ስለሚል ነው። 1) "በደል በእጄ ከተገኘ"፡ ይህ ማንም ሳይበድለው ከመሬት ተነስቶ ማንንም እንዳልበደለ ያሳያል። 2) "በጎ ለዋለልኝ ክፉ መልሼ ከሆነ"፡ መልካም ያደረገለትን ሰው አልበደለም 3) "ጠላቴን በከንቱ"፡ ጠላቱ ሳይደርስበት አልደረሰበትም። ከእነዚህ የትኛውንም በደል በድሎ ከሆነ እግዚአብሔር ለጠላት እጅ አሳልፎ እንዲሰጠው ይጸልያል።

3. ***መዝ 7፡6-9 ጸሎት፡*** **የፍትህን አምላክ ፍርድ ይጠራል**

እርሱ በድሎ ከሆነ ጠላቶቹ እንዲያጠፉት እንደጸለየ፥ አሁን ደግሞ በበደሉት ጠላቶቹ ላይ ይጸልያል። የሚጸልየው ግን ጠላቶቹ እንዲሞቱ ሳይሆን ሥራቸው እንዲጠፋ ነው። እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ ስለሆነ የክፉዎችን ሥራ እንዲያጠፋና ጻድቁን እንዲያጸና ይጸልያል። እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ ስለሆነ የዘማሪውን ጸሎት ሰምቶ ሳይሆን የሚፈርደው፥ የሁሉን ልብና ኩላሊት መርምሮና ማን በደለኛ እንደሆነ አውቆ ነው።

"የህዝቦች ጉባኤ ይክበብህ" ሲል እግዚአብሔር ፈራጅነቱ እሱን በሚያምኑት ብቻ ሳይሆን በማያምኑትም፥ በአለም ህዝቦች ሁሉ እንደሆነ ያሳያል። ስለዚህም ለራሱ ብቻ ሳይሆን በአለም ሁሉ ለተከሰሱ ህዝቦች እግዚአብሔር እንዲፈርድ ይጸልያል። የፍትህ አምላክ ፍርድ እንዲሰጥ ይጠይቃል።

4. **መዝ 7፡10-13 በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት ይናገራል**

የዘማሪውም እምነት በእግዚአብሔር አዳኝነትና ጻድቅነት ላይ ነው። አዳኝ ስለሆነ ከአሳዳጆቹ ክፋት እንደሚያድነው ያሳያል። እንዲሁም ጻድቅ ስለሆነ በደለኛውን ሳያዳላ እንደስራው እንደሚከፍለው ያሳያል። የእግዚአብሔር አዳኝነትና ጽድቅ በግልጽ ይናገራል።

5. **መዝ 7፡14-16 ክፉ ሰዎችን ከፋታቸው ያጠፋቸዋል፡**

ስለዚህ ዘማሪው እግዚአብሔር በቁጣው እንዲነሳ ሲጸልይ፥ የእግዚአብሔር ጥበቃና ምህረት ከእነርሱ ተነስቶ፥ እግዚአብሔር ለስራቸው አሳልፎ እንዲሰጣቸው ነው። የእግዚአብሔርን ፍትህ ይጠይቃል። እግዚአብሔር ነው ለክፋታቸው አሳልፎ የሚሰጣቸው። እግዚአብሔር ማንንም ባልሰራው አይፈርድበትም።

6. **17 የፍትህ አምላክ፥ ልዑሉ እግዚአብሔር ይመስገን።** ዘማሪው እግዚአብሔር ጻድቅ እንደሆነ ይናገራል። የእግዚአብሔር ጽድቁ የፍትህ አምላክ መሆኑ ነው። (ሁሉን በእኩል ዓይን ያያል። አያዳላም)።

7. **የአዲስ ኪዳን ግንኙነት፡-**

ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል እንደሚከተለው ይላል “እንግዲያስ የነቢያት ገዳዮች ልጆች እንደሆናችሁ በራሳችሁ ላይ ትመሰክራላችሁ።32 እናንተ ደግሞ የአባቶቻችሁን መስፈሪያ ሙሉ። 33 እናንተ እባቦች፥ የእፉኝት ልጆች፥ ከገሃነም ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ?” (ማቴ 23፡31)። ሐዋርያ ጳውሎስም በሮሜ መልዕክት እንዲህ ይላል “እንደዚህም በሚያደርጉት ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እውነተኛ እንደ ሆነ እናውቃለን። አንተም እንደዚህ በሚያደርጉ የምትፈርድ ያንም የምታደርግ ሰው ሆይ፥ አንተ ከእግዚአብሔር ፍርድ የምታመልጥ ይመስልሃልን? ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቍጣ ቀን ቍጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ። ...11 እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላምና” (ሮሜ 2፥2-5 እና 11)።

**የመወያያ ጥያቄዎች፡-**

1) በዚህ መዝሙር በመግቢያው መሰረት ዘማሪው የደረሰበት ችግር ምንድን ነበር? እንዴትስ ነው ችግሩን የገለጠው?

2) ዘማሪው የተከሰሰበት ክስ እውነተኝነት አለው?

3) መዝ 7፡1-2 ላይ የዘማሪው ጸሎት ምንድን ነው? በዝርዝር ተነጋገሩ። እግዚአብሔር ከምን እንዲያድነው ነው የሚጠይቀው? በአዲሱ ትርጉም ይዘነጣጥሉኛል፥ ይቦጫጭቁኛል ሲል ዘማሪው እየፈራ ስላለው ችግር ምን ያስረዳል?

4) መዝ 7፡3-5 ለኪሱ የዘማሪው ምላሽ ምንድን ነው?

5) መዝ 7፡6-9 የዘማሪው ጸሎት ቁ.1-2 ከጸለየው ጸሎት ልዩነቱ ምንድን ነው? በተለይ ቁ9ኝን ተመልከቱ።

6) መዝ 7፡10-13 ዘማሪው በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነት ምን ይመስላል?

7) መዝ 7፡14-16 መሠረት ክፉዎች ቅጣታቸው እንዴት ይመጣል። ከፋታቸው የሚያጠፋቸው ከሆነ መጸለይ ምን ይጠቅማል?

8) መዝ 7፡17 ዘማሪው የሚያመሰግነው ስለምንድን ነው?

9) ይህ መዝሙር ከአዲስ ኪዳን ጋር ምን ግንኙነት አለው (ሮሜ 2፡2-5)?

10) ከዚህ መዝሙር ምን ተማርክ? በሀሰት ስንከሰስ ምን ማድረግ አለብን? ሌሎችንስ በሀሰት እንዳንከስ ተግሣጽን ወይንም ማስጠንቀቂያ ምን ያስተምራል?

**መደምደምያ፡-**

እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅና የፍትህ አምላክ እንደሆነ አውቀን ችግር ስደርስብን በእምነት እርሱን በመጠበቅ መጸለይ አለበን። እርሱ ታጋሽ ፈራጅ ነውና አልፈን በሌሎች ላይ ክፉ የምናደርግ ከሆነ ከክፋታችንም መመለስ አለብን።

# ጥናት ስድስት

## የግል ለቅሶ፡ ሞት አፋፍ ላይ ያለ ሰው ለቅሶ ወይም ስለ መሢህ መዝሙር
## የንባብ ክፍል፡-መዝሙር 22

**የጥናቱ ዓላማ፡-**

ተስፋ በሚያስቆርጥ ችግር ውስጥ ብንገባም እንኳ እግዚአብሔር ለሌሎችም ለእኛም ከዚህ በፊት ያደረገልንን በጎነት በማሰብ እምነታችንን ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ አድርገን ለዛሬ ችግራችን የእርሱን ፊት ያለማቋረጥ እንድንፈልግ ለማበረታታት።

***መግቢያ፡***

ይህ መዝሙር በሞት አፋፍ ላይ ያለ ሰው እግዚአብሔርን እንዴት እስከመጨረሻው ድረስ ታምኖ እንደ ቆየና እርሱም እንዴት እንዳዳነው ለመመስከር የተፃፈ መዝሙር ነው። በተጨማሪም ዘማሪው ያለማቋረጥ የሚጸልይ፥ እግዚአብሔር ለእርሱም ለሌሎቹም ያደረገውን የማይረሳ፥ በእርሱም ሁሌ የሚታመን መሆኑን ያሳያል። እግዚአብሔርም ያደረገለትን በጉባኤ እንደመሰከረና ከእርሱ ህይወት ተነስቶ ለሌሎች ትምህርት እንደሰጠ እናያለን። መዝ 4 እና መዝ 9 ብዙ የምስማሙት ነገር አለው። ደግሞም ዘማሪው ብዙ ጊዜ ጸልዩ እግዚአብሔር እንዳልመለሰለትና ዘማሪውም ሌላ አዳኝ እንዴሌለው አውቆ እስከመጨረሻው እግዚአሔርን ተሰፋ እንደሚያደርግ ማየት ይቻላል።

ይህ መዝሙር ኢየሱስ በመስቀል ላይ የደረሰበትን ስቃይ እርሱም የጸለየውን ጸሎት ያስታውሰናል። አንዳንዱን ክርስቶስ በመከራው ጊዜ ቃል በቃል ተጠቅሟል (ማቴ 27፡35፣39፣43)። ከዚህም የተነሳ ብዙዎች የነብዩ መዝመር ነው ይላሉ። በርግጥ መዝሙሩን በሙሉ ስናጠናው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለኢየሱስ የሚሆኑ አንዳንድ ጉዳዮች አሉት። ለምሳሌ በቁጥር 6 ላይ ዘማሪው ራሱን "እኔ ትል ነኝ ሰውም አይደለሁም" ይላል። ኢየሱስን በመስቀል ላይ ሆኖ ሳለ ሰዎች እንደናቁት እንዲሁ ይህን ዘማሪም ሰዎች ንቀውታል። በአዲስ ኪዳን ብዙ የተጠቀሰ መዝሙር ነው። ነገር ግን ኢየሱስ ራሱን ትል ነኝ፥ ሰው አይደለሁም አላለም።

1. ***<u>መዝ 22፡ 1-2 ለቅሶ፡ እስከመቼ?</u>*** ብሎ ይጠይቃል። ያለማቋረጥ የሚጸልይ ዘማሪ ነው። ችግሩ እስኪፈታ ድረስ ጌታን ይፈልጋል። ይህ ክፍል በማቴ 27፡46 በማር 15፡34

2. ***<u>መዝ 22፡3-5 የእግዚአብሔር በጎነት በታሪክ፡-</u>***

በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ለሌሎች እስራኤል ያደረገውን ይናገራል። "እግዚአብሔር በታሪክ ያደረገውን ሊደግም የሚችል አምላክ ነው" ይሉት ነበር። ቁ.1 እና ቁ.2 የሚቃረን ይመስላል ነገር ግን አይቃረንም። ዘማሪው የሚያለቅሰው በእግዚአብሔር ላይ እምነት ስላለው ነው። እግዚአብሔር ድሮ በአባቶቻቸው ዘመን ለሌሎች ያደረገውን መድገም የሚችል አምላክ መሆኑን ስለሚያውቅ ነው ላለበት መከራ የሚያለቅሰው። የሆነው ሁሉ ቢሆን እግዚአብሔር የታመኑትን ያድናል። ታላቅ ችግር ውስጥ ቢሆንም እግዚአብሔርን ያምናል።

3. ***<u>መዝ 22፡6-8 የሚቀበለው መከራ፡ የጸሎት ርዕስ</u>***

ዘማሪውን ሌሎች ልክ ክርስቶስን መስቀል ላይ ይሳለቁበት እንደነበረ መዝሙረኛውንም "የታመነው አምላኩ ያድነው" ይሉት ነበር። በማቴ 27፡39-40 "የሚያልፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ ይሰድቡት ነበርና፡ቤተ መቅደስን የምታፈርስ በሦስት ቀንም የምትሠራው፥ ራስህን አድን፤ የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ከመስቀል ውረድ አሉት" እያሉ ይሳለቁበት ነበር።

4. ***<u>መዝ 22፡9-10 በጌታ መታመን</u>***

ዘማሪው እግዚአብሔርን ከመወለዱ ጀምሮ የህይወቱ ባለቤት እንደሆነ ይመሰክራል፤ያረጋግጣል። በዚህ ሁሉ ታላቅ መከራ ጌታ የህይወቱ ጅማሬ እንደሆነ እምነቱን ይገልጻል።

5. **መዝ 22፡11 ጸሎት፡ አትዘግይ።**
በዚህ ቁጥር ዘማሪው በማንም ሰው እንዳልታመነ ይናገራል። አምላኩ እንዲረዳውም ይማጸናል። የእግዚአብሔርን ቅርበት መጠየቅ ብልህነት ነው።

6. **መዝ 22፡12-22 የሚቀበለው መከራ፡ የጸሎት ርዕስ**
በእነዚህ ቁጥሮች ዘማሪው የሞት አፋፍ ላይ እንዳለ ይናገራል። አንዳንድ የሚላቸው ነገሮች በኢየሱስ ህይወት የሆኑ ናቸው። ይህ ማለት ግን የዘማሪው ጸሎት ሁሉ ስለኢየሱስ የሚናገር ነው ማለት አይደለም። ለምሳሌ በቁ6 ላይ እኔ ትል ነኝ፥ ሰው አይደለሁም ይላል። ኢየሱስ ትል ነኝ አይልም። ደግሞም ከሰው ያነስኩ ነኝ ብሎ አያውቅም። ምሳሌያዊ ንግግርም መሆኑን ማወቅም አለብን። ኮርማዎች፣በሬዎች፣አንበሳ፣ ውሾችንና አውራሪስን ለጠላቶቹ ምሳሌ ይጠቀማል።

7. **መዝ 22፡19-21 ጸሎት**
መዝ 22፡12-18 ስለደረሰበት ተስፋ አስቆራጭ መከራ ተናግሮ አሁንም እግዚአብሔር እንዲያድነው መጸለዩ ዘማሪው በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት ያሳያል።

8. **መዝ 22፡22 የምስጋና ስለት ይገባል።**

9. **መዝ 23-31 ዘማሪው ስለቱን ፈጸመ**
እግዚአብሔር ጸሎቱ ስማለት (ቁ 24)። ስለዚህ ዘማሪው በጉባኤ ለማመስገን የገባውን ቃል ፈጸመ።
ማመስገን ብቻ አይደለም ማስተማርም ጀመረ (ቁ26~31)

**የመወያያ ጥያቄዎች፡**

1) መዝ 22፡1-2 ስለ ዘማሪው ለቅሶ ምን ማለት ይቻላል?

2) መዝ 22፡3-5 ዘማሪው ስለ እግዚአብሔር የሚናገረው ምንድን ነው? ይህ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት በቁ1እና2 ላይ ካለው ለቅሶው ጋር ሲተያይ የሚቃረን ይመስልሃል? እንዴት?
3) መዝ 22፡6—8 እና 12-18 መሠረት ዘማሪው የደረሰበት መከራ ምን ይመስላል?
4) መዝ 22፡9-10 ዘማሪው እግዚአብሔር ለማን ያደረገውን ይናገራል? አሁንም ለቅሶውንና እምነቱን ስታይ ሁለቱ የሚቃረኑ ይመስልሃል?
5) መዝ 22፡12-18 የዘማሪው ለቅሶ ከጌታ ኢየሱስ ጋር በማነጻጸር ተነጋገሩ (ማቴ 27፡45-46)። ይህ ማለት ግን የዘማሪው ለቅሶ ሁሉ ስለ ኢየሱስ ሊሆን ይችላል?
6) መዝ 22፡12-18 ዘማሪው ችግሩን እንዴት እንደገለጸው አይተህ በቁ19-21 ከዚህ ከችግሩ እግዚአብሔር እንዲያወጣው መጸለዩን ስታይ ስለ ዘማሪው እምነት ምን ማለት ትችላለህ?

7) መዝ 22፡22-25 ዘማሪው ስላቀረበው ስለትና ስለአፈፃፀሙ ስታይ ምን ትማራለህ? ጸሎቱስ ተሰምቶለታል?

8) መዝ 22፡26-31 በክፍሉ ዘማሪው የሚያስተምረው ምንድን ነው?

9) ከዚህ መዝሙር ምን ተማርክ?

**መደምደምያ፡-**

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ነገሮች ተስፋ አስቆራጭ ደረጃ እስኪደርሱ ድረስ ዝም ሊል ይችላል። የእግዚአብሔር ዝምታ ግን የእርሱ ክፋት ወይም ግድ አለመሰኘት ወይም አለመቻል አይደለም። ይህን የምናውቀው ከዚህ በፊት ለሌሎችም ለእኛም ያደረገውን በጎነት አይተን ነው። ስለዚህ በጎነቱንና ፍቅሩን አውቀን ባለንበት ፈታኝ መከራው ውስጥ እርሱን መታመን አለብን።

# ጥናት ሰባት

## የመርገም ጸሎት

## የምንባብ ክፍል፡ መዝሙር 69

**የጥናቱ ዓላማ፡-**

ስለጌታ ስንነቀፍ በጸሎት በመታገሥ የእርሱን መታደግ እየጠበቅን እንድንኖር ለማበረታታትና እኛ ደግሞ ሌሎችን እንዳንነቅፍ ለማስጠንቀቅ ነው።

**መግቢያ፡-**

ባለፉት አራት ጥናቶች የጸሎትና የለቅሶ ወይም የሰቆቃ መዝሙሮችን አጥንተናል። በዚህ ጥናት ደግሞ “የመርገም ጸሎት” መዝሙርን እናጠናለን። ይህ መዝሙር ለእግዚአብሔርና ለቤቱ የሚቀናውን ሰው ሌሎች በእግዚአብሔር ስም የተጠሩ እንዴት እንደጠሉት፥ እንደሰደቡት፥ እንዳሳፈሩትና እንዳዋረዱት ያስተምራል። እርሱንም ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም እንደዚሁ እንዳረጉና ለዚህም ክፋታቸው ዘማሪው ከእግዚአብሔር ፍርድን እንደሚጠይቅ የሚናገር መዝሙር ነው። አንዳንድ ሰዎች የዘማሪውን ጠላት ከሰይጣን ጋር ብቻ ያያይዙታል። “እኛ ጠላት የለንም፣ ጠላታችን ሰይጣን ብቻ ነው” ይላሉ። ይህ ግን ሙሉ በሙሉ እውነት አይደለም። ጌታ ኢየሱስ “ጠላትህን ውደድ” ሲል ሰይጣንን ውደድ ለማለት አይደለም። ማቴ 5፡44 እና ሮሜ 12፡20 በግልጽ የሚያምኑም የማያምኑም ሰዎች በክፋት በእኛ ላይ ሊነሱ ይችላሉ ይላል። ሰዎች **<u>በፈቃዳቸው</u>** የተለያዩ ልክ ያልሆኑ ነገሮችን ሲፈልጉ በውስጣቸው ጥላቻ እያደገ ይመጣል። ጥላቻውንም በተግባር መግለጥ ይጀምራሉ።

ይህ ተቃዋሚ ያደርጋቸዋል። ጥያቄው የሰው ጠላት አለን ወይስ የለንም ሳይሆን፥ በንጹህ ሰው ላይ የሚነሱ አማኞች በእግዚአብሔር ፊት ከፍተኛ በደል እያደረሱ እንዳለና፥ ይህም ትልቅ ፍርድ ሊያስከትል እንደሚችል የሚያሳይ መዝሙር ነው። በዚህ መዝሙር ያሉ ብዙ ጥቅሶ በአዲስ ኪዳን ስለ ኢየሱስ የተነገሩ እንደመሆናቸው የዘማሪው ጸሎት በመንፈስ ተመርቶ እንደሆነ ማየት እንችላለን።

1. **<u>መዝሙር 69፡ 1-4 የአድነኝ ጸሎት</u>**

ቁጥር 1 የመጀመርያ ጊዜ የአድነኝ ጸሎት

ቁጥር 1እና2 ዘማሪው የደረሰበትን ችግር በስዕላዊ መልክ ይገልጸዋል፡ መቆም እንዳልቻለ፥ችግሩ ሊያጠፋው እንዳለ ይናገራል። እነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የዘማሪው ችግር በውሃ ውስጥ መስጠም ይመስላል። ነገር ግን በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ዘማሪው ችግሩን እግዚአብሔር በአፋጣኝ እንዲሰማው ለማድረግ ብሎ የገለጸበት መንገድ እንጂ ችግሩ መስጠም አይደለም። እየሰጠመ ያለ ሰውን ማዳን ፋታ አይሰጥም። ይህ አገላለጽ እግዚአብሔር በችኮላ ጸሎቱን እንዲሰማው ለማድረግ ነው። ምክንያቱም ሊሰምጥ ያለውን ሰው ማዳን ጊዜ አይሰጥም። ቁ 17 ላይ ደግሞም “ፈጥነህ መልስልኝ” ይላል።

ቁጥር 3 ከዚህ መዝሙር በፊት የተጸለየ ግን ያልተመለሰ የአድነኝ ጸሎት ሲሆን ዘማሪው እስኪደክመው ድረስ ጸለየ። ቁጥር 4 ዘማሪው ከላይ በስዕላዊ መልክ የገለጸውን ችግሩን አሁን በግልፅ ይናገረዋል፡ የሚጠሉት ሰዎች እንደበዙና ጥላቻቸው በከንቱ እንጂ እርሱ ካደረገው ነገር የተነሳ እንዳልሆን ይናገራል። ጥላቻም ብቻ ሳይሆን ሊያጠፉትም ይፈልጋሉ። እስካሁን ድረስ ሰርቀሃል በማለት እያሳበቡ የወሰዱበት ብዙ ነገር አለ። ይህ በተለያዩ አማኞች ህይወት የሆነና እየሆነ ያለ ነገር ነው።

2. **<u>መዝሙር 69፡ 5-6 ምልጃ:</u>** ዘማሪውን የሚጠሉትና የሚከሱት ባልሆነ ነገር እንደሆነ ቢናገርም፥ በእግዚአብሔር ፊት ግን ነፃ እንዳይደለ ያምናል። ይህ መዝሙር ምናልባት ከመዝሙር 51 በኋላ የተዘመረ ይሆናል። የዘማሪው ሃጢያት ምን እንደሆነ ባይታወቅም፥ ለሃጢያቱ ግን ቅጣት ከእግዚአብሔር እንደተቀበለና፥ አሁን በሌሎች ሰዎች እየተጠላና እየተከሰሰ እንዳለ እናያለን።

ዘማሪውን ከሚያስጨንቀው ነገር አንዱ የሌሎች ቅዱሳን ልብ በእርሱ ምክንያት እንዳይዝል፥ ከጌታም እንዳያርቃቸው ነው።

3. **<u>*መዝሙር* 69፡ 7-12 *አንገት መድፋት*</u> (ከቁ5-6 *ጋር አስተያይ*)**

በእነዚህ ቁጥሮች ዘማሪው አሁን ባለበት ሁኔታ ለእግዚአብሔር እና ለቤቱ የሚቀና፥ የሚጸልይ፥ የሚያለቅስ እንደሆነና ከቤተሰቡም ጀምሮ ብዙዎች የሚያደርገውን ሁሉ ዋጋ እንደሌለው አድርገው እንደሚያጣጥሉበት ይናገራል።

4. **<u>*መዝሙር* 69፡ 13-18 *የሁለተኛ ጊዜ የአድነኝ ጸሎት*</u>**

ከቁ1-4 ያለውን ጸሎቱ ይደግማል። በቁ1 እና 2 የጠቀሰው "ውሃ" የሚጠሉት ሰዎች እንደሆኑ ይናገራል። ውሃ ምሳሌያዊ ንግግር ነው። ይህን ምሳሌያዊ ንግግር ነቢያትም ተጠቅመውታል (ኢሳ 43፡1)።

5. **<u>*መዝሙር* 69፡ 19-21 የጠላቶቹ ከፋት</u>**

ሌሎች ዘማሪውን ከማፅናናት ይልቅ እንደሰደቡት፥ እንዳሳፈሩትና እንዳዋረዱት ይናገራል። የሚያጽናና ወይም አይዞህ የሚል አልተገኘም።

6. **<u>*መዝሙር* 69፡ 22-28 የመርገም *ጸሎት*</u>**

ዘማሪው በጠላቶቹ ላይ እንዲሆን የሚጸልየው ፍትሃዊ ፍርድ ነው። እንዲሆንባቸው የሚጠይቀው ሁሉ እርሱና ሌሎች ላይ ባደረጉት መጠን ነው፥ በዋነኝነት ጥያቄው የበቀል ሳይሆን ለሌሎችም በማሰብ ደግመው ሌሎችን እንዳይበድሉ፥ የእግዚአብሔርን ቤት/ህዝብ እንዳያበላሹ ነው። የእግዚአብሔርን ፍትህ መጠየቅ ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር እርሱን በማይታዘዙት ላይ ከብዙ ትዕግስት በኋላ እጅግ ጨካኝ አምላክ ነው። ለህዝቡና ለቃል ኪዳኑ ጠንቃቃ አምላክ ነው።

7. ***መዝ* 69፡29 የመጨረሻ የአድነኝ ጸሎት**

8. **<u>*መዝሙር* 69፡ 30-32 የምስጋና ስለት</u>**

ዘማሪው ጌታ ጸሎቱን ሲመልስና ሲያድነው እንደሚያመሰግነው፥ የእሱም መዳን ደግሞ ለሌሎች መፅናናት እንደሚሆን ይናገራል።

9. **<u>*መዝሙር* 69፡ 33-36 ለሌሎች ተስፋ</u>**

ከምርኮ በኋላ የተጨመረ ነው። ምናልባት ዕዝራ ሊሆን ይችላል። መዝሙሩ ከዳዊት ህይወት አልፎ ለህዝቡ ሁሉ የሚሆን እንደሆነ ስላየ የጨመረው ይሆናል። በምርኮ ያለው ህዝብ ለበደሉት በደል ከጌታ ቅጣት ለሰባ አመት ተቀብለዋል። ለዘማሪው እንዳሰበ እግዚአብሔር ለምርኮውም ህዝብ እንደሚያስብ የሚናገር ክፍል ነው። መዝሙሮች ለየትኛውም ዘመን ይሰሩ ነበር።

**የአዲስ ኪዳን ግንኙነት**

ይህ መዝሙር ቃል በቃልና እያንዳንዱ ቁጥር ባይሆንም በክርስቶስ ህይወትና አገልግሎት ተፈጽሟል። ለማመሳከር ዮሐ 2፡ 17 ዮሐ 15፡25 ዮሐ 19፡28-30 ሮሜ 15፡3 መመልከት ይቻላል።

**የመወያያ ጥያቄዎች፡**

**(ይህ ጥናት ትኩረት የሚሻው ስለሆነ በዚህ ጥናት የወጡ ጥያቄዎች ከማብራሪያ ጋር ናቸው)። በተጨማሪም የሁለት ቀን ጥናት ማድረግ ትችላላችሁ።**

1. በመዝ 69፡1-2 ዘማሪው እራሱን እንዴት ነው የሚያቀርበው? የሰጠመበትስ ውሃ ምንድ ነው?
2. ቁ 14እና15ን ስናነብ ግን የሰጠመበት ውሃ ምን እንደሆነ ይናገራል? ታዲያ ችግሩ የሚጠሉት ሰዎች እንጂ ውሃ ውስጥ መስጠም ካልሆነ፥ ዘማሪው በቁ1እና2 ሊሰምጥ እንዳለ የተናገረው ለምንድን ነው?

3. በቁ 3 መሠረት እግዚአብሔር ጸሎቱን በችኮላ እንዲሰማው ለማድረግ መፈልጉ ከምን የተነሳ ነው?

4. በቁ 4 መሠረት ዘማሪው የደረሰበት ችግር ምንድን ነበር? በምንስ ምክንያት ነው?
5. በቁ 5 ላይ እራሱን በእግዚአብሔር ፊት ራሱን እንዴት ነው የሚያየው? ከቁ.4 ሀሳብ ጋር እንዴት ይያይዛል?(Hint: እግዚአብሔር የበደለን ስው መጥላት ሳይሆን መምከር፥ መገሠጽ እና ልንጸልይለት ነው የሚገባው)።

6. በቁ 26 ላይ እግዚአብሔር በእርሱና በሌሎች እግዚአብሔርን በበደሉ ላይ ያደረገውንና የሚጠሉት ሰዎች ያደረጉበትን አስተያይ። የሚጠሉት ሰዎች ጥፋት ምንድን ነው?

7. በቁ6 ላይ ዘማሪው ለሚጠሉት ሰዎች ያደረገው ምንድ ነው? ለምን?

8. ከቁ7-12 ዘማሪው የሚያደርገውን እና የሚጠሉት ሰዎች የሚያደርጉበትን እያስተያይተህ ተወያዩ። ከእነዚህ ቁጥሮች ስለ እነዚህ ሰዎች ማንነት ምን ትረዳለህ? ለዚህ ክፍል ብዙዎች የሚያምኑ እስራኤላውያን እንጂ የሌላ አገር ጠላቶች አይደሉም ይላሉ። ዘማሪው የሚያደርገውን መንፈሳዊ ነገር ሁሉ የሚነቅፉ ሰዎች ናቸው። በቁ 26 መሠረት ዘማሪው ለሃጢያቱ ከእግዚአብሔር በቂ ቅጣት ተቀብሎአል። እንደዘማሪው በጌታ ለሃጢያታቸው የተቀጡትን ሁሉ የሚንቁ፥ የሚከሱ፥ የሚሰድቡ ናቸው። እነዚህ የውስጥ ሰዎች ናቸው። በዚህ ነገር ተወያዩ። ይህ እውነት አሁንም አለ ብላችሁ ታምናላችሁ? እንዴት?

9. ዘማሪው ስለሚጠሉት ሰዎች ከቁ22-28 ድረስ የሚጸልየው ምንድን ነው? ለምንድን ነው እንደዚህ የከፋ (የመርገም) ጸሎት የሚጸልየው? ይህንን ጸሎት ከቁ6 ጋር እናስተያይ። ይህ መዝሙር የሚያምኑ ሰዎች እንዲህ ዓይነት ክፋት በሌላ አማኝ ላይ ሲሰሩ እጅግ ከባድ በደል መሆኑን ለማሳየት ነው። ለሌሎች መማለድ፥ ድካማቸውን ማገዝ ሲገባቸው ክስና ስድብ የሚያወርዱ ሊማለድላቸው አይገባቸው በማለት የበደላቸውን ክብደት ያሳያል። ከቁ6 ጋር ስናስተያየው ዘማሪው ለእግዚአብሔር ህዝብ ግድ የሚለው ነው። ስለዚህ የእነዚህ የነቃፊዎች እና የከሳሾች መኖር የእግዚአብሔር ህዝብ ሊያቆሽሽ ስለሚችል ነው በዋነኝነት የፍርድ ጸሎት የሚጸልይባቸው እንጂ ለገዛ እራሱ በቀል አይደለም።

- ከባድ ጸሎቶችን የምንጸልየው ለግላችን ጥቅም ነው ወይስ ለጌታ ቤት ቅናት ነው?

10. ዘማሪውንና ጌታ ኢየሱስን በማነጻጸር ከዚህ በታች ከየትኞቹ ጥቅሶች ጋር እንደሚዛመድ ተነጋገሩ። ጌታ ኢየሱስንና ዘማሪውን በማነፃፀር ተነጋገሩ።
ዮሐ 2፡17 ዮሐ 15፡25 ዮሐ 19፡28~30 ሮሜ 15፡3

11. ከዚህ መዝሙር ምን ተማርክ? አብዛኛውን ጊዜ ራሳችንን በዘማሪው ቦታ ብቻ ነው የምናስቀምጠው። ነገር ግን ይህ መዝሙር ለተግሳፃችንም ነውና የተፃፈው ራሳችንን በዘማሪው ጠላቶች ቦታም እያስቀመጥን ራሳችንን መመርመር አለብን። ቅዱሳንን ያለምክንያት እንጠላለን? እግዚአብሔር የቀጣውን ቅጣት እንጨምርበታለን? ተግሣጽን ተቀብለሃል? ራሳችንን ምናልባት እንዳንሳሳት በጌታ ፊት እናስቀምጣለን።

**መደምደሚያ፡-**

ስለ ጌታ ቀንተን ስንኖር ከማያምኑ ብቻ ሳይሆን አምነናል ከሚሉም ነቀፌታ ሊመጣብን ይችላል። ነቀፌታው ጌታን ማገልገል እስኪያስጠላን ሊያደርስን ቢችልም እንኳ በጌታ ፊት በማልቀስ ጌታን ታግሠን ብንጠብቅ ጌታ ይመጣልናል። ለሁሉም ተገቢውን ፍርድም ይሰጣል። እኛም ሌሎችን ቅዱሳን ያለ ምክንያት እየጠላን ህይወታቸውን የሀዘን ህይወት ከማድረግ መጠንቀቅ ይኖርብናል።

## ጥናት ስምንት

**የህብረት ለቅሶ**
**የምንባብ ክፍል**
**መዝሙር 44**

**የጥናቱ ዓላማ፡--**

አንዳንድ ጊዜ ኃጢአት ሳንሰራም በእግዚአብሔር ፈቃድ መከራ ልንቀበል እንደምንችልና በዚህ ጊዜ ሙሉ እምነታችንን እግዚአብሔር ላይ አድርገን ጌታን መጠበቅ እንድንችል ለማበረታታ ነው።

**መግቢያ፡-**

ይህ የእስራኤል ህዝብ የለቅሶ መዝሙር ነው። ህዝቡና ንጉሡ እየተቀባበሉ የሚዘምሩት መዝሙር ነው። ለጦርነት ሄደው በጠላት ከተሸነፉ በኋላ በእግዚአብሔር ፊት "ለምን" እያሉ የሚያለቅሱበት መዝሙር ነው። ከመዝሙሩ እንደምናየው እስራኤላውያን ወይም የይሁዳ ህዝብ ምንም የበደሉት በደል ሳይኖር ይመስላል ይህ ሽንፈት የገጠማቸው። ይህ መዝሙር በተለይም የእስራኤልን የቱንም ንጉስ ሊያመለክት ይችላል ብለው ብዙዎች ያምናሉ። ሳንበድለው ለመከራ አሳልፎ ሰጠን ብለው እግዚአብሔርን ከመተው ይልቅ በሥራውና በባህሪው ላይ ተደግፈው ለድል እግዚአብሔርን ማመን መምረጣቸውን የምናይበት መዝሙር ነው። ይህን የህዝቡን ለቅሶ የዘመሩት ንጉስ ዳዊት የሾማቸው የሌዊ ዘር የሆኑት ከአሮን ዘር የቆኃት ቤተ ሰብ የሆኑት የቆሬ ልጆች ናቸው (2ዜና 20፡19)። መዝሙሩ በአራት ይከፈላል (44፡1-8፤44፡9-16፤44፡17-22፤44፡23-25)። መዝሙሩ በነጠላና በብዙ የተዘመረ መዝሙር ሲሆን ንጉሱና ህዝቡ የዘመሩ እንደሆነም ይታመናል።

**ክፍል አንድ መዝ 44፡1-8**
**የህዝቡና የንጉሡ እምነት፡- እግዚአብሔር ያደረገላቸው ድል ምስጋና**

**ተቀባብለው የዘመሩ መዝሙር**

ሀ. ህዝቡ፡ መዝ 44፡1-3 እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ያደረገውን ድል ያስታውሳሉ

ለ. ንጉሡ፡ መዝ 44፡4 ንጉሡም እግዚአብሔርን የከዚህ በፊቱ ድል አድራጊ ራሱ እግዚአብሔር እንጂ እርሱ እንዳልሆነ ይናገራል

ሐ. ህዝቡ፡ መዝ 44፡5 አሁን ላሉበት ችግር እግዚአብሔርን ይታመናሉ። በእርሱ ድል እንደሚያደርጉ ይናገራሉ።

መ. ንጉሡ፡መዝ 44፡ 6 በራሱ እንደማይተማመን ይናገራል።

ሠ. ህዝቡ፡ መዝ 44፡7-8 በእግዚአብሔር ድል እንደሚያደርጉና ሁሉ በእርሱ እንደሚመኩ ሁሌም እንደሚያመልኩት ይናገራሉ።

**<u>ክፍል ሁለት መዝ 44፡9-16</u>**
**<u>የህዝቡና የንጉሡ ለቅሶ፡- ስለ ደረሰባቸው ሽንፈት</u>**

***ሀ. ህዝቡ፡ መዝ 44፡9-14 ጌታ አሳልፎ ለጠላት ስለሰጣቸው በእነርሱ ላይ የደረሰውን ችግር ይዘረዝራሉ (በጠላት መማረከም ሊሆን ይችላል)***

**ለ. ንጉሡ፡ መዝ 44፡15-16 ንጉሡ እንደተዋረደ ይህም ውርደት ከጠላትና ከሚዘልፉ ሰዎች የተነሳ እንደሆነ ይናገራል**

**ክፍል ሶስት -<u>መዝ 44፡</u> 17-22**
**ህዝቡ፡ የደረሰባቸው ችግር ሁሉ ያለ በደላቸውና ያለጥፋታቸው እንደሆነ ይናገራሉ**

**<u>ክፍል አራት መዝ 44፡</u>** 23-25
**<u>መደምደምያ፡ የሁሉ ለቅሶ (የእርዳታ ጥሪ)</u>** ለቅሶና ጸሎት
ጸሎት ቁ.26 የበደሉት በደል የለም ብለው ብያምኑም የእግዚአብሔርን ምህረት ይጠይቃሉ።

**የመወያያ ጥያቄዎች፡**

1) መዝ 44፡ 1-3 ህዝቡ የሚናገሩት ምንድን ነው? ለምን ይህን መናገር አስፈለጋቸው? (መልሳችሁ ከዚህ በታች ያለውን ሀሳብ መመሳሰል አለበት፡- እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ያደረገውን ያስታውሳሉ። እግዚአብሔር የማይለዋወጥ አምላክ ስለሆነ፥ ድሮ ያደረገውን በማስታወስ የራሳቸውን እምነት ይጠብቃሉ)።

2) በቁ4ና 6 ንጉሡ የሚናገረው ምንድን ነው? (ለዚህ ጥያቄ ተመሳሳይ መልስ፡- እርሱ ንጉሥ ቢሆንም እግዚአብሔርን ንጉሤ ይለዋል። ለህዝቡም ከዚህ በፊት ድል የሰጠው እግዚአብሔር ራሱ እንጂ የህዝቡ መሪዎች እንዳይደሉ ያውጃል። በራሱና በሰይፉ እንደማይተማመን ይናዘዛል።)

3) በቁ5 እና 7-8 የህዝቡ እምነት ምን ይመስላል?

4) ከቁ1-8 የእምነትን ነገር ተናግረው ከቁ9 ጀምሮ ማልቀሳቸውን ስታይ ስለ ለቅሶአቸው ምን ትማራለህ? (ተመሳሳይ መልስ ለቅሶ የእምነት እንጂ የጥርጥር አይደለም።)

5) በቁ9-14 መሠረት ህዝቡ የሚያለቅሱት ለምንድን ነው?

**ካልጨረሳችሁ በሚቀጥለው ሳምንት ማጥናት ትችላላችሁ**

6) በቁ17-22 መሠረት ህዝቡ ለቅጣት የሚያደርስ የሰሩት ጥፋት ነበር? በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የህዝቡ ህይወት ምን ይመስላል? ከዚህ ህይወታቸው ምን ትማራለህ?

7) በቁ15-16 ንጉሡ የተዋረደው ህይወት ከምን የተነሳ ነው ይላል? (Hint: 1) ከጠላት 2) ከሚዘልፉና ከሚነቅፉ ሰዎች የተነሳ ነው)። ከዚህስ ምን ትማራለህ?

8) ከቁ23-26 ህዝቡ ከሚጸልየው ጸሎት ምን ትማራለህ? በደል ባይኖርባቸውም ስለምህረትህ ተቤዠን ማለታቸው ስለምህረት ምን ያስተምራል?

9) ከዚህ የህዝብ ለቅሶ ምን ተማርክ? እነርሱ ለሃገራቸው ነው ያለቀሱት። እኛስ እንደቤተክርስትያን የምናለቅስበት ጉዳይ ያለ ይመስልሃል? ካለ ለህብረቱ አካፍል። በጸሎታችንም ጊዜ መጸለይ እንችላለን።

**መደምደምያ፡-**

በእግዚአብሔር ፊት በንጽህና መኖር በረከትን ቢያመጣም፥ አንዳንዴ በእግዚአብሔር ፈቃድ ፈተናና መከራ ሊመጣብን ይችላል። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ለኛም ለሌሎች ያደረገውንና ማንነቱን በማሰብ ለገጠመን መከራ በራሱ ጊዜ መልስ እንደሚሰጠን አምነን በጸሎት ቢያስፈልግ በለቅሶ በፊቱ መቆየት አለብን። በህይወታችን እግዚአብሔር የሚያደርገው ሁል ጊዜ ላይገባን ቢችልም እርሱን ግን አምኖ መኖር ያዋጣናል።

# ጥናት ዘጠኝ

## የንባብ ክፍል መዝ 51

## የኃጢአት ኑዛዜ ንሰሃና እና የህይወት መታደስ

**ንጉስ ዳዊት ወደ ኦርዮ ሚስት ወደ ቤርሳቤህ ከገባ በኋላ ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ መጥቶ ኃጢአቱን በነገረ ጊዜ የዳዊት መዝሙር**

**ዓላማ፡-** እግዚአብሔርን አምነው የሚኖሩ ሰዎች ኃጢአት ቢሰሩ በፈጹም ንሰሃ መመለስ እንዳለባቸው ማስገንዘብ።

**መግቢያ፡-**

ይህ መዝሙር ማጣቀሻ ታሪክ ያለው የንሰሃ መዝሙር ሲሆን ብዙ ሰዎች ከሚያውቁት መዝሙሮች አንዱ ነው። ንጉስ ዳዊት ይቅርታንና መታደስን ከእግዚአብሔር ለማግኘት የዘመረው መዝሙር ነው። መዝሙር 51 ከ2ኛ ሳሙ 11-12 ታሪክ ጋር አብሮ የሚሄድ በንጉስ ዳዊት ህይወት የተፈጸመ እውነተኛ ነገር ነው። ንጉስ ዳዊት ኦሪዮንን በማስገደል በሰራው ኃጢአት ነቢዩ ናታን ስወቅሰው ንሰሃ የገባውን ታሪክ ጋር ይገናኛል። መዝ 6፤32፤38፤51፤102፤130፤143 ከመዝ 51 ጋር የንሰሃ መዝሙሮች ተብለው ይታውቃሉ። በተለያየ ምክንያት ሰው በኃጢአት ሲወድቅ ምን ማድረግ እንዳለበት ጥሩ ትምህርት ያስተምራል። የንሰሃ ትምህርት አንዱ የአዲስ ኪዳን ቤ/ክ ትምህርት ነው።

1. **መዝ 51 ከ2ኛ ሳሙ 11-12 እይታ፡- የንጉስ ዳዊት በኃጢአት መውደቅ**

አሞናዊያን ሀገሪቷን በወረሩ ጊዜ ሰው ሁሉ ሰልፍ ላይ በነበረ ወቅት ንጉስ ዳዊት ሳይሄድ በመቅረቱ የኤልያብን ልጅ የኬጢያዊውን የኦርዮን ሚስት ቤርሳቤህን ስትታጠብ አያት፣ተመለከታት፣አስመጣት፣በቤቱም አመነዘረባት። እርሷም አረገዘች። ይህም ብቻ ሳይሆን ኃጢአቱን ለመሸፈን ሲሞክር ኦርዮን ማስገደሉን ታሪኩ ይነግረናል። ነገር ግን ሁሉም ነገር በድብቅ የሆነ ቢመስልም 2ሳሙ 11፡27 እንዲህ ይላል " … ነገር ግን ዳዊት ያደረገው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሆነ"። 2 ሳሙ 12፡9 እና 12 "አሁንስ በፊቱ ክፉ ትሠራ ዘንድ የእግዚአብሔርን ነገር ለምን አቃለልህ? ኬጢያዊውን ኦርዮን በሰይፍ መትተሃል፥ ሚስቱንም ለአንተ ሚስት ትሆን ዘንድ ወስደሃል እርሱንም በአሞን ልጆች ሰይፍ ገድለሃል.. 12 <u>**አንተ ይህን በስውር አድርገኸዋል**</u> እኔ ግን ይህን በእስራኤል ሁሉ ፊትና በፀሐይ ፊት አደርገዋለሁ "። **የታሪኩ እውነት በንጉስ ዳዊት ጊዜ የሆነ ቢሆንም በኋላኞቹ ዘመናት ሁሉ እንደተዘመረ መዘንጋት የለብንም**

2. **መዝ 51፡1-2 የንሰሃ ሂደት**

ንጉስ ዳዊት ሰለ ሰራው ኃጢአት ምህረትና ይቅርታ ሲጠይቅ የጌታን ባህርይ ይጠቅሳል ማለትም እግዚአብሔር ቸርና ሩህሩህ አምላክ ነው ይላል። ዳዊት ለሰራው ኃጢአት ሁልጊዜ በእግዚአብሔር እጅ መውደቅን ይመርጣል (2 ሳሙ 24፡14) "ዳዊትም ጋድን፡- እጅግ ተጨንቄአለሁ ምሕረቱ ብዙ ነውና በእግዚአብሔር እጅ ልውደቅ በሰው እጅ ግን አልውደቅ አለው")። ነቢዩ ናታን ለንጉስ ዳዊት ኃጢአት እንደሰራ ሲነግረው እንደ ንጉስ ብዙ ምክንያቶችን ማቅረብና የልብ ትዕቢትን ማሳየት ሲችል አላደረገም። አዳም ለሰራው ኃጢአት ሄዋንን ምክንያት እንዳደረገ አላደረገም። ሁሉም ክርስቲያን ከዚህ መማር አለበት። ንጉስ ሳኦል ለሰራው ኃጢአት ንሰሃ መግባት ሳይሆን ያደረገው ምክንያቶችን ማቅረብ ነበር። ቁ.2 እንደሚነግረን ጌታ የህይወት ንጽህናን ይፈልጋል።

3. **መዝ 51፡3-7 አለመታዘዝ ከሁሉ በላይ እግዚአብሔርን መበደል ነው**

በዚህ ክፍል ንጉስ ዳዊት ለነቢዩ ናታን እንደነገረው ኃጢአተኛ መሆኑን ለራሱም አልካደም። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጣስ ሰውን ሳይሆን ከሁሉ በፊት እግዚአብሔርን መበደል እንደሆነም በግልጽ አስቀምጧል። ይህ ማለት ሰዎች አይጎዱም ማለት አይደለም። የሚደጋግማቸውም ቃላት መተላላፍ፣በደል፣ኃጢአት፣ክፋት አንድ ዓይነት መልዕክት የሚያስተላልፉ ቃላቶች ናቸው። በኃጢአት ምክንያት ለሚመጣውም ችግር ሁሉ እግዚአሔር የፍትህና ጻድቅ አምላክ እንደሆነ ይናገራል። ማንንም መክሰስ አይቻልም። "እነሆ፥ በዓመፃ ተፀነስሁ፥ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ" ቁ.5 ይህ ቁጥር የሚነግረን የሰው ልጅ ከመወለዱ ጀምሮ በውስጡ የኃጢአት ዝንባሌ መኖሩን ነው። ይህንን ማሸነፍ የሚቻለው ዘውትር የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ በውስጣችን በማክበር ነው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ከእኛ አይሄድም። እግዚአብሔርን ማወቅ

ጥበብን (በየቀኑ የመኖር መርህ) ማወቅ ነው። ይህን መርህ እግዚአብሔር እንዳስተማረው ይናገራል ስለዚህም እውነትን ይፈልጋል።

4. **መዝ 51፡7-12 ፊጹም ኑዛዜና ንስሃ የሙሉ ማንነት መታደስ ነው**

የንጉሱ ፍጹም የልቡ መሻት መንጻት ነው። ቁ.7 ላይ የተጠቀሰው “ሂሶጽ” በመንጻት/መስዋዕት ጊዜ ደም ለመርጨት የአይሁድ ህዝብ እንዲጠቀም ከእግዚአብሔር የታዘዘ የተክል ዓይነት ነው (ዘሌ 14፡1-7)። ንጹህ መሆን የመታደስ የመጀመሪያው ደረጃ ነው። በበደል ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይቶ መኖር ደስታ ማጣትና አጥንቶቹ እንደተሰባበሩ ሰው መሆን ነው (51፡8)። ሌላው አማኝ ሲታደስ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ እንደሚሰራ እርግጠኛ መሆን አለበት። ውድቀታችን መንፈስ ቅዱስን ከእኛ እንዲሄድ ሊያደርግ እንደሚችል ከጌታም ፊት ማጣል እንዳለ ማወቅ አለብን። በብሉይ ኪዳን “መንፈስ” እና “ቅዱስ” (ከስላሴ አንዱ አካል) የሚሉ ሁለት ቃላቶች በአንድ ላይ የተቀመጡት በመዝ 51፡10 እና ኢሳ 63፡10-11 ናቸው። ከጌታ ጋር መሆን ድነት ደስታ አለው። ይህ እንዳይወሰድ ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

5. **መዝ 51፡13-19 በኑዛዜና ንሰሃ የመታዘዝ ውጤት**

በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ንጉስ ዳዊት ከምህረት በኋላ የሚያደርጋቸውን ነገሮች ቃል ይገባል። 1. ኃጢአተኞችን ወደ ጌታ በማስተማር እንደሚመልስ ይናገራል። በተጨማሪ ቁ.14 እንደሚናገር ስለ ኦሪዮ ደም አስቦ ይጸልያል። ስለ ጌታም ጽድቅ ሲናገር ይደሰታል ቁ.15። ቁ.16 እና 17 በተጠናከረ መልኩ እግዚአብሔር የሰውን የጽድቅ ኑሮ እንጂ ያለ ጽድቅ ኑሮ መስዋዕትን አይፈልግም። ስለዚህ ለዳዊት ከጌታ ጋር ንጽህ ህብረት ማድረግ ከሁሉ ነገር ተቀዳሚ ነገር ነው። ቁ 19 እንደሚያስተምረን መስዋዕት ሁሉ ከጽድቅ መስዋዕት በኋላ መሆን አለበት። ይህም ጌታን ደስ ያሰኘዋል። ለኢየሩሳሌም ደግሞ ይጸልይላታል። የንጉሱ ከጌታ ጋር ያለው ህብረት ለኢየሩሳሌም የድል ህልውና መሰረት ነው።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ለመዝ 51 የ2ሳሙ 11-12 ታሪክ ማወቅ እጅግ ጠቃሚ ስለሆነ ታሪኩን በግልጽ ተወያዩ። ንጉስ ዳዊት በዚህ ክፍል ምን ምን ኃጢአት ሰራ? ለጊዜው ከመዝ 51 ጋር አታገናኙ።
2. ከመዝ51፡ 1-6 ቁ.3 “እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፥ ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና” ከሚለው ቃል የተረዳችሁትን መልእክት ተነጋገሩ
3. ቁ.4 “አንተን ብቻ በደልሁ፥ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ”በዚህ ጥቅስ መሰረት ሰው ኃጢአት ሲሰራ እግዚአብሔርን ብቻ ነው የሚበድለው ማለት ነው? ይብራራ።
4. 51፡7-12 ስለ ሁለንተና መታደስ ምን ያስተምራል?
5. መዝ 51፡13-19 የተረዳችሁትን ተወያዩ (ከ1-12 ጋር ማገናኘታችሁን አትርሱ)
6. የንጉስ ዳዊት ህይወት ከጴጥሮስ ሕይወት ጋር ምን ይገናኛል? ስለ እግዚአብሔር ትልቅ ምህረት ተወያዩ
7. መጽሐፍ ቅዱስ የሰዎችን ውድቀት ለምን ተጻፈ። ብንደክምም ችግር አይኖረውም ማለት ነው? ካልሆነ ምን ይመስላችሁሃል?
8. ከዛሬ ጥናት ምን እንማራለን?
9. ዛሬ ምንም እንኳን ምንም ከባድ ስህተት ውስጥ የገባን ባይመስለንም ጠቅላላ የንስህና የፍጹም መታደስ ጸሎት እንጸልይ።

***መደምደሚያ፡-***

ንጉስ ዳዊት ራሱን አልደበቀም። እግዚአብሔርን ማሳዘን መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን እንደሆነ ተናግሯል። ከጌታ ጋር ያለው ህብረት ከሁሉ በላይ ነው። መዝሙር 51 ለምንሰራው የህይወት ውድቀት ሳንደብቅና ምክንያት ሳናበዝ ራሳችንን በጌታ ፊት ማፍሰስ እጅግ አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ያስተምረናል። እግዚአብሔር እኛ ወደ እርሱ ስንመለስ እርሱም በምህረት ይመለስል። ምናልባት በሰው ፊት ከመጋለጥ ለማምለጥ ብለን የሥጋን ጥበብ መጠቀም ውድቀትን ይጨምራል እንጂ አያድነንም። ከቤተሰብ ጀምሮ የመሪ ውድቀት ለብዙ ነገሮች ውድቀት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ማወቅ አለብን። የከተማ ወይም የአንድ ሀገር ውድቀት ከንጉስ ውድቀት ጋር እጅግ የተያያዘ ስለሆነ ንጉስ ዳዊት ስለ ጽዮንም (ስለ ኢየሩሳሌም) ወደ

እግዚአብሔር ይለምናል። መንፈስ ቅዱስ ከእኛ እንዳይሄድ መንጠንቀቅ አለብን።

## ጥናት አስር

### የንባብ ክፍል፡ መዝሙር 19:1-14
### የአምልኮ መዝሙር
### “የተገለጠ የእግዚአብሔር ፍጹምነት”

**ዓላማ፡ ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ያለን ትክክለኛ መረዳት ያለንን የጸሎት ይዘት እንደሚቀርጽ ማስገንዘብ።**

**መግቢያ፡-**

መዝሙር 19 ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት ከሚናገሩ የአምልኮ መዝሙሮች አንዱ ነው። የጌታንም ታላቅነት የሚገልጸውም በፍጥረት ውስጥ ነው። ይህ መዝሙር 14 ቁጥሮች ሲኖሩት ከቁጥር 1-6 ባለው ክፍል ፍጥረት የእግዚአብሔርን ክብር እንዴት እንደሚናገር ወይም እንደሚገልጥ ያመለክታል። ሁለተኛ ከቁጥር 7-11 የእግዚአብሔር ቃል እንዴት የተወደደ እንደሆነ ይናገራል። የጌታን ቃል ሕግ፣ ምስክር፣ሥርዓት፣ ትእዛዝ እያለ ይገልጣል። በዚህም ታላቅ ቃል ውስጥ ራሱን እንዴት እንዳየና በጌታውም ፊት እንዳቀረበ ከቁጥር 12-14 ባለው ክፍል ውስጥ እንመለከታለን። ከዚህ ታላቅ ጌታ ማንነት አንጻር ራሱን እያየ የጸለየውን የልብ አምልኮ ወይም የውዳሴ ጸሎት በዚህ መዝሙር ተገልጧል። የፍጥረትን ታላቅነት አስበን እናውቃለን። የጌታ ሥራ በፍጥረት ውስጥ እጅግ ታላቅ ነው።

1. **ሰማያት ክብሩን ይናገራሉ፤ [መዝ.19:1-4]**

የዳዊት ዝማሬ ሊጠየቅ የሚገባን አንድ ጥያቄን የሚመልስ ይመስላል። ሰማይና የሰማይ ፍጥረታት ምን ያሳስቡናል፤ ያመለክቱናል? ሰነፍ አንዳች ሳያስተውል ይቀርና ፍጥረትን እንዳለ ከማየት በስተቀር እግዚአብሔርን ሳያይበት ይቀራል። ከፍጥረት ጀርባ ምን እንዳለ አያስተውልም። እጅግ ውብ የሆነ ስዕል ወይም ቅብ ስታዩ ምን ታስታውላላችሁ? ሰዓሊውን ወይም የቀባውን። የቀባውን ሰው ማስታወስና ማድነቅ ካልቻለን ከላይ ያለውን ብቻ የምናይ ሰዎች ብቻ እንሆናለን።

እግዚአብሔር የረዳው ከፍጥረት ውበት ፈጣሪውን አድንቆ ስለዚህ ጌታም ማንነት ተረድቶ ራሱን ያይበታል። ዘማሪው የሚያስተውለው፤ ሰማያትንና የሰማይ ፍጥረታትን ቀና ብሎ ያየው አስተዋይ የፈጣሪን ክብር ይመለከታል ብሎ ለማረጋገጥ ነው። የጌታ እጅ ሥራ የሆኑት በቀን የሚናገሩት ነገር አላቸው፤ በሌሊት ደግሞ የሚፈነጥቁ ከዋክብትና ጨረቃ አጥብቀው የሚያወሱት የጌታን ግርማ ነው። እውነተኛ የሆነውን የሳይንስ ግኝቶችን መመልከት ጌታ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ያስተምረናል 19፡4 “**ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ፥ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ**”።

የእነዚህ ፍጥረታት መልዕክት እስከ ዓለም ዳርቻ የሚወጣ ነው። በሥፍራ፣በባህል፣በሥልጣኔና እውቀት ፣በማህበረሰብና በዘረኝነት፣ በፖለቲካም ሆነ በቋንቋ ሳይወሰኑ ለሰው ልጅ ሁሉ ስለ ታላቁ ፈጣሪ ይናገራሉ።

2. **ፀሐይ የኃይሉ ብርታትና ነጸብራቅ** [19:5-6]

ፀሐይን በሰማይ ስናያት ምን ታመለክታለች? ለዚህም ዘማሪ ፀሐይን እንደ ሙሽራና እንደ አርበኛ አድርጎ ያሳያል። የሙሽራ ፊት ከእልፍኙ ሲወጣ በደስታ እንደሚፈካ/እንደሚያበራ፤ የፀሐይ ውበት የጌታን ድምቀትና ቁራጥነት ታሳያለች። እንደ አርበኛ ሲል በቁርጠኛነት በኃይሉ ታምኖ ጸሐይ ጨለማን እንደምትረታ በፊቱ አንዳች ላይሰወር ሁሉን ይገልጥ ዘንድ ለሁሉ ብርሃን ይሆን ዘንድ ያለውን ግርማ ያሳያል።

ይህ በምድር ሁሉ እንደሚሆን ሲገልጽ **“አወጣጡ ከሰማያት ዳርቻ ነው፣ ዙረቱም እስከ ዳርቻቸው ነው፤ ከትኩሳቱም የሚሰወር የለም”** በማለት ይናገራል። በብርሃኑ ነገርን በመግለጥ ቢሆን በማቃጠል ችሎቱ አንዳች እኩያ የለውም።

ለመውጣት መግባታችን ምክንያትና በላያችን ለመፍረድ ጉልበትና ችሎት ያለው እርሱ ብቻ መሆኑን እንደ ምሳሌ ያመለክታል።

3. ለእግዚአብሔር-ለብቻኛ ፈጣሪ መገዛት

**ዘማሪው (የሰው ልጅ) እነዚህን ነገሮች በማስተዋል ለፈጣሪ መገዛት አለበት። ለምን? ለሚለው መልሱን መዝ 19፡7-11 ያስተምራል። በቃሉ ውስጥ የተገለጠ ጌታ** [መዝ 19፡ 7-11] በዚህ ክፍል የጌታ ቃል በተለያየ ነገር ተገልጧል። ማለትም ውጤቱንም በማስከተል (ለምሳሌ "**የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው" ስለሆነ ውጤቱ "ነፍስን ይመልሳል" "የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ ነው" ውጤቱ "ሕፃናትን ጠቢባን ያደርጋል"**። ህጻናት የሚለው ትሁታንና የዋሆችን ሊያመለክትም ይችላል። ጌታን በቃሉ ውስጥ እንዴት እንደሚገለጥ ለማሳየት የቃሉን ሥራ ህግ፣ ምስክር፣ ሥርዓትና ትእዛዝ በማለት እንዴት እንደተገለጠና እንደሚሰራ ያመለክታል።

ሀ. **መዝ 19፡7 ህጉ ፍጹም ነው፡-** ፍጹም የሆነው ህግ የሳተችን ነፍስ ይመልሳል። ከመጥፋት ይጠብቃታል፤ ከጠፉችም ደግሞ ይመልሳታል። በእግዚአብሔር ዘንድ የራቀን እንደገና የሚያድስ በቀናው ጎዳና የሚያስኪድ የይቅርታና የምህረት ኃይል በእርሱ ዘንድ አለ። መታመን ብቻ መሰረታዊ ነገር ነው።

**ለ. መዝ 19፡7 ምስክሩ የታመነ ነው፡-** በሰው ልጅ ህይወት የሚሰራው ድንቅ ነው። "ሕፃናትን ጠቢብ ያደርጋል" በማለት ላልበሰሉ ብስለትን፣ ማስተዋል ለጎደላቸው ጥበብን የሚሰጥና ጠቢብ አድራጊ መሆኑን ያሳያል።

**ሐ. መዝ 19፡8 ሥርዓቱ ቅን ነው፡-** የእግዚአብሔር ሥርዓት በትክክል ስለሚመራ ለሚከተሉት የልብ ደስታን ይሰጣል። እውነተኛ ደስታ ያለው የዚህን ጌታ ሥርዓት በመከተልና በመጠበቅ ነው። ሥርዓቱን የሚከተሉት በቅን መንገድ ላይ ራሳቸውን ያገኛሉ። ከዚህ የተነሳ ነፍሳቸው ከሀዘንና ከጸጸት በመጠበቅ የልባቸው ደስታ ሙሉና የጸና ይሆናል።

**መ. መዝ 19፡8 ትእዛዙ ብሩህ ነው፡-** ይህ አባባል የጌታ ትእዛዝ የማያዛባና ግልጽ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በእርሷ ለሚመሩ ብሩህ ቀን ይወጣላቸዋል፤ ወይም በቀን የሚመላለሱ ጨለማ በመንገዳቸው የሌላቸው ናቸው። ዓይናቸው የበራላቸው ናቸው፤ አይሰነካከሉም። የልቧናቸው ዓይኖች የበሩ ናቸው፡፤ አካሄዳቸው የተቃና ነው።

**ሠ. መዝ 19፡9 የጌታ ፍርሃት ንጹሕ ነው።** ይህ የጥበብ ቃል ነው። ሰውን ለዘላለም ከጥፋት የሚጠብቅ እንደ እግዚአብሔር ፍርሃት ያለ አንዳች የለም። ስለዚህ ነው በቃሉ ውስጥ ያለ ጥበብ ሰውን ወደ እግዚአብሔር ፍርሃት ስለሚመራ ዘላለማዊነት አለው።

**ረ. መዝ 19፡9 ፍርዱ እውነትና ቅንነት ነው፡-** የጌታ ፍርድ እውነትንና ቅንነትን በአንድነት የያዘ እንከን የማይወጣለት ነው። ይህ ጌታ የሚበይነው እንከን የማይወጣለት በፍርዱ ጥላ ያሉ ፍጥረታት ሁሉ በእውነትና በቅንነት መመራታቸውን ያስረግጣል።

**ማጠቃለያው፤**

**የጌታ ቃል እንደዚህ ስለሆነ**

**ሀ. የከበረና የሚፈለግ ነው (መዝ 19፡10)፡-** "ከወርቅና ከክቡር ዕንቁ ይልቅ ይወደዳል፤ ከማርና ከማር ወለላም

ይጣፍጣል።" ይህ ቃል ደግሞ የሚያመለክተው ዋጋው እጅግ የላቀ መሆኑን ነው። ለሰው ልጅ ሞገሱና ጌጡ ይህን ቃል መጠበቅ ነው። የሚመረጥ ጣፋጭ ነው። ችግር ከሌለበት በቀር ማንስ ይጠላዋል? ለሁሉም ሰው ግን እንደወርቅና ማር የሚሆነው ሲጠብቀው ነው።

**ለ. የዘማሪው ምርጫ ፡-** "ባሪያህ ይጠብቀዋል፤ በመጠበቁም እጅግ ይጠቀማል።" ሁለት ነገርን ይናገራል። የጌታ ቃል ወደው በምርጫ ሊጠብቁት የሚገባ ነው። ይህ ቃል ወደው ለሚጠብቁት ጥቅም አለው። ቀደም ብለን እንደ አየነው፤ ለቃሉ በመገዛት ዕረፍትና በረከት አለ ። ዳዊት ይህን ተረድቶ ነው "ባሪያህ ይጠብቀዋል፤ በመጠበቁም እጅግ ይጠቀማል" የሚለው። ስለዚህ መጠበቅ ጥቅም አለው ማለት ነው።

**እንደዚህ ውድ እና እጅግ ጣፋጭ ከሆነ የዘማሪው ጥያቄና ትኩረት በሚቀጥሉት ቁጥሮች ተጠቅሰዋል ( መዝ 19፡12-14)**

***ሀ. ዘማሪው በዚህ እጅግ ግሩም ቃል ላይ ስህተት እንዳይሰራ መጠንቀቅና ሁል ጊዜ በንስሃ መመላለስ እንዳለበት ይናገራል። እኛም በተሰጠን ውድ የጌታ ቃል ድነት መጠንቀቅ አለብን።***

**ሌሊትና ቀን ለቃሉ ጥንቃቄ በተሞላ ህይወት መኖር የጌታ ሰው ኃላፊነት ነው** [19:12-14]

የዳዊት መረዳት ያደረሰው ራሱን ወደ ማየትና በተሰበረ ልብ ወደ አምላኩ መቅረብ ነው።

ማንነትን መለየት፤ ከእግዚአብሔር አንጻር ራሱን ሲያይ

- "ስህተትን ማን ያተውላል? ከተሰወረ ኃጢያት አንጻኝ " አለ።
- "የድፍረት ኃጢያት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ"
- "የዚያን ጊዜ ፍጹም እሆናለሁ፣ ከታላቁም ኃጢአት እነጻለሁ"

የመጨረሻው ልመናው ሁለንተናን የሚመለከት ነው፡-

- "አቤቱ፣ ረድኤቴ መድኃኒቴም፣ የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን"። እግዚአብሔር ሽንገላን ያውቃል። ከእርሱ መደበቅ አንችልም። ሁል ጊዜ ራሳችንን ግልጽ ማድረግ አለብን።

በአጠቃላይ ዘማሪው ሁለንተናውን ለጌታ ማስገዛት ይፈልጋል። ሁላችንም ይህ ህይወት ልኖረን ይገባል።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. የመዝ 19 ጥናት ዓላማው ምንድ ነው?
2. መዝ 19፡1-2 ላይ ፍጥረት እንደሚናገር ያስተምራል? እንዴት ፍጥረት ይናገራል? ወይስ ምን ማለት ነው?
3. መዝ 19፡1-4 ሊነግረን የፈለገው ምንድ ነው? ድምጻቸው ወጣ ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. መዝ 19፡5 ሙሽራና አርበኛ የሚለውን ምሳሌያዊ ንግግር ምን ማለት እንደሆነ ተወያዩ
5. መዝ 19፡7-9 በማንበብ ዘማሪው ለጌታ ቃል የተጠማቸውን ስያሜዎች ተነጋገሩ። የእግዚአብሔርን ህግ የመከተል ውጤቱስ ምንድ ነው ይላል?
6. መዝ 19፡ 12-14 እየተናገረ ያለው ሐሳብ ከላይ ከተጠቀሰው ከዋናው ከዘማሪው ሀሳብ ጋር እንዴት ይገናኛል?
7. ከተመቻቸሁና በጎ ፈቃዳችሁ ከሆነ በሚቀጥለው ሳምንት ስለ ፍጥረት የሚያሳይ ቪዲዮ/ዲቪዲ እንድታዩ እናበረታታለን (ሁሉም ቡድን ላይሆን ይችላል) ።

8. ከዛሬው መዝሙር ለህይወታችን ምን ቀረ?

***መደምሚያ፡-***

ስለ እግዚአብሔር ሀልውና ከተፈጥሮ ማየት እንደሚቻል መዝ 19 በግልጽ ያስቀምጣል። በርግጥ የሰው ልጅ ራሱ አፈጣጥሩ የእግዚአብሔርን መኖር ያረጋግጣል (ህሊናችን ማለት ነው)። ተፈጥሮ ተጨማሪ ነገር ነው። ስለዚህ ተፈጥሮን እያዩ እግዚአብሔርን ማምለክ የዚህ መዝሙር ዓላማውም ነው። ለዚህ ህያው ለሆነ ከወርቅ ይልቅ ለከበረና ከማር ይልቅ ጣፋጭ ለሆነ ቃል መገዛት የዘማሪው አንዱ ጸሎት ነው። በየቀኑም ይህንን ቃል እንድንል ያሳስባል። ጌታ ለሰጠን ክቡር ድነት ቦታ መስጠት እጅግ መሰረታዊ ነገር ነው።

## ጥናት አስራ አንድ

### የንባብ ክፍል

### *መዝሙረዳዊት 124*

### *የእምነት ወይም የመታመን መዝሙር*

**ዓላማ፡- የእግዚአብሔርን ጥበቃና አብሮነትን በማስተዋል እግዚአብሔርን ማመስገንና ማሳወቅ**

***መግቢያ፡-***

መዝሙር 124 ዘማሪው እግዚአብሔርን መታመኑን ከሚገልጡ መዝሙሮች መካከል የሚካተት መዝሙር ነው፡፡ መዝ **11፥ 16, 23, 62, 63, 91, 121,** ከዚህ መዝሙር ጋር ተያይዞ በምሳሌነት የሚጠቀሱ መዝሙሮች ናቸው፡ ይህን መዝሙር የመዝሙር 18 እና 69ን ድምጽ ስለሚያስተጋባ የጻፈው ዳዊት እንደሆነ ብዙዎች ያምናሉ። ከምርኮ በኋላ ግን ይህ መዝሙር ብዙ ተዘምሯል። በዚህም ዘማሪው ተራሮች በኢየሩሳሌም ዙሪያ እንደሆኑ እንዲሁም እግዚአብሔርን በህዝቡ በእስራኤል ዙሪያ መሆኑን በመረዳት እና በማስተዋል የዘመረው የእምነት መዝሙር ነው። ለዚህም በመዝ 125፡2 ያለውን ሃሳብ በማየት በግልጽ መረዳት ይቻላል ። መዝ 124 እስራኤልን ሊውጧት የሚሹ ጠላቶች በዙሪያው ቢኖሩም በአምላኳ በእግዚአብሔር ተጠብቃ ከጠላቶቿ ሁሉ ተርፋ በአሸናፊነት ለመቆም የመቻሏን ሚሲጢር እያበሰረ፡ ይናገራል። በመቀጠልም ይህንን ላደረገው ለእርሱ ለእግዚአብሔር የምስጋናን ያቀርባል፡፡

የእግዚአብሔር ህዝብ ከግብጽ ወደ ተስፋይቱ ምድር ባደረገው ጉዞ ላይ ብዙ ጠላቶች መንገድ ዘግተው አላሳልፍ በማለት ተዋግተዋቸው ነበር፡ እንደ እውነታው ቢሆን ኖሮ የእስራኤል ጠላቶች ከእነሱ ይልቅ የሚበረቱ እና ሊያጠፉቸው እንደሚችሉ የሚያጠያይቅ ጉዳይ አልነበረም፡፡ የእግዚአብሔር ህዝብ በዙሪያቸው ካሉት ጠላቶቻቸው አንጻር ሲታዩ እጅግ ትንሽ ያውም ለጦርነት ያልሰለጠኑ ለውጊያ ብቃት የሌላቸው ነበሩ። ነገር ግን "ከጎናቸው እግዚአብሔር ነበር"። እግዚአብሔር ደግሞ ጥቂት እና ደካማ ከሚመስለው ህዝቡ ጋር ስለነበረ፡ እንዲህ ማለት እንችላለን "ምንም ለሌለው እግዚአብሔር አለው " ወይንም "ሁሉ ላለው ለመሰለው ግን እግዚአብሔር የለውም"። ይሄ ስለሆነም ሊያጠፉቸው የሚፈልጉና የሚችሉት የጠላቶቻቸው የከነዓናውያን የኬጢያውያን የአሞራውያን የፌሪዛውያን የኤዊያውያን እና የኢያቡሳዊያን አይን እየተመለከተ የእግዚአብሔር ህዝብም የእግዚአብሔርን ማዳን እያየ በጠላቶቻቸው መካከል በድል ተሻገረ ወደ ተሰጣቸው የተስፋ ምድርም ገቡ።

**የርዕስ ማብራሪያ**

**"የየዕለቱ መዝሙር"**

ይህ ከመታመን ወይንም ከእምነት መዝሙራት መካከል የሚመደብ ሲሆን፡ በመጀመሪያው ቁጥሮች ላይ እንደምንመልከተው ይህ ክፍል እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር ባይሆን ኖሮ እስራኤል ሊደርስባት የሚችለውን ይዘረዝራል።

**መዝ 124፡1 እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር ስለ መሆኑ አዋጅ**

***ሀ. መዝ 124፡ 1 "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን እስራኤል እንዲህ ይበል"***

*መዝሙረኛው የሚጀምረው እስራኤል ያለፈበትን ጎዳና ወደ ኃላ ዞር ብሎ በመቃኘትና በመመልከት እንዴት በጠላቶቻቸው መካከል ሊያልፉ ቻሉ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በዚህ ወይም በዚያ ምክኒያት ነው (በኃይላችን፣ በጉልበታችን ወይም በጥበባችን ነው) የሚለው ስላልነበር ለዚያ ጥያቄ ያገኘው ምላሽ እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር መሆኑ ብቻ እና ብቻ ነበር እንጂ ሌላ ሊቆጠር የሚችል ምንም ዓይነት በቂ ምክኒያት አላገኘም። ዛሬ ህይወታችን በየትኛውም አይነት ሁኔታ ውጣ ውረድ የበዛበት ሰልፍ የበረታበት ቢሆንም እንኳን እስራኤልን ባለፈበት መንገድ አብሮ ሆኖ የረዳ እና ያበረታው የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር ይሆናል ሳይሆን ከህዝቡ ጋር ነው።*

**ለ. መዝ 124፡2-4 እግዚአብሔር ጽኑ መሸሸጊያ አምባና እና የማምለጫ ዓለት ነው፡**

2**እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን ሰዎች በእኛ ላይ በተነሡ ጊዜ፥**

3**ቍጣቸውን በላያችን በነደደ ጊዜ፥ በዚያን ጊዜ ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር**

4**በዚያን ጊዜ ውኃ ባሰጠመን ነበር፥ በነፍሳችንም ላይ ፈሳሽ ባለፈ ነበር**
5**በዚያን ጊዜ የጐርፍ ውኃ በነፍሳችን ላይ ባለፈ ነበር።**

መዝሙረኛው እንዳስቀመጠው በመጀመሪያው ቁጥር ላይ እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር መሆኑ ምንም ጥያቄ የለውም። ይሁን እንጂ ታዲያ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑ ሰዎች በእኛ ላይ አይነሱም ማለት አይደለም ወይንም ሰልፍ ጦርነት አልባ ጉዞ ይሆንልናል ማለት ከቶውንም አይደለም፡፡ ምክንያቱም የጻድቃን መከራቸው ብዙ እንደሆነ (መዝ 34፡19) እንዳውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለሆነ ሰይጣን ሆን ብሎ ቀዳዳ እና ምክንያት ፈልጎ ሰዎችን ሊያሰልፍብን ጦርነት ሊከፍትብን እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል። ውጊያም ሆነ ሰልፍ በህይወታችን በሚነሳበት ጊዜ ቸኩለን እግዚአብሔርን ምን አድርጌው ነው ሰዎች ሁሉ የተነሱብኝ በማለት ግራ መጋባት እና መናወጥ የለብንም (መክ10፡4)። በአጭሩ ጠላቶች አይኖሩንም ብለን ማሰብ እንደሌለብን ከዚህ ክፍል መገንዘብ እንችላለን። **እግዚአብሔርንም ምንም አድርገነው ወይንም ሰዎችን ያደረግናቸው ነገር ኖሮ ላይሆንም ይችላል፡፡ ነገር ግን** እግዚአብሔር ወደ አየልን እንዳንደረስ በመንገዳችን ላይ ጠላቶች ይነሱብናል። ይህም ብቻ አይደለም የጠላቶቻችን ፍላጎት እና ምኞታቸው በህይወት እንኳን እንድንኖር የማይፈልጉ ጨካኞች መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልገናል። ቢሳካላቸው ደግሞ ዓላማቸው ነፍሳችንን የሚጎዳ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል፡ (ሮሜ 8፡35)።

**ሐ. 124፡6-8 እግዚአብሔርን ስለ ጥበቃው በማስተዋል በመታመን ማመስገን**

6. **ለጥርሳቸው ንክሻ ያላደረገን እግዚአብሔር ይባረክ።**
**7. ነፍሳችን እንደ ወፍ ከአዳኞች ወጥመድ አመለጠች። ወጥመድ ተሰበረ እኛም አመለጥን**
**8. ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን በሠራ በእግዚአብሔር ስም ነው**

ዘማሪው ከዚህ በፊት ባሉት ቁጥሮች እስራኤል ያለፈችበትን ጎዳና በታሪክ ዞር ብሎ በመገረም ከተመለከተ በኃላ እግዚአብሔር ከጎኑ ሆኑ ያደረገላትን ጥበቃ በማስተዋል ለመቃኘት ሞክሯል፡፡ በዚህም ሊነክሷት አፋቸውን ከፍተው ጥርሳቸውን አሹለው የነበሩት ጠላቶቿ አላገኟትም። ሊነክሷት አልሞከሩም ማለት አይደለም ወይንም ሊነክሷት ይችሉ ነበር ማለትም አይደለም፡፡ ዳዊት በስዕላዊ መልኩ የሳለው እጅግ በጣም ቀርቦው እሰይ አገኘን ነክስናት ባሉበት እርሷም አበቃልኝ ተነከስኩ ባለችበት ጊዜ ነው ድንገት ከጥርሳቸው ውስጥ እግዚአብሔር በተዓምራቱ ያስመለጣት። የሃማ ታሪክ ይህን ያስተምራል (አስቴር 9፡1-6)። እንዲሁም ሊይዛት የተዘጋጀው ወጥመድ ሸሽታ አመለጠችው አይደለም የሚለን ወይንም ሊይዛት ትንሽ ሲቀረው አመለጠች አይደለም የሚለን። ይህማ ሁሉም ሰው ለጥቂት ተረፍኩ ነው የሚለው ። ይልቁንም እስራኤል አንድ ጊዜ አይደለም ብዙ ጊዜ ወጥመድ ውስጥ ገብታ ነገር ግን ወጥመድ ተሰብሮ ነው እስራኤል ያመለጠችው። እግዚአብሔር ለፈርዖን የላከበት መልዕክት ህዝቤን ልቀቅ የሚል ነበር ፈርዖንም ህዝቡን አለቅም በማለት አሻፈረኝ ቢልም ትዕዛዝ ከዙፋን ወጥቶል እና የፈርዖን ቀንበር ህዝቡን ሊይዛቸው አልቻለም ቀንበር ተሰብሮ አመለጡ። ዘጸ5፡1-2። ለእስራኤል መዳን ከጠላቶቿ ማምለጥ ይሄ ወይንም ያን ተብሎ የሚጠቀስ ሳይሆን ረድኤት የሆነላት ሰማይንና ምድርን የፈጠረው በእግዚአብሔር ስም ነው። በማለት ከደመደመ በኋላ ዘማሪው ትኩረቱን ይህን ሁሉ ለእስራኤል ላደረገው አምላክ ምስጋና ውዳሴ በማቅረብ ይጀምራል።

እግዚአብሔር ያደረገልን ነገር ሁሉ ተሰብስቦ ወደ ምስጋና እና አምልኮ ሊያደርሰን ይገባል።የእግዚአብሔር ስም ለአብረሃም ጋሻ ሆኖለታል (ዘፍ.15፡1)። ዛሬም ጋሻችን ነው በሚያስፈራውና በሚያስደነግጠው ፊት እግዚአብሔር እቁሞ ለእኛ የሚያደርጋትን ማዳን እናያለን (ዘጸ 14፡13)። በዚህም ዘመን ዘማሪው እንዲህ ብሎ ዘምሯል፡-

"ስምህ ጋሻዬ እና ከለላዬ ሆኖልኛልና ጌታ በዘመኔ፣
ሳልሰጋ እኖራለሁ ልቤ አርፎ፣
በኃያሉ ክንድህ ተደግፎ"

ዘጸ 15፡ 3 "እግዚአብሔር ተዋጊ ነው ስሙም እግዚአብሔር ነው። ማዳኑ ከወደሮኞቻችንና ከሚጠሉን ሁሉ እጅ ነው"።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. **መዝ 124፡ 1 እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን ኖሮ የሚለውን ሃሳብ እንዴት ትረዳዋለህ?**

2. **አስቸጋሪ በሆኑ ጎዳናዎች  እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው ለማለት ቀላል ይመስላችኋል ? ለምን? (መዝ 23፡4)**

3. **በተመሳሳይ መልኩ እስራኤል ያለፈችባቸውን አስቸጋሪ ጎዳናዎች የምታስታውሱትን ያኽል ተነጋገሩበት ?**

4. **መዝ 124፡2-5 እስራኤል ስለ ገጠማት ተግዳሮት ዝርዝር ነገር ደረጃ በደረጃ ተነጋገሩበት ?**

5. **በመዝ 124፡4- 5 በዚህ ክፍል የተገለጡ ስዕላዊ መግለጫዎች ምንድ ናቸው?**

6. **መዝ 124፡6-7 ዘማሪው ሥዕላዊ በሆነ መልኩ ሊገልጽ የሞከረውን ሃሳብ እንዴት ትረዳዋለህ ?**

7. **በዚህ ክፍል ሃሳብ መሰረት እስራኤል በነዚህ ሁሉ ተግዳሮት ጸንታ የቆመችበት ሚስጢር ምንድነው ? በሁኔታዎች ውስጥ የእግዚአብሔር አብሮ መሆን ወይም አለመሆን የሚያመጣው ልዩነት ምንድነው ትላለህ?**

8. **ዛሬ ለምታልፍበት ሁኔታ የሚሆን እውነት ከዚህ ክፍል ምን ተረዳህ?**

9. **ከዚህ በፊት ባለፍክበት ልብ ሳትለው እግዚአብሔርን ስለጥበቃው ሳታመሰግንበት ያለፍከው ነገር ይኖር ይሆን? በእግዚአብሔር ታመኑ!!**

***መደምደሚያ፡-***

እነሆ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋም መዝ 121፡4 ዓይኖቻችንን ወደተራሮች አንስተን ረዳታችንን ፍለጋ አንደክምም ረድ ኤታችን ሰማይንና ምድርን ከሰራው ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ ተረድተናል አውቀንማል። እግራችንን ለመናወጥ አይሰጥም እነሆ  እግዚአብሔር ይጠብቀናል ይጋርደናል፡፡ ፀሃይ በቀን አያቃጥለንም ጨረቃም በለሊት፡ እርሱ ከክፉ ሁሉ ይጠብቀናል ነፍሳችንንም ይጠብቃታል፡ ከሌሊት ግርማ በቀን ከሚበርር ፍላጻ በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር አንፈራም በላባዎቹ ይጋርደናል ከክንፎቹ በታች ተማምነን እንቀመጣለን፡ መዝ 121፡1-8 መዝ 27፡1=5 መዝ91፡1-16 ( ይነበቡ)።

ስለዚህ በእግዚአብሔር ህዝብና በጠላቶቻቸው መካከል ያለው ልዩነት የእግዚአብሔር አብሮ መሆን ወይም አለመሆን ብቻ ነበር ማለት ነው። የእግዚአብሔር ህዝብ ሙሴ ከሞተ በኋላ እኛ  ለሙሴ እንደታዘዝን ሁሉ እንዲሁ ለአንተም እንታዘዛለን ነገር ግን እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር እንደነበር እንዲሁ ከአንተ ጋር ይሁን በማለት ለወጣቱ መሪ ለኢያሱ የእግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር የመሆኑን ቁልፍ ሚናና አስፈላጊነት ሲያሰምሩበት እንመለከታለን (ኢያ 1፡17)። እግዚአብሔር ከጥቂቱ ጋር ሲሆን ብዙ ይሆናል። እግዚአብሔር ከደካማው ጋር ሲሆን ብርቱ ይሆናል። እንዲሁም እግዚአብሔር ከተሸነፈው ጋር ሲሆን ከአሸናፊዎች ሁሉ ይበልጣል፡፡ ዋናው ቁም ነገር የእግዚአብሔር ህዝብ ድል በቀናው ጊዜ ይህን እኔ በሃይሌ እና በብርታቴ አደረኩት እንዳይሉ ይልቁንም ጠላቶቻቸው ሲገዙላቸው በሰላም ተዘለው ሲቀመጡ ይህ ሁሉ የሆነው እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለሆነ ብቻ ነው ብለው ከጎናቸው ሆኖ ከንዳቸውን ያበረታውን አምላካቸውን በመታመን እንዲያመሰግኑት እንዲያመልኩት ያስፈልጋል (ኢያ7፡12)።

## ጥናት አስራ ሁለት

### የንባብ ክፍል

### መዝሙረ ዳዊት 8

### የምስጋና መዝሙር

### እግዚአብሔር ታላቅና ልዑል ፈጣሪ ስለሆነ ሊመሰገን ይገባዋል

**ዓላማ፡-** እግዚአብሔር (ኤሎሀም) ኃያልና ፈጣሪ ልዑል መሆኑን አውቀን ማመስገን እንዳለብን ደግሞ ለማሳሰብ

***መግቢያ፡-***

ይህ መዝሙር በመጽሐፍ አንድ (በመዝ 1-42) ውስጥ ያለው መዝሙር ሲሆን ያተኮረው በእግዚአብሄር ጌትነት ላይ ነው። ስለ ሰው ልጅ ክቡርነት የሚያሰላስልና የሚያውስ መዝሙር ነው። በተጨማሪም የፍጥረትን ታሪክ ከዚህ መጽሐፍ ጀርባ እንዳለ ማወቅ አይከብድም። ዘማሪው የጌታን የፍጥረቱን ኃይል እያሰበና እግዚአብሔርን አያመሰነ ይገኛል። በመዝሙር መጽሐፍ የተለያዩ የምስጋና መዝሙሮች ማለትም የግለሰብና የጉባኤ ወይም የማህበረሰብ መኖራቸውን መርሳት የለብንም።

ዘማሪው በዚህ መዝሙር በተለይም ሁለት ነገሮችን በተመስጦ ውስጥ በማየት ይደነቃል፣ያመሰግናል። 1. በሰማይ ባሉ ፍጥረታት የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ሲያይ 2. በዚህ ትልቅ ፍጥረት ውስጥ እግዚአሔር ሰውን ማክበሩን ማለትም እርሱን በምሳሌው መፍጠሩንና እንዲገዛም ማድረጉ። ይህ <u>**ዘማሪው እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን አድርጎታል።**</u> ፍጥረት ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ አስባችሁ ታውቃላችሁ? ግን ደግሞ እግዚአብሔር አንተን ወይንም አንቺን እንዴት በመልኩና በምሳሌው እንደፈጠረስ አስበህ/ሽ/ ታውቃለህ/ለሽ?

ቁ.1 እና ቁ.9 መሪ አዝማቾች ወይም ሀሳቦች ሲሆኑ የተቀሩትን ቁጥሮች ለሁለት በመክፈል ማየት ይቻላል ማለትም ከ2-4 እና ከ5-8። በተጨማሪ ከፊት መዝሙር 7ን እና ከኋላ መዝ 9ን ማንበብ የበለጠ እውቀት ይሰጠናል። መዝሙረኛው መዝ 7 ላይ እርዳታ በመፈለግ የሚዘምር ሲሆን፣ መዝ 8 ደግሞ ኃይሉን በመረዳቱ አመስግኖ በመዝ 9 ላይ ግን በትልቅ አምልኮ ይቀርባል። መዝሙር 8 ከመዝ **104፣107፣ 116፣ 136 እና ሌሎችም ጋር በትምህርቱ ተመሳሳይነት አለው። በአዲስ ኪዳንም ጌታ ኢየሱስ** በማቴ 21፡15-17 የመዝ 8፡2 ሀሳብ ጠቅሷል።

1. ***መዝሙር 8፡1፣2-4 ጌታ ታላቅነቱን በምስክር ያረጋገጠ ስለሆነ መመስገን አለበት***

ዘማሪው መዝሙሩን የሚጀምረውና የሚጨርሰው በምስጋና ሲሆን የሚያመሰግናቸውን ምክንያቶች በዝርዝር በቁጥር 1 እና 9 መካካል ባሉት ቁጥሮች ያስቀምጣል። "... **ስምህ በምድር ሁሉ እጅግ ተመሰገነ"፥** ይህ ቁ.1 ላይ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ስም የባህሪዩ ወይንም የማንነቱ መገለጫ ነው ። ለህዝቡም ዋናውም መታወቂያ መንገዱ ስሙ ነው ((ዘጸ 3፡13-14)። ስሙ ባህርዩና ኃይሉ ነው። ምስጋናውን ለመስጠት ስሙን መጥራት መሰረታዊ ነገር ነው። በቁ.2 መሰረት ጠላቶቹን ለማሳፈር ተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን ሁሉ ነገር የማይገባቸው ከሚመስላቸው ልጆችና ሕጻናት እንዲያመሰግኑት ያደርጋቸዋል (ትሁታንና የዋሆች)። ይህም ኃይል አለን ለሚሉት ለጠላቶቹ እፍረት ይሆናል። ሳይንስ ትልልቅ ነገሮችን አግኝቷል (ለምሳሌ ፕላኔቶችን) ነገር ግን በትንንሽ ነገሮች ውስጥም የእግዚአብሔርን ኃይል ማየትና ማመስገን ይቻላል። እጅግ ትልቅ ነው ከሚባል ከሰው ነገር የእግዚአብሔር ትንሽ ነው የሚባል ነገር ይበልጣል (1ቆሮ 1፡25)። ለምሳሌ ያህል ቁ. 3 ላይ በዝርዝር ከፍጥረት የተጠቀመው ጸሐይን፣ጨረቃንና ኳዋክብትን ነው። መዝ 19፡1 እና 104 ተመሳሳይ ነገር ይኖራቸዋል። በተጨማሪ ይህ መዝሙር ከዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ጋር ይዛመዳል። ታዲያ እነዚህን ግዙፍ ፍጥረታት ስታዩና ስታስቡ የሰውን ልጅ ከዚህ ጋር ስናነጻጽር እግዚአብሔር የሰጠን ክብር እጅግ አስገራም ነው። ስለዚህ በቁ.4 መሰረት ሰው እንዴት የተከበረ የእግዚአብሔር ፍጥረት እንደሆነ በማሰብ ዘማሪው እግዚአብሔርን ያመሰግናል።

2. ***መዝ 8፡5-8 ለሰው ልጅ የተሰጠው ትልቅ ሥልጣን በማሰብ ህዝቡ እግዚአብሔርን ማመስገን አለበት***

ዘማሪው ቁ. 4 ላይ በጥቅሉ ያስቀመጠውን ማለትም ለሰው ልጅ እግዚአብሔር ያደለውን ሥልጣንና ክብር በሚቀጥሉት ቁጥሮች ያብራራል። ቁ. 5 ላይ "ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው" የሚለው ሀረግ ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ያለውን ማንነት የሚጠቅስ ሊሆን እንደሚችል ብዙዎች የሚስማሙበት ሐሳብ ሲሆን ከመላዕክት አሳነስከው የሚለውም ሰው ሟችና በጊዜ የተገደበ መሆኑን ያሳያል። ከእግዚአብሔር ተልከው መላዕክት ለምሳሌ በጦርነት ጊዜ የሚያደርጉትን ታላላቅ ነገሮችን ዘማሪው እያሰበ ዘምሯል ብለው ያምናሉ ("በዚያችም ሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ ወጣ፥ ከአሦራውያንም ሰፈር መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ገደለ ማለዳም በተነሡ ጊዜ፥ እነሆ፥ ሁሉ በድኖች ነበሩ" (2 ነገስ 19፡35 )። "ከመላእክት" የሚለው ቃል ከሰማያዊ ፍጥረታት ወይም ከእግዚአብሔር አሳነስከው የሚልም ትርጉም ጥሩ ተቀባይነት አለው።

ከቁጥር 6-8 በዘፍ1፡26-28 ባለው ክፍል ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተሰጠውን ሥልጣን ያብራራል። እግዚአብሔር በመልኩና በምሳሌው በብዙ ክብር ቢፈጥረውም በርግጥ በሰው ልጅ ኃጢአት ምክንያት የሰው ዘር ሙሉ በሙሉ ሥልጣኑን አልተጠቀመም። ሆኖም ግን ስለ ተሰጠው ሥልጣን የሰው ልጅ ጌታን ማመስገን አለበት። ይህ ሥልጣን ደግሞ ከኃላፊነት ጋር የተሰጠ እንደነበረ ማንም መዘንጋት የለበትም። በተጠያቂነት ከተጠቀመ ትልቅ ክብር ነው። ጌታ የሰጠንን ሥልጣን ችላ ማለት የለብንም።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. የዚህ ጥናት ዓላማው ምንድ ነው? መዝ 8፡1-9 በማንበብ ቁ.1 እና ቁ.9 ደግመን ብናነብ ምን ትምህርት እናገኛለን።
2. ከጥናቱ መግቢያ ምን ተረዳችሁ?
3. መዝ 8፡2-4 በዚህ ክፍል "ከሕፃናትና ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ ስለ ጠላትህ፥ ጠላትንና ቂመኛን ለማጥፋት" ሲል ምን ማነጻጸሩ ነው? ምንስ ሊያስተምረን ፈልጎ እንደሆነ ተወያዩ?
4. መዝ 8፡5-8 ምን ትምህርት ይሰጠናል? የሰው ልጅ ምን እንዲያደርግ ይጠበቅበታል?
5. መዝ 8፡6-8 ከዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ጋር ምን ይገናኛል (ዘፍ 1፡26-28)
6. የሰው ልጅ የተሰጠውን ሙሉ ሥልጣን እየተጠቀመ ይገኛል ብላችሁ ታምናላችሁ? አዎን/አይደለም? ለምን?
7. ስለ አንድ የምታውቁት ፍጥረት አንስታችሁ ምኑ እግዚአብሔርን እንድናደቅ እንደሚያደርግ ተነጋገሩ
8. ዛሬ ሁላችንም ስለ ራሳችን እየአሰብን እንደተመቸን ጌታን እናመስግን

***መደምደሚያ፡-***

መዝ 8 እግዚአብሔርን ለማመስገን እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ምክንያቶችን የሚያቀርብ ምዕራፍ ነው። ጌታን የማመስገን ህይወት እንዲኖረን የራሳችንን አፈጣጠር ማየት ጥሩ ምክንያት ይሆናል። ጌታን ትንንሽ ልጆችም ማመስገን ይችላሉ (በምሳሌያዊ ንግግር ደግሞ ትሁታንና በመንፈሳቸው ዝቅ ያሉ የዋሆች)። ይህም ደግሞ በዓለም ላሉ ለእግዚአብሔር ጠላቶች ትልቅ ነን ለሚሉ ሁሉ የዓይን ዕፍረት ነው። የሰው ልጅ በውድቀቱ ምክንያት ከጌታ የተሰጠውን ክብር መጣሉ ከማሳዘን ውጭ የሰው ልጅ የእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ አለበት። ይህን ሁሉ በማሰብ እግዚአብሔር እንዲመሰገን ዘማሪው ይጠራል። ጌታ የራሱን መልክና ምሳሌውን ከማስቀመጡም በላይ በኃጢአት የሞተውን ማንነታችንን እንደገና ማደሱ ሙሉ ምስጋና እንድንሰጥ ፍቅር ጨምሮብናል።

## ጥናት አሥራ ሶስት
### የንባብ ክፍል
### መዝሙረ ዳዊት 95
### የአምልኮ መዝሙር
### የጉባኤ አምልኮ ግብዣ ወይም ጥሪ

**ዓላማ፡- የእግዚአብሔር ህዝብ ፈጣሪውን በደስታ እንዲያመልክ የቀረበ ጥሪ**

**መግቢያ፡-**

መዝሙር 95 በአምልኮ መዝሙሮች መካከል የሚካተት መዝሙር ሲሆን ለመጥቀስ ያህል መዝ 47, መዝ 93 መዝ 96-99 ማየት ይቻላል። ይህ ክፍል የእግዚአብሔር ህዝብ ታላቅና የተፈራውን እግዚአብሔርን፣ የአማልክት ሁሉ አምላክ የነገስታት ሁሉ ንጉስ የሆነውን፡ ጌታ እግዚአብሔርን በደስታ ወደ እግዚአብሔር ተጠግቶ አምላኩን እዲያመልከው የህዝቡን ልብና መንፈስ የሚያነሳሳና ክፍል ሲሆን በአንጻሩም ደግም እግዚአብሔር ሊከበር እና ሊፈራም የሚገባም አምላክ ስለሆነ የእግዚአብሔር ህዝብ **እግዚአብሔርን በማክበር እና** በመፍራት ሊያመልኩት የሚገባም እንደሆነም የሚያሳስብ ክፍል ነው። በአጭሩ ይህ ክፍል እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ህብረት መካከል በደስታ ቀረብ ተብሎ የሚመለክ አምላክ መሆኑን በማውሳት በሌላ ጎን ደግሞ እግዚአብሔር የሚያስፈራ አምላክ ስለሆነ በማክበር እና በፍርሃት የሚመለክ መሆኑን ያመለክታል። በአዲስ ኪዳን ሮሜ 12፡1-4 በሙሉ ማንነታችን እንድናመልክ ይጠይቀናል።

**የርዕስ ማብራሪያ**

**"የየዕለቱ መዝሙር"**

ማንኛውንም መዝሙር ከማጥናታችን በፊት ስለ መዝሙሩ የሚናገሩትን አመልካች ነገሮችን ማየት እንዳለብን ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰ ሁሉ ይህም መዝሙር በተመሳሳይ መልኩ የሚታይ ይሆናል። ንጉስ ዳዊት ከጻፋቸው የአምልኮ እና የውዳሴ መዝሙሮች መካከል የሚገኝ መዝሙር ሲሆን በመጀመሪያው ቁጥሮች ላይ እንደምንመለከተው ይህ ክፍል የእግዚአብሔር ህዝብ አምላኩና ፈጣሪውን በቅዱሳን ጉባኤ መካከል እንዲያመልከው ወደ አምልኮ ጉባኤውን የሚጠራ የየዕለቱ መዝሙር ነው። መዝሙሩም በተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች በመከፋፈል መመልከት የሚቻል መሆኑን ሳይዘነጋ፡ ለዚህ ጥናት እንዲመች ከዚህ በታች ባለው ሁኔታ ምዕራፉን በመከፋፈል መመልከት እንችላለን።

**1፡ ከቁጥር 1-2 እግዚአብሔርን ህዝቡ በደስታ እንዲያመልክ ስወደ አምልኮ የሚጠራ ወይንም የሚጋብዝ ሲሆን።**

**2፡ ከቁጥር 3-5 ያለው ደግሞ እግዚአብሔር መመለክ ያለበት በምን ምክንያቶች እንደሆነ ያትታል ።**

**3፡ ከቁጥር 6-7 ላይ ህዝቡን ለስግደትና ለመገዛት ጥሪ ያቀርባል ወይንም ይጋብዛል። እንዲሁም በቁጥር 7 ላይ ህዝቡ ሊሰግድለትና ሊገዛለት የሚገባበትን ምክኒያቶች በመጥቀስ ሃሳቡን ያጠናክራል።**

**4፡ ከቁጥር 8-11 ያለው እግዚአብሔር በማክበር እና በመፈራት መመለክ እንደሚገባው ያሳስባል።**

1. **መዝ 95፡1-2 በደስታ ወደ እግዚአብሔር ቀርበን እናምልከው** (የአምልኮ ጥሪ)
   "1 ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን **ለአምላክ ለመድሃኒታችን እልል እንበል፡**
   **2 በምስጋና ወደ ፊቱ እንድረስ፡ በዝማሬም ለእርሱ እልል እንበል።"**

የእግዚአብሔር ህዝብ ለጊዜው ታይቶ በሚጠፋ ነገርና በምድራዊ ስኬት ላይ ተመርኩዞ ሳይገደብ የደስታው ምንጭ እና የምስጋናውን ምክንያት እግዚአብሔርን ብቻ ታሳቢ በማድረግ ሲሆን፡ በእግዚአብሔር ጉባኤ

እግዚአብሔርን በሚያመልኩት ህብረት መካከል ተመልካች ሳይሆን በደስታ አምላኩን ሊያመሰግን እና ሊያምልክ እንደሚገባ ይህ መዝሙር ያመለክታል። እግዚአብሔር አምላኩ እና አዳኙ የሆነለት ህዝብ በህብረት አምልኮ በጉባኤ ወደ እግዚአብሔር ቀረብ ብሎ በብዙ ደስታ በመዝሙርና በውዳሴ በቅኔ እና በማህሌት ወዳዳነው አምላክ በታላቅ አምልኮ ሊተምም ይገበዋል። ይህም የእግዚአብሔር ህዝብ እግዚአብሔርን ለማምለክት በሚነሳበት ጊዜ መጀመሪያ ሊታሰብ የሚገባው እነርሱ ህዝብ ይሆኑኛል እኔም አምላክ እሆናቸዋልሁ ያለውን እና አምላክ እንዲሆነን እኛም የርስቱ ህዝቡ እንድንሆን የፈቀደውና የወደደውን እግዚአብሔር ነው እንጂ ሰው የሚታሰብበት ሊሆን አይገባም፡ ኤር 24፡7, 32፡38።

2. **መዝ 95፡3-5 እርሱ ብቻውን አምላክ ነውና ሊመለክ የሚገባቸው ምክንያቶች አሉት**

"3 እግዚአብሔር ታላቅ አምላክ ነውና ፡ በአማልክትም ሁሉ ላይ ታላቅ ንጉስ ነውና፡
4 እግዚአብሔር ህዝቡን አይጥላቸውም፡ ይምድር ዳርቻዎችም በእጁ ውስጥ ናቸው።
የተራሮች ክፍታዎች የእርሱ ናቸው።
5 ባሕር የእርሱ ናት፡ እርሱም አደረጋት፡ የብስንም እጆቹ ሠሩአት።"

በእነዚህ ቁጥሮች ደግሞ መዝሙረኛው ከላይ የእግዚአብሔር ህዝብ ጉባኤውን ወደ አምልኮ ከጠራ እና ከጋበዛቸው በኃላ በመቀጠል እግዚአብሔር ለምን ሊመለክ እንደሚገባው ዝርዝር ምክንያቶችን ያቀርባል፡ በመነሻውም እግዚአብሔር ሰዎች አማልክት ናቸው እንደሚሏቸው ሳይሆን እርሱ ታላቅ አምላክ በመሆኑ ምክንያት ምስጋና እና አምልኮ ይገባዋል ይላል። በመቀጠልም ሰዎች በቀደመውም ይሁን በዚህ ዘመን ቢሆን አማልክት የሚሏቸው ብዙ ቢኖሩም እነርሱ የሰው እጅ ስራዎች ብቻ ሲሆኑ እግዚአብሔር ግን የአማልክት ሁሉ ንጉስ ነውና አምልኮ ይገበዋል ይላል። ሌላው መዝሙረኛው የሚያቀርበው ምክንያት ይህ ታላቅ የአማልክት ሁሉ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ህዝቡን <u>የማይጥል የታመነ አምላክ ስለሆነ</u> በደስታ ሊመለክ እንደሚገባው አስረግጦ ያስረዳል። ለዚህም የዘጸዓት ታሪክ ጥሩ ማስረጃ ነው ። እንዲሁም በሰማያት ውስጥ ያለው የማይታየውም ሆነ በምድር የሚታየው ነገር ሁሉ የተፈጠረውና የተገኘው በእርሱ ስለሆነ እናምልክ ይላል። ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድን ማንበብ ጥሩ ማስረጃ ይሆናል።

3. **መዝ 95፡6 ለእግዚአብሔር ልንሸነፍ ያስፈልገናል**

**"6 ኑ እንስገድ ለእርሱም እንገዛ፡ በእርሱ ባደረገን በእግዚአብሔር ፊት እንበርከክ።**
**7 እርሱ አምላካችን ነውና፡ እኛ የማሰማሪያው ህዝብ የእጅም በጎች ነንና።"**

መዝሙረኛው ቁጥር አንድ ላይ **ለእግዚአብሔር ህዝብ ለጉባኤው ያቀረበው የምስጋና እና የአምልኮ ግብዣ ጥሪ እንደነበር** የማይዘነጋ ሲሆን። በዚህ ቁጥር ላይ የመዝሙሩ አዝማች ወደ ሆነው ሃሳብ ይመለስና የእግዚአብሔርን ህዝብ በድጋሚ ለአምልኮ ጥሪ እያቀረበ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልገናል። እንስገድ እንገዛ እንበርከክ በሚሉት ቃላት አጅቦ የተነሳበትን የምስጋና እና የአምልኮና ሃሳብ ወደ ሚቀጥለው ደረጃ ሲወስደው እንመለከታለን። ይህም ስግደትና መገዛት ለእግዚአብሔር የመማረክና ሙሉ በሙሉ የመሸነፍ ወደ ሆነው የአምልኮ ደረጃ ሲያመጣቸው እናያለን። የአምልኮ ትርጉም ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ከመስገድ፣ ለእግዚአብሔር ከመገዛትና ለእግዚአብሔር ከመሸነፍ ያነስ ሊሆን አይገባውም። አምልኮ ሙሉ ማንነትን ለፈጣሪ ማስገዛት ነው። ራዕ 4፡10-11 ( ይነበብ) እንዲሁም ከዚህ ጋር በማያያዝ መዝሙረኛው ስግደትም ሆነ መገዛት የሚያስፈልግበትን ምክኒያቶች ያነሳል፡ አንደኛ እግዚአብሔር እርሱ አምላካችን ስለሆነ ( ሃሌ ሉያ እርሱ እግዚአብሔር አምላኬ ነው) ስለዚህም ስግደትም ሆነ መገዛቴ የተገባው ነው፡። ቀድሞ ነገስታት የህዝቡ እረኞች እና ጠባቂዎች ናቸው ተብሎ ይታሰብ እንደነበረው እንዲሁ እግዚአብሔር የህዝቡ ጠባቂ ስለሆነ የእግዚአብሔር ህዝብ ሊሰግድለት እና ሊገዛለት ሙሉ ለሙሉ ሊማረክ ይገባል ብሎ በእነዚህ አስረጂ ምክኒያቶች የተነሳበትን ሃሳብ ያጠናክራዋል።

4. **መዝ 95፡8-11 ካለፈውን ታሪክ በመማር በማክበር እና በመፍራት እናምልክ**

"8 በምድረበዳ እንደ ተፈታተኑት፡ እንዳስቆጡት ጊዜ
ዛሬ ድምጹን ብትሰሙ ልባችሁን አታጽኑ፡
9 የተፈታተኑኝ አባቶቻችሁ ፈተኑኝ ስራዬንም አዩ፡
10 ያቺን ትውልድ አርባ አመት ተቆጥቻት ነበር
ሁል ጊዜ ልባቸው ይስታል፡ እነርሱም መንገዴን አላወቁም አልኩ
11 ወደ እረፍቴም እንዳይገቡ በቁጣዬ ማልኩ፡

**5. እግዚአብሔር የማምለክ እድል ከሰጠ በልማድ ሳይሆን በመፍራትና በመቀደስ መመለክ አለበት።**

**በእነዚህ ቁጥሮች መዝሙረኛው ለ**እግዚአብሔር ህዝብ ለእግዚአብሔርን ለማምለክ እና ለእግዚአብሔር ለመሸነፍ ወይንም ለመገዛት ያቀረበውን ግብዣ እና ጥሪ በተመለከት አጽንኦት በመስጠት ጉባኤው በደስታ ወደ አምላኩ ጠጋ ብሎ በነጻነት አምላኩን እንዲያመልክ የተፈቀደለት መሆኑን ታላቅ ክብር ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ታላቅ እና የሚያስፈራ አምላክ ሆኖ ሳለ በህዝቡ ሊመለክ ሊወደስ የፈቀደ መሆኑ ሰው ሊገምተው ወይንም ሊረዳው ከሚችለው በላይ ነው፡ እንዲህ አይነቱ የአምልኮ ነጻነት ያለው የእግዚአብሔር ህዝብ ልብ ሊለው የሚገባው እውነት ደግሞ እግዚአብሔር ሲመለክ ሊከበር እና ሊፈራም የሚገባው መሆኑን ነው። ለዚህም ዘማሪው ከቀደመው ከእግዚአብሔር ህዝብ ታሪክ በመጥቀስ ማስረጃውን በማቅረብ ጠንከር ባለ ማሳሰቢያ የተነሳበትን ሀሳብ ይደመድማል (ዘኁ14፡11 ፣ ዘጸ 17፡7) 78፡18 ቁ.41)። በሚገባ ነገር ጌታን ካላመለክን ጥፋት ልገጥመን ይችላል።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. **በመዝ 95፡1 ዘማሪው ያቀረበው ጥሪ ወይንም ግብዣ ለማንና ምንድ ነው? እንዴት ነው በ**እግዚአብሔር ደስ የሚለን? ይህን ሃሳብ እንዴት ትረዱታላችሁ?
2. **መዝ 95፡ 1-2 በህዝቡና እና በ**እግዚአብሔር መካከል ያለው ግኑኝነት ምንድነው?
3. **ደስታ፣ ምስጋና፣ ዝማሬ እና እልልታ የሚሉትን ሃሳቦች የሚያያይዛቸው ምንድነው? አማኝ እንዴት ማምለክ እንዳለበት ይናገራል (በስሜቶቻቸው)?**
4. **ከመዝ 95፡3-5** እግዚአብሔርን ለማምለክ ዘማሪው ያቀረባቸውን ምክንያቶች በዝርዝር ተነጋገሩባቸው?
5. **በመዝ 95፡ 6 ላይ ዘማሪው ያቀረበው ጥሪ ወይም ግብዣ ምንድነው?**
6. **ስግደት መገዛት እና መንበርከክ የሚሉት ቃልት የሚያመለክቱት አብይ ወይንም ዋና ሃሳብ ምንድነው(ውጫዊ አምልኮ) ?**
7. **በመዝ 95፡7 ለ**እግዚአብሔር ለመሸነፍ የሚያስፈልግበትን ዘማሪው የሰጣቸወን ምክንያቶች ተወያዩበት።
8. **ከመዝ 95፡8-11** እግዚአብሔርን በማክበር እና በመፍራት ማምለክ ያለብን ለምንድነው?
9. **ይህ ጥናት ለዛሬ ዘመን አምልኮ ምን ትምህርት ይሰጣል?**

***መደምደሚያ፡-***

ይህ መዝሙር በየዕለቱ የእግዚአብሔር ህዝብ እንደ እግዚአብሔር ጉባኤ በህብረት እና በአንድነት ፈጣሪውን ስለ

ጌትነቱ በማስተዋል እና በመረዳት ክልብ በሆነ ደስታ በውዳሴ እንዲያመልክ የሚጋብዝ እና የሚጣራ መዝሙር እንደሆነ መረዳት እንችላለን። እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ጉባኤ መካከል በደስታ ሊመለክ ይገባዋል፡፡ በቤተክርስቲያን ውዳሴና ስግደታችን የሚገባው ለእርሱ እና ለእርሱ ብቻ ነው። መታዘዝና መገዛትም ለማንም አይገባም የተገባው ብቻውን አምላክ ለሆነው ለነገስታት ንጉስ ለጌቶች ጌታ ከአሁን ጀምሮ እስከ ለዘለአለም ለእርሱ ይሁን። አሜን። ታላቅ እና የሚያስፈራው እግዚአብሔር ለህዝቡ አምላክ ለመሆን የወደደ እና የፈቀደ ስለሆነ የእግዚአብሔር ህዝብም በዚህ መረዳት አምላኩን በሙሉ ደስታ እና ነጻነት በእግዚአብሔር ጉባኤ ሊያመልከው የሚገባ ሲሆን፡ አምልኮው እግዚአብሔር በማክበር እና በመፍራት ሊያደርገው እንደሚገባ መዘንጋት አይኖርበትም። ጌታ እንደሚገባ በቅድስና ካልተመለከ እንዳልታዘዙት ጊዜ እንደ እስራኤላውያን መጎዳት ሊሆን ይችላል።

## ጥናት አሥራ አራት
### የጽዮን መዝሙር
### የንባብ ክፍል
### መዝሙረ ዳዊት 46

**ዓላማ፡- እግዚአብሔር ለጽዮን ወይም ለህዝቡ ጽኑ ግንብና የማይደፈርስ ምሽግ መሆኑን ማሳየት**

**መግቢያ፡-**

ጽዮን ማለት ምሽግ ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ጽዮን የሚል ቃል ከ150 ጊዜ በላይ ተጠቅሶ ይገኛል። ይህች ከተማ ምድራዊና ሰማያዊ ኢየሩሳሌምን ታመለክታለች። ለእግዚአብሔር ሕዝብ መጠሪያም ይሆናል (ኢሳ 40፡1፣ዕብ 12፡22፣ ራዕ 14፡1)። ይህ ጥናት የሚመለከተው ስለ ጽዮን ከተጻፉት መዝሙሮች አንዱን ማለትም መዝሙር 46ን ይሆናል። መዝ 48፣76፣84፣87፣122 ተመሳሳይ መዝሙሮች ናቸው። መዝሙሩን የሚመራው መሪ ሀሳብ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለ ሆነ አንፈራም" የሚል ይሆናል።

ይህ መዝሙር ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ከተማ በመሆኗ ከጽዮን የቀረበ ምስጋና ነው። መዝሙር 46 የእግዚአብሔርን ኃልዎት በህዝቡ መካካል መገኘቱን ያደንቃል። መዝሙሩ የረዥም ጊዜ ትንቢታዊ መልእክትም አለው። ማለትም በአዲስ ኪዳን ያለውን የጌታ ህዝብ ያመለክታል። አንዳንድ ሰዎች መዝሙሩን የአሶር ንጉስ ሰናክሬም የይሁዳን ንጉስ ሕዝቅያስን ለመውረር በዛተ ጊዜ የተዘመረ መዝሙር ነው ይላሉ (2ነገስ 18-19 እና ኢሳ 36-38)። ሌሎች ደግሞ ንጉስ ኢዮሳፍጥን በዙሪያ የነበሩ የአህዛብ ነገስታት ለመውረር በመጡ ጊዜ የተዘመረ መዝሙር ነው ይላሉ(2ዜና 20፡1-30)። ይህ ሀሳብ የማይጣል በጣም ጥሩ ሀሳብ ቢሆንም ከዚያም በኋላ በነበሩ ዘመናት በቤተ መቅደስ ይዘመር የነበረ መዝሙር መሆኑን መዘንጋት የለብንም። አሁንም ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ይዘመራል። መዝሙሩ በሶስት አንጓዎች ይከፈላል (1-3፣4-6፣8-10)። የመዝሙሩ መሪ አዝማች ያለው ቁ.7 እና 11 ላይ ነው።

**የርዕስ ማብራሪያ**

**"ለመዘምራን አለቃ ስለ ምሥጢር የቆሬ ልጆች መዝሙር"**

ማንኛውንም መዝሙር ከማጥናታችን በፊት ስለ መዝሙሩ የምናገሩትን አመልካች ነገሮችን ከራሱ ከምዕራፉ መግቢያ ማየት እንዳለብን ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰ ይህም መዝሙር እንደዚሁ ይሆናል። በርእሱ **"የቆሬ ልጆች"** የሚለው ሐረግ ከሌዊ ዘር ከቆሬ (የቀዓት ዘር) ወገን የሆኑትን መዘምራንን የሚያመለክት ሲሆን በቅዳሴ ሥርዓት የሚያገለግሉ መዘምራን ናቸው። ቆሬ የሌዊን ልጅ የቀዓትን ቤተሰብ ይወክላል። አሳፍ ከሌዊ ልጆች **የጌርጌሶናዊያን** ሲሆን ኤዶታም ደግሞ **የመራሬ** ወገን ነው (ዘኍ 3፡17-51)። ሌዊ ከያዕቆብ 12ቱ ልጆች አራተኛው ልጅ ነው። እግዚአብሔር ለራሱ አገልግሎትም የለየው መሆኑ ይታወቃል።

መዝሙር 46 ምናልባት ሴቶች መዘምራንን በከበሮ በማጀብ ወደ ቤተ መቅደስ እየተጓዙ የተዘመረ መዝሙር እንደሆነ ይገመታል። መዘምራኑ በጊዜው በነበሩ የሙዚቃ ዕቃዎች የተደራጁና እጅግ የተቀናጁ ሲሆን የመዘምራኑ አለቃም በመዝሙር ጸጋ የተቀባ ነበር።

**ሀ. መዝ 46፡1-3 እግዚአብሔር ጽኑ ምሽግ ነው**

***"1 አምላካችን መጠጊያችንና ኃይላችን፥ ባገኘን በታላቅ መከራም ረዳታችን ነው።***

***2 ስለዚህ ምድር ብትነዋወጥ፥ ተራሮችም ወደ ባሕር ልብ ቢወሰዱ አንፈራም።***

***3 ውኆቻቸው ጮኹ ተናወጡም፥ ተራሮችም ከኃይሉ የተነሣ ተናወጡ"።***

ቁ.1 የሚያስተምረን እግዚአብሔር የዓለማትና የሰዎች ሁሉ ፈጣሪ ስለሆነ ዓለማት ማለትም ተፈጥሮም ይሁን የሚያስፈሩሩ የፖሎቲካ አገዛዞች ትልቅና አስቸጋሪዎች የሚመስሉ ቢሆኑም እግዚአብሔር ለጽዮን መጠጊያና አሸናፊ ነው። እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስለሆነ በወቅቱ የጽዮን ተቃዋሚዎች ጽዮንን ማሸነፍና ማጥፋት እንደማይችሉ የሚያሳይ የመዝሙር ክፍል ነው። ይህ ክፍል የእስራኤልን ህልውና የሚፈታተኑ ጠላቶችን በምሳሌያዊ ንግግር ይናገራል። በዘጸዓት፣ በነገስት መጽሐፍት፣ በዳንኤል፣ በአስቴርና በሌሎችም መጽሐፍት እንደምናየው የግብጽ ፈሪኦኖች፣ የአሶር ነገስታት፣ የባቢሎን፣ በፋርስ የሃማ ዛቻ እና ሌሎችም ጽዮንን ወይም የእግዚአብሔርን ህዝብ ሊያጠፋ አልቻሉም።: መዝ 104፡6-9 ተመሳሳይ መልዕክት አለው። ዋናው ቁም ነገር ጽዮን ማለትም ህዝቡ በጠላቶቹ ድል ለማግኘት እግዚአብሔርን ማመንና መፈለግ ብቻ ይጠበቅባታል። በአዲስ ኪዳንም የሐዋርያው ጳውሎስ ትምክህቱም ይህ ነበር። “እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ሊቃወመን ይችላል?” (ሮሜ 8፡31)። እንደምናውቀው በታሪክ ቤተ ክርስቲያንን ሊያጠፋ የቻለ ማንም የለም።

**ለ. መዝ 46፡4-6 እግዚአብሔር በከተማው (ከሕዝቡ) ጋር ነው**

***4. የወንዝ ፈሳሾች የእግዚአብሔርን ከተማ ደስ ያሰኙሉ ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ።***
***5. እግዚአብሔር በመካከልዋ ነው አትናወጥም፥ እግዚአብሔርም ፈጥኖ ይረዳታል።***
***6.አሕዛብ ተናወጡ መንግሥታትም ተመለሱ እርሱ ቃሉን ሰጠ፥ ምድርም ተንቀጠቀጠች።***

በዚህ ክፍል ደግሞ ከላይ የተጠቀሱ ነገሮች ሁሉ ይኑሩ እንጂ የእግዚአብሔር ጥበቃና ጸጋ ያልተለያትን ጽዮንን እምነቷ በእግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ መዝሙሩ ያረጋግጣል። ብርቱና ኃያል አምላክ ከጽዮን ወይም ከሕዝቡ ጋር ስለ ሆነ ጽዮንን የሚያስፈራራት ነገር አያሰጋትም ። ይህ ደግሞ ለከተማዋ ወይም ለህዝቧ ያለመናወጥ ምክንያቷ ነው። በዚህ ክፍል **“የወንዝ ፈሳሾች”** የሚለው ሀረግ የእግዚአብሔርን የማያቋርጥ የደስታ ተሃዲሶና በረከት የሚያመለክት ነው። ከአየር ቅጽበት ህልውና ይልቅ የእግዚአብሔር ህልውና ለከተማዋ/ለህዝቡ ይፈጥናል። ቤተ ክርስቲያን እምነቷ ከበረታ የእግዚአብሔር መገኛ ቦታ ነች። እኛም የአዲስ ኪዳን አማኞች ምንም የሚያስፈራራን ነገር ቢኖር በጌታ መታመን ብቻ ነው የሚያስፈልገን። ጌታ ኢየሱስ ለህዝቡ እንዲህ ሲል ቃል ገባ “እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ” (ማቴ 28፡20)።

**ሐ. መዝ 46፡8-10 የእግዚአብሔር ሰላም ለዓለም ሁሉ የሚደርስ ይሆናል**

ወደ ሚቀጥለው ክፍል ከመሸጋገራችን በፊት ቁ. 7 እና ቁ. 11 የመዝሙሩ አዝማች ሆኖ የህዝቡ ምላሽና መሪ ሀሳብ እንደሆነም ልንዘነጋ አይገባንም። (ቁ.7 “የሠራዊት ጌታ ከእኛ ጋር ነው የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው”። ቁ.11 “የሠራዊት ጌታ ከእኛ ጋር ነው የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው”።)

**8 የእግዚአብሔርን ሥራ፥ በምድር ያደረገውንም ተአምራት እንድታዩ ኑ።**
**9 እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ጦርነት ይሽራል። ቀስትን ይሰብራል፥ ጦርንም ይቈርጣል በእሳትም ጋሻን ያቃጥላል።**
**10 ዕረፉ፥ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ እወቁ በአሕዛብ ዘንድ ከፍ ከፍ እላለሁ፥ በምድርም ላይ ከፍ ከፍ እላለሁ።**
**11 የሠራዊት ጌታ ከእኛ ጋር ነው የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው።**

ዘማሪው በዚህ ክፍል ለእግዚአብሔር ሥራ ትኩረት በመስጠት እርሱ የሰጠውን ድል ለሌሎች ይመስክራል፣ወደ እርሱ እንዲመጡም ይጋብዛል። ጌታ ህዝቡን እንዴት እንደሚያድንና እንደሚጠብቅ እዩ ይላል። ይህ ክፍል ደግሞ በዓለም ላይ የሆኑትን ታሪኮች መታየት እንዳለበትም ያሳስባል። እርሱ ሲፈልግ በበረዶ ድንጋይ የህዝቡን ጠላቶች ያሸንፋል **“ከእስራኤልም ልጆች ፊት እየሸሹ በቤትሖሮን ቍልቍለት ሲወርዱ፥ ወደ አዜቃ እስኪደርሱ ድረስ እግዚአብሔር ከሰማይ ታላላቅ የበረዶ ድንጋይ አወረደባቸውና ሞቱ የእስራኤል ልጆች በሰይፍ ከገደሉአቸው ይልቅ በበረዶ ድንጋይ የሞቱት በለጡ” (ኢያሱ 10፡11)**። ጌታ እግዚአብሔር ያደረገውን ድል ማሰብና ማየት ወደ ፊትም ለሚመጡ ነገሮች ሁሉ በእርሱ ላይ

ትልቅ እምነት እንዲኖረን ይረዳናል።

ቁ.9 በወቅቱ የሰራ ቢሆንም ትንቢታዊ መልእክት ያለው ክፍል እንደሆነም ብዙዎች ያምናሉ ማለትም ወደ ፊት መሲህ (ክርስቶስ) ጦርናትን አስወጊዶ በዓለም ስለሚያመጣው ሰላም የሚያመለክት ክፍል ነው። መዝ 65፡6-7፣ 1ሳሙ 2፡4 እና ኢሳ 9፡2-7 ለዚህ ቁጥር ተጨማሪ ማስረጃዎች ናቸው። ቁ.10 ላይ የተጠቀሰው "**እረፉ**" የሚል ቃል **<u>እወቁ፣አስተውሉ ልብ አድርጉ ማለት ነው</u>**። ምክንያቱም በዓለማትና በነገስታት ሁሉ ላይ እግዚአብሔር ገዥ ስለሆነ የምድር ህዝብ የእግዚአብሔርም ህዝብ ጭምር ሀሳቡን ሁሉ ለእርሱ መተው አለበት። ይህ ድል በክርስቶስ መወለድ መሞትና ከሞት መነሳት የሆነ ታሪክ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ 12፥7 እና 32 ላይ እንደሚከተለው ብሏል "7 ነገር ግን የእናንተ የራሳችሁ ጠጕር ሁሉ እንኳ የተቈጠረ ነው፤ እንግዲያስ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች ትበልጣላችሁ። ... 32 አንተ ታናሽ መንጋ፥ መንግሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና አትፍሩ" ይላል። የክርስቶስ ዳግም ምጽዓት የዓለም መጨረሻና ለሚያምኑ ሁሉ የዘላለም ሰላም ነው። ይህንን ጽዮን ማወጅ አለባት።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ጽዮን ማለት ምን ማለት ነው? ማንን ወይንም ምንን ይወክላል?
2. ከመግቢያ እንደተረዳችሁት የመዝሙር 46 መሪ ሀሳብ ምንድ ነው? ምንን ያመለክታል?
3. በመዝ 46፡1-3 ባለው ክፍል "ስለዚህ ምድር ብትነዋወጥ፥ ተራሮችም ወደ ባሕር ልብ ቢወሰዱ አንፈራም" ብሎ ዘማሪው ስለ ጽዮን ከዘመረው ምን እንማራለን? የምን ምሳሌያዊ ንግግር ነው?
4. የመዝ 46፡4-6 ዋናው መልዕክት ምንድ ነው? "የወንዞች ፋሳሾች" የሚለውስ ሀሳብ ምንን ያመለክታል? ከቤተ ታሪክ ጋር ምን ይገናኛል?
5. የእግዚአብሔር ከተማ ያለመናወጧ ዋና ምክንያት በዚህ ክፍል መሰረት ምንድ ነው? ለቤ/ክንስ ምን ትምህርት አለው?
6. በመዝ 46፡8-10 ባለው ክፍል "የእግዚአብሔርን ሥራ፥ በምድር ያደረገውንም ተኣምራት እንድታዩ ኑ" ከሚለው መልእክት ምን ተረዳችሁ? ከላይ ካሉት ጥቅሶች ጋር ምን ግንኙነት **አለው?**
7. **ቁ.10ን በማንበብ "እረፉ" የሚለውን ቃል ትርጉም ተነጋገሩ? ቤት ቁጭ በሉ ማለት ነው? ካልሆነ ምንድ ነው?**
8. **ይህ መዝሙር ከዛሬይቷ ጽዮን ጋር እንዴት ይገናኛል?**

***መደምደሚያ፡-***

በአጠቃላይ መዝ 46 እንደሚነግረን እግዚአብሔር አሸናፍ እንጂ ተሸንፎ አያውቅም። ብዙ ሰዎች ሞክረው አልቻሉትም። ስለዚህ እግዚአብሔር ለህዝቡ ወይም ለጽዮን አስተማማኝ መጠጊያ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሁል ጊዜ ህዝቡን ለመርዳት አብሮ ይኖራል። ቤ/ክንንም በየቀኑ ያድሳታል። በመጨረሻም ክርስቶስ ፊጹም ሰላም እንደምስጣት ቤተ ክርስቲያን ማወቅ አለባት። ቤ/ክ እኛ ነን።

# ጥናት አሥራ አምስት

**የንባብ ክፍል**
***መዝሙር 2፡1-12***
***የመሢህ መዝሙር***

***ዓላማ፡-***

እግዚአብሔር ለሚፈልገው ዓላማ ሰዎችን ማለትም ነገስታትንና ሌሎችንም እንደሚቀባና ጠላቶቹም ልቋቋሙት እንደማይችሉ ማሳወቅ። (በግሪክ ቋንቋ ክርስቶስ ማለት የተቀባ ማለት ነው። ስለዚህም ከመሢህ መዝሙር የእግዚአብሔርን ቅባት ዓላማና በአዲስ ኪዳንም ከክርስቶስ ህይወትና አገልግሎት ጋር ያለውን ግንኙነት ማሳወቅ ተጨማሪ ነገር ይሆናል)።

***መግቢያ፡-***

መሢህ ማለት በእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ሥራ የተቀባ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርም ይሁን ሰዎች የተለያዩ ሰዎችን ለሚፈልጉት ሥራ ይቀቡ ነበር። ንጉስ፣ካህን፣ነቢይና ሌሎችም ይቀቡ ነበር። ለምሳሌ እግዚአብሔር በኢሳ 45፡1 “እግዚአብሔር ለቀባሁት፥ አሕዛብንም በፊቱ አስገዛ ዘንድ የነገሥታትንም ወገብ እፈታ ዘንድ፥ በሮቹም እንዳይዘጉ መዝጊያዎቹን በፊቱ እከፍት ዘንድ፥ ቀኝ እጁን ለያዝሁት ለቂሮስ እንዲህ ይላል” ብሎ እግዚአብሔር ነገስታትን ለሚፈልገው ዓላማ እንደሚቀባ ያረጋግጣል። እስራኤላውያን በቅባት ያምኑ ነበር።

መዝሙር 2 ስለ መሢህ ቅባት ይናገራል። መዝ 45፣72፣110፣132 እና ሌሎችም በመዝሙር መጽሐፍ ስለ መሲህ የምናገሩ መዝሙሮች ናቸው። በተለይም ስለ ንግስና ቅባት ለምሳሌ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ስለ ሳኦል 1ሳሙ 10፡11 ፣ 1ሳሙ 24፡10፣ስለ ዳዊት 1ሳሙ 16፡13፣ስለ ኢዮአስ 2 ነገስ 11፡12 እንዳሉ ማየት ይቻላል። በእርግጥ በጊዜው ለዳዊትና ለዘሮቹ ንግስና ጊዜ እንዲዘመር የተዘጋጀ መዝሙር እንደሆነ በዙዎች ቢያምኑም (2ሳሙ 7) በኋላ በነበሩት ዘመናትም ተዘምሯል።

የአዲስ ኪዳን ሙሉ ተፈጻሚነቱን ሲናይ ግን እግዚአብሔር ህዝቡን ከኃጢአት እስራት ነጻ ሊያወጣ በቀባውና ከንጉስ ዳዊት ዘር በመጣው በክርስቶስ ህይወትና አገልግሎት ነው (ሉቃስ 4፡17-19፣ኢሳ 61፡1)።

ክርስቶስ በሉቃ 24:44 እንደሚከተለው አለ “ ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት **በመዝሙራትም** ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው”። በዮሐ 4፡25 የሳምራዊቷ ሴት መሲህን ይጠብቁ እንደነበረ ተናገረች።

***መዝሙር 2፡1-12***

1. ***መዝ 2፡1-3 ንጉሱን የቀባው እግዚአብሔር በዙሪያ ካሉት ከጠላቶቹ ይበልጣል***

እነዚህ ቁጥሮች በትክክሉ ካነበብናቸው በዙሪያው የነበሩ ነገሥታት እግዚአብሔር የቀባውን ንጉስ እናጥፋው ብለው የሚማካከሩ መሆናቸውን ነው። ቁ.1 ላይ **“ለምን?”** የሚለው ጥያቄ እንዴት ቢደፍሩ ነው ማለት ነው። በእግዚአብሔርና እርሱ በቀባው ላይ መነሳት የማይቻልና የማይሆን ነገር ነው። ቁ.2 እንደሚነግረን እነዚህ ጠላቶቹ በተቀባው ንጉስ ላይ ብቻ ሳይሆን የተነሱት ሰማይና ምድርን በፈጠር በአምላኩም ጭምር ነው። አህዛብ፣ነገስታትና አለቆች የእስራኤልን ነጻነት ስለማይፈልጉ የተቀባውን ንጉስ ማጥፋት ይፈልጋሉ።

ይህን ሀሳብ ሐዋርያው ጴጥሮስ በሐዋ 4፡26 ስለ ክርስቶስ ሲናገር “የምድር ነገሥታት ተነሡ አለቆችም በጌታና በተቀባው ላይ አብረው ተከማቹ ብለህ የተናገርህ አምላክ ነህ” ብሎ ከብሉይ ኪዳን ጋር ያገናኛል። ቁ.3 ሥራ ላይ ልውል የማይችል ምክራቸውን ይናገራል።

2. ***መዝ 4-6 እግዚአብሔር በናቁት ላይ ምላሽ ይሰጣል***

ከቁ.1-3 በመሲህ ላይ ያሰቡትንና የተወያዩትን ነገር እግዚአብሔር አይቶ በፊጹም ማድረግ የማይችሉት ነገር እንደሆነ ከቁ.4-6 ይናገራል። የሰው ልጅ በትዕቢቱ የተታለለ ነው። በዚህም ምክንያት ለራሱ በሚጠቅመው የህይወት መመሪያ ማመጹ ለራሱ ውድቀት ነው። ደግሞም ሰው የራሱ ፈቃድ ስላለው እግዚአብሔር እውነቱን እንዲያውቅ ብዙ በሮችን ከመክፈት በላይ አያስገድድም። ጌታ ከጥንት ጀምሮ በእርሱ በማይታመኑትና በአምላክነቱም በሚነሱት ላይ በንቀት ይናገራል። ቁ.6 "እኔ ግን ንጉሤን ሾምሁ በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ"'ይህ ቁ. እንደሚነግረን መሲሁንና እግዚአብሔርን አህዛብ ለማጥፋት ይመካከሩ እንጂ እራሱ እግዚአብሔር መሲሁን (የተቀባውን ንጉሱን) በጽዮን በተቀደሰው ተራራው እንደሾመ ይናገራል። እግዚአብሔር የፈለገውን ሊያደርግ የሚከለክለው የለም። ፈሪኦንም ሊከልክለው አልቻለም። እግዚአብሔርን ስለ ናቀ ተቀጣ። እግዚአብሔር ጠላቶቹ እያዩት ንጉሱን ይቀባል።

**3. መዝ 2፡7-9 መሲሁ-የተቀባ ንጉስ የእግዚአብሔርን የንግስናውን አዋጅ ያውጃል**

በእነዚህ ቁጥሮች በእግዚአብሔር የተቀባው ንጉስ የእግዚአብሔርን ስም እንደሚያውጅ ይናገራል። ቁ.7 **"አንተ ልጄ ነህ እኔም ዛሬ ወለድሁ"። ይህ ክፍል መሲሁ የእግዚአብሔር እንደሆነ የምናገር ክፍል ነው።** በወቅቱ የተነገረለትን ንጉሱን (ዳዊትን) ከእርሱ የሚወጣው ንጉስ የእግዚአብሔር ልጁ ወይም አገልጋይ ይሆናል ማለት ነው ((2 ሳሙ 7፡12-17)። ይህን ክፍል በአዲስ ኪዳን የሐዋ ሥራ 13፡33 ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ትንሳዔ ሲሰብክ ጠቅሶታል። የዕብራውያን ጸሐፊም ስለ ልጁ ስለ ክርስቶስ ተናግሮታል (ዕብ 1፡5)። ይህ ልጁም የዓለም ገዥ እንደሚሆን ይናገራል። ንጉስ ሰለሞንን ያየን እንደሆነ በብዙ ክብርና ዝና እስራኤልን ገዝቷል። ነገር ግን መዝ 2 እና 2ሳሙ 7 የሚናገራቸው ሁሉ በዳዊት፣በሰለሞንና በእግዚአብሔር በተቀቡ በሌሎች ነገስታት ሙሉ በሙሉ የተፈጸሙ አይደሉም። ስለዚህ ሌላ የሚያሟላ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ምድር መጣ። ቁ.8 ላይ"ለምነኝ" የሚለው ቃል ልጁ ከእርሱ ጋር ፊጹም አንድነትና ህብረት እንዳለው የሚያሳይ ሀሳብ ነው። ሌላው ደግሞ ልጁ ህብረት እንዲያደርግ የተጠየቀ ሀሳብ ነው ይላሉ።

በቁ.9 "በብረት በትር ትጠብቃቸዋለህ፥ እንደ ሸክላ ሠሪ ዕቃዎች ትቀጠቅጣቸዋለህ" የሚለው ቃል በነገስታት ጊዜ የተፈጸመ ቢሆንም የፊጻሜ ዘመንም ጭምር የሚናገር ትንቢት ነው። ራዕ 12፡5 "አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ"። ራዕ 19፡15 "አሕዛብንም ይመታበት ዘንድ ስለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል፤ እርሱም በብረት በትር ይገዛቸዋል፤ እርሱም ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቍጣውን ወይን መጥመቂያ ይረግጣል")። የጌታ ዳግም ምጽዓት ዓለማት ሙሉ በሙሉ የሚገዙበት ጊዜ ይሆናል።

**4. መዝ 2፡10-12 እግዚአብሔርና በመሲሁ ላይ ለሚያምጹ ማስጠንቀቂያና የመመለስ እድል ይሰጣቸዋል**

በማጠቃለያም በእነዚህ ቁጥሮች እነዚህ እግዚአብሔርንና በእርሱ የተቀባውን የናቁት እንዲገዙና እንዲመለሱ ይጠየቃሉ፤ ያስጠነቅቃቸዋልም። ቁ.12 "ዝቅ ብላችሁ ሳሙት" የሚለው ቃል መገዛትን ያሳያል።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. *መሲህ ማለት ምን ማለት ነው? መሲህ በብሉይ ኪዳን ማን ነው?*
2. *መሲህ በብሉይ ኪዳን ለምን አስፈለገ?*
3. *መዝ 2፡1-3 በማንበብ የተረዳችሁትን ተወያዩ። አህዛብ፣ነገስታትና አለቆች በማን ላይ ነው የተነሱ? ለምን?*
4. *መዝ 2፡4-6 ከቁ.1-3 ጋር ምን ግንኙነ አለው?*
5. *መዝ 2፡6 "እኔ ግን ንጉሤን ሾምሁ በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ" የሚለውን ቃል የተናገረው ማን ነው? ለምን?*
6. *መዝ 2፡7-9 የመሲሁ ሥራ ምንድ ነው? በወቅቱ ወይም አሁን?*
7. የመዝ 2፡10-12 ማጠቃለያ መልዕክት ምንድ ነው?
8. በአዲስ ኪዳን ከመዝ ምዕራፍ 2 ተጠቅሷል? ከማን ጋር አያይዘው ነው የጠቀሱ?

***መደምደሚያ፡-***

መሲህ ለአንድ ዓላማ የተቀባ ነው። **<u>ይህንን ቃል በጊዜው የነበሩ ሰዎች እንደ እኛ ኢየሱስ ነው ብለው መናገር እንደማይችሉ ማወቅ ጥሩ ይሆናል።</u>** እግዚአብሔር ንጉሱን ለህዝቡ ነጻነት ይሾማል። ማንም ሊቋቋመውም አይችልም። ስምዖን በሉቃ 2፡26 "በጌታም የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር" ብሎ ስለ ክርስቶስ ይናገራል። በብሉይ ኪዳን ንጉሱ ህዝቡን ነጻ እንዲያወጣ እንደሚቀባ ክርስቶስ በእግዚአንብሔር የተቀባ (መሲህ) ኃጢአተኞችን ነጻ የሚያወጣ ንጉስና ካህን ነው። ስለ ክርስቶስ ጴጥሮስ በሉቃ 9፡20 "ከእግዚአብሔር የተቀባህ " ነህ ብሎ መሰከረለት። እንደዚሁም በሐዋ 4፡26 "ምድር ነገሥታት ተነሡ አለቆችም በጌታና በተቀባው ላይ አብረው ተከማቹ ብለህ የተናገርህ አምላክ ነህ" ብሎ ከብሉይ ኪዳን ጋር ያገናኛል። የራዕይ ትንቢት ራዕ 12፡5 አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ። ራዕ 19፡15 "አሕዛብንም ይመታበት ዘንድ ስለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል፤ እርሱም በብረት በትር ይገዛቸዋል፤ እርሱም ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቍጣውን ወይን መጥመቂያ ይረግጣል")። በመጨረሻም ግዛት ሁሉ ለእርሱና ለልጆቹ ይሆናል።